| ተ.ቁ | የጉዳዩ አይነትና አመልካቾች | መዝገብ ቁጥር | ገፅ |
|---|---|---|---|
| 1. | **1. የንብረት መብት** | | |
| | 1.1. እነ አቶ ረጋሳ ስዩም(17 ሰዎች) | 33/09 | |
| | 1.2. እነ ወ/ር ኤልሳቤጥ ተስፋ ጽዮን(2 ሰዎች) | 131/07 | |
| | 1.3. እማሆይ ባንችአምላክ ደርሶልኝ | 08/08 | |
| | 1.4. ወ/ሮ ሃሳይ ዶዮ | 08/07 | |
| | 1.5. ወ/ሮ አለሚቱ ገብሬ | 913/05 | |
| | 1.6. ወ/ሮ ሃና አድማሱ | 16/08 | |
| | 1.7. አቶ ሙየዲን የኑስ | 17/08 | |
| | 1.8. አቶ ነጋሽ ዱባለ | 20/08 | |
| | 1.9. ቄስ ወርቁ ዳዲሞስ | 22/08 | |
| | 1.10. አቶ ኪዳነ ማርያም ተክሉ | 38/09 | |
| | 1.11. ወ/ሮ እናት በለጠ | 39/09 | |
| 2. | **2. ፍትህ የማግኘት መብት** | | |
| | 2.1. አቶ አንድነት ከበደ | 31/09 | |
| | 2.2. እነ ውዴ ተስፋሁን(3 ሰዎች) | 37/09 | |
| | 2.3. አቶ ሚልክያስ አየለ | 08/10 | |
| | 2.4. አቶ ታሪኩ መኮንን | 18/08 | |
| | 2.5. አቶ ሕዝቅኤል ማራ | 94/07 | |
| 3. | **3. የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች** | | |
| | 3.1. ወ/ሮ ራኒያ አህመድ ኢብራሂም | 08/09 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 3.2. ወ/ሮ አዜብ ቱፋ | 15/08 | |
| | **4. ወላጅን የማወቅ መብት** | | |
| | 4.1. ህጻን ሱራፌል ዘውዱ | 896/05 | |
| | 4.2. አቶ ብርሃኑ ረጋሳ | 21/08 | |
| | 5. **የንግድ ምልክት ቅድሚያ የማግኘት መብት** | | |
| | 5.1. ሲክስ ኮንቲኔንተስ ሆቴል ኢንክ | 34/09 | |
| | 6. **ሙያን የመምረጥ መብት** | | |
| | 6.1. እነ አቶ ወሰን አለሙ (2 ሰዎች) | 19/08 | |

## የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

### ራዕይ

የሕገ መንግሥት የበላይነት ሰፍኖ፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሁሉም መስክ እኩልነታቸውና የፈጣን ኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸው ተረጋግጦ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ፣ ስር የሰደደ አንድነትና ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ዳብሮ ማየት፣

### ተልእኮ

ሕገ መንግሥቱን በመተርጎም፣ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቦች አንድነት ስር እንዲሰድና እንዲዳብር በማድረግ፣ በክልሎች መካከል ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ግንኙነቶችን በማዳበር፣ ፍትሐዊና ውጤታማ የድጎማ በጀትና የጋራ ገቢዎች ማከፋፈያ ቀመር በማዘጋጀትና በመወሰን፣ ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን በማጥናትና በመለየት፣ እንዲሁም ዜጎች ሕገ መንግሥቱን ጠንቅቀው አውቀው ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በቁርጠኝነት መሥራት፣

### እሴቶች

- ትክክለኛና አድልዎ የሌለበት ውሳኔ መስጠት፣
- በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታና በፖለቲካ አመለካከት ወዘተ… ልዩነት ሳይደረግ ሁሉንም በእኩልነት ማገልገል፣
- የሚመለከታቸውን ሁሉ በማሳተፍ የተለያዩ ሐሳቦችና አመለካከቶች በነፃ እንዲንሸራሸሩ ማድረግ፣
- የምክር ቤቱን ባለድርሻዎች በቅንነት ማገልገል፣
- ባለድርሻዎችን ሊያሳትፍ በሚያስችል ግልፅ አሰራር ተመስርቶ ማከናወንና የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች ግልፅ ማድረግ፣
- ለሕገ መንግሥቱ፣ ለሕዝቡ፣ ለሕሊናቸው እንዲሁም ምክር ቤቱ ለሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ታማኝና ተገዥ መሆን፣
- ማናቸውንም አመለካከቶችና ልዩነቶች በመቻቻልና በመከባበር መንፈስ ማስተናገድ፣
- አቤቱታዎችን በሕገ መንግሥቱና በአዋጅ በተቀመጡ የጊዜ ገደቦች ምላሽ እንዲያገኑ ማድረግ፣
- ለሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፣

## ስልጣንና ተግባር

- ሕገ መንግሥቱን ይተረጉማል፣
- የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ያደራጃል፣
- የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ይወሰናል፣
- በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት ስር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፣
- በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ ይፈልጋል፣

- የክልሎችና የፌዴራል መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፣
- በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ይለያል፣
- ማንኛውም ክልል የፌዴራል ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራል መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፣
- በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 103(5) መሠረት የምርጫ ቦርድ በሚያቀርብለት ረቂቅ መሠረት የምርጫ ክልሎች አከላለልን ይወስናል፣
- በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 99 መሠረት ለፌዴራል ወይም ለክልል መንግሥታት ተለይተው ባልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ስልጣኖች ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጋራ ይወሰናል፣
- በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 70(2) መሠረት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በሚደረግ የጋራ ስብሰባ የአገሪቱን ፕሬዝዳንት ይመርጣል፣
- በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 105(1) እና (2) በተደነገገው መሠረት ሕገ መንግሥቱን በማሻሻል ሂደት ይሳተፋል፣

በስልጣኑ ስር በሚካተቱ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ጋር በመተባበር ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፤ እንደአስፈላጊነቱም ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣

- የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣
- የራሱን አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመርጣል፡፡

የተከበሩ ወ/ሮ ኬሪያ ኢብራሂም

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ መልዕክት

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62(1) እንዲሁም ምክር ቤቱን ለማጠናከር ሥልጣን እና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 4(1) ዓ.ም መሠረት ሕገ መንግሥቱን የመተርጐም ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህ ጋር በተየያዘ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 11(2) ሥር የሕገ መንግሥት ነክ ጉዳዮች ውሳኔ ውጤት በሚለው ስር ውሳኔው በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅም ምክር ቤቱ ለዚሁ ዓላማ በሚያዘጋጀው ልዩ መጽሔት ታትሞ እንደሚወጣ ይደነግጋል፡፡

የፌደሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ተመርምረው ትርጉም ያስፈልጋቸዋል በሚል ለምክር ቤቱ በሚያቀርባቸው የውሳኔ ሀሳቦችና ትርጉም አያስፈልጋቸውም በማለት ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ይግባኝ ባዮች በሚያቀርቡት ቅሬታ ላይ ተመስርቶ ከተወያየ በኋላ የመጨረሻ ውሳኔ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

እነዚህ የፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔዎች በሕገ መንግሥቱ የተሰጡ መብቶችን ለማስከበር የሚረዱ በመሆናቸው ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ በተለይ ለፍትህ አካላት፣ ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለምርምር ተቋማትና በአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ሕገ መንግሥታዊ ግንዛቤን በመፍጠር ረገድ እየተጫወቱት ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ቁጥር 3 መጽሔት ለህትመት በቅቷል፡፡

አስገዳጅ የሕገ መንግሥት ትርጉም ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋል ከጀመሩ አጭር ጊዜያት ያስቆጠሩ በመሆናቸው የብቃትም ሆነ የልምድ ውሱንነቶች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እነዚህ እጥረቶችም በውሳኔዎች ላይ አልፎ አልፎ ሲከሰቱ ይታያሉ፡፡

በዚህ መስክ የረጅም ዘመናት ታሪክና ልምድ ያላቸው አገሮችም ቢሆን ከስህተቶቻቸው እየተማሩ አሰራራቸውን እያዘመኑ ሄደዋል፡፡ እኛም ከነዚህ አገሮች ተሞክሮና ልምድ በመቀመር በውሳኔዎቻችን ላይ የሚሰጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ግብዓት በመውሰድ በሕገ መንግሥቱ የተሰጠንን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ጥረታችንን አጠናክረን እንደምንቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶች፣ ፍርድ ቤቶች፣ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ የዴሞክራሲ ተቋማት ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችና

በአጠቃላይ ህብረተሰቡ ለጥረታችን መሳካት የማይተካ ድርሻ አላቸውና ሁሉንም በምክር ቤቱ ሥም እያመሰገንሁ በቀጣይ ሥራዎቻችን ከጎናችን እንዳትለዩን በምክር ቤቱ ሥም ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

## የተከበሩ አቶ እሸቱ ደሴ

## የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ መልዕክት

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62(10) እንዲሁም ምክር ቤቱን ለማጠናከርና ሥልጣን እና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 52(1) እና (2) መሠረት ምክር ቤቱ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች እንደሚያቋቁም ተደንግጓል፡፡ በዚሁም መሠረት የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራውን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው የሚመሩለትን አቤቱታዎች ከሕገ መንግሥቱ ጋር በማገናዘብና እንደአስፈላጊነቱ በሙያው ጥልቅ እውቀት ከአላቸው የሕግ ምሁራን ጋር የአትኩሮት ውይይት (focus group discussion) በማድረግ፣ ለውሳኔ ሀሳቡ የሚያግዙ ልዩ ልዩ ግብዓቶች በማሰባሰብና በማካተት፣ አስፈላጊውን ምርመራና ማጣራት አድርጎ ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዩች ቋሚ ኮሚቴ በምክር ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ጥረቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ እነዚህን የምክር ቤቱን የውሳኔ ሃሳቦች የፍትህ፣ የዴሞክራሲና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የምርምር ተቋማት በየሥራዎቻቸው ውስጥ ተግባራዊ እንደሚያደርጓቸው በመተማመን በራሴና በቋሚ ኮሚቴው ስም መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!

## አጠቃሎ /Summary/

1. **የአመልካቾች እነ አቶ ረጋሳ ስዩም እና ተጠሪዎች እነ አቶ ሙስጠፋ ከድር ጉዳይ:-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**እነ አቶ ረጋሳ ስዩም (17 ሰዎች)
  - ተከራካሪ ወገኖች ... አመልካቾች - እነ አቶ ረጋሳ ስዩም (17 ሰዎች)

    ተጠሪዎች - እነ አቶ ሙስጠፋ ከድር (10 ሰዎች)
- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካቾች ለክርክር መነሻ የሆነው 6 ሄክታር የግጦሽ መሬት ከተጠሪዎች ጋር በጋራ ስንጠቀምበት የቆየን ቢሆንም አሁን ግን ተጠሪዎች ለብቻቸው ስለያዙት እንዲለቁልን በማለት ባቀረቡት ክስ መነሻነት በተካሄደ ክርክር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸው በመሆኑ በይዞታው ላይ ባለመብቶች ናቸው በማለት በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾችና ተጠሪዎች ይዞታውን በጋራ እንዲጠቀሙበት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 9፣ 40(5) እና 50 ስለሚጥስ ትርጉም እንዲሰጥልን በማለት አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው።
- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**
  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣40(5)፣ 50፣ እና
  - የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠ/ አስተዳደር አዋጅ ቁ. 130/99 አንቀጽ 15፣ 25፣
- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  ክርክር ያስነሳው ይዞታ የወል የግጦሽ መሬት መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶች ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የአመልካቾችን ሕገ መንግሥታዊ መብትን በሚጥስ መልኩ ይዞታው የተጠሪዎች የግል ይዞታ ነው በማለት መወሰናቸው አመልካቾች ከጋራ የግጦሽ መሬት ይዞታቸው የሚያፈናቅልና ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(5) ጋር የሚቃረን ነው። በመሆኑም ውሳኔው የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው።
- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

የፍርድ ቤቱ ውሳኔ አመልካቾች ከጋራ የግጦሽ መሬት ይዞታቸው የሚያፈናቅልና ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(5) ጋር የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካቾችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም፡፡

2. **የአመልካቾች እነ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ተስፋፅዮን እና ተጠሪ የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጉዳይ፡-**

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-*** እነ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ተስፋፅዮን (2 ሰዎች)
  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካቾች - እነ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ተስፋፅዮን (2 ሰዎች)

    ተጠሪ - የቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-***

  አመልካቾች ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በሕግ የሚፀና ጋብቻ መስርተው በጋራ ያፈሯቸው መኖሪያ ቤትና መኪናዎች በዜግነት ኤርትራዊ በሆኑት 2ኛ አመልካች ስም ተመዝግበው በመገኘታቸው ብቻ በስር ፍርድ ቤቶች 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በነበሩት እነ ተጠሪ በጨረታ በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ለነበሩት 3ኛ ወገን መሸጣቸው አግባብ ባለመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ያቀረቡት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ባለማግኘቱና ውሳኔው ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች እና በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1)(2) ስለ ንብረት መብት የተደነገገውን የኢትዮጵያዊቷ 1ኛ አመልካች መብትን ስለሚቃረን የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልን በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-***

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣32፣ 33፣ 40፣
  - የዜግነት አዋጅ ቁጥር 378/1996 አንቀጽ 21፣
  - የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 390፣ 391፣1185፣
  - ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው መመሪያ፣
  - ነሐሴ 01 ቀን 2001 ዓ.ም. የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ማስፈፀሚያ አንቀጽ 6(2)፣

- ***የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-***

ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የዜግነት መብት ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣምና የተሟላ አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ የ1922 የኢትዮጵያን የዜግነት ሕግ (እንደተሻሻለ) የሻረው የኢትዮጵያ የዜግነት አዋጅ ቁ.378/1996 አንቀጽ 21 የኢትዮጵያ ዜግነት ማጣት በዚያ ሰው የትዳር ጓደኛና ልጆች ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት አይኖርም በሚል በግልፅ ደንግጎ የሚገኝ ሆኖ እያለ በ1ኛ አመልካች ላይ የተላለፈው ውሳኔ ከዚህ በሚቃረን ሁኔታ መወሰኑ የ1ኛ አመልካችን የዜግነት እና የንብረት ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈጻሚነት የለውም፡፡

3. **የአመልካች እማሆይ ባንቺአምላክ ደርሶልኝ እና ተጠሪ አቶ አበባው ሞላ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**እማሆይ ባንቺ አምላክ ደርሶልኝ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - እማሆይ ባንቺ አምላክ ደርሶልኝ

  ወኪል፦ የአማራ ብ/ክ/መ/ የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ

  ተጠሪ - አቶ አበባው ሞላ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  ይህ ጉዳይ በገንዘብ ብድር ዕዳ መያዣነት ስም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 የተደነገገውን መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው፤ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው ተብሎ የተደነገገውን ሕገ መንግሥታዊ መብትን የሚጥስ የፍርድ ቤት ውሳኔን የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ በአመልካች አቤቱታ ላይ በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ ያቀረበበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣40(3፣4)፣ እና

- የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 19፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር ስምምነት በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በሚል የተደነገገውን ሕገ መንግሥታዊ ክልከላ የጣሰ እና አመልካችን ከይዞታቸው ያፈናቀለ በመሆኑ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የጣሰ ነው፤ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

**4. የአመልካች ወ/ሮ ሐሳይ ዶዮ እና ተጠሪዎች እነ አቶ ትንሳኤ ኩታሌ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**ወ/ሮ ሐሳይ ዶዮ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - ወ/ሮ ሐሳይ ዶዮ

  ተጠሪዎች - እነ አቶ ትንሳኤ ኩታሌ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  ይህ ጉዳይ የመሬት ሽያጭን የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ አመልካች ለተጠሪዎች በቃል ስምምነትና በአካባቢ ባህል መሠረት በጋራ አርሰን ምርቱን በጋራ ለመጠቀም ተዋውለን የያዙት የእርሻ መሬት ይዞታ ድርሻዬን አልለቅም በማለት በማስቀረታቸው የእርሻ መሬት ይዞታዬን እንዲለቁልኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከይዞታዬ ያለመነቀል ሕገ መንግሥታዊ መብቴን ስለጣሰ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጠኝ በማለት አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ9 (1፣2)፣13(1)፣ 40(3)፣
  - የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1845፣እና
  - የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የገጠር መሬት አስ/አጠ/ አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 2(7)፤

- ***የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-***

ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ9(2) እና 13(1) መሠረት ሕገ መንግሥቱን የማስከበር ግዴታ ስለተጣለባቸው የመሬት ሽያጭ ግልጽ ሆኖ ሲታይ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ተገቢውን ማጣራት ማድረግና መወሰን ሲገባው ሕገ ወጥ ለሆነ የመሬት ሽያጭ ውል ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ውሳኔ ማሳለፉ ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር ውሳኔ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- ***የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-***

የገዜ ጎፋ ወረዳ ፍርድ ቤት የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3) ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

**5. የአመልካች ወ/ሮ አለሚቱ ገብሬ እና ተጠሪ አቶ ጫኔ ደሳለኝ ጉዳይ፡-**

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-*** ወ/ሮ አለሚቱ ገብሬ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - ወ/ሮ አለሚቱ ገብሬ

  ተጠሪ - አቶ ጫኔ ደሳለኝ

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-***

ተጠሪው የአመልካች ይዞታ የሆነውን የእርሻ መሬት ለሃምሳ ዓመታት በኪራይ የያዝኩት ነው በማለት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያወጣበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን ክስ የይርጋ ጊዜን መሠረት በማድረግ ውድቅ በማድረጉ አመልካች ውሳኔው ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) እና አንቀጽ 35(7) ድንጋጌዎች ጋር ስለሚቃረን አጣሪ ጉባኤው የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት አቤቱቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-***
  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣35(7)፣ 40(3፣4)
  - የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1168(1)፣1845፣እና
  - የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የገጠር መሬት አስ/አጠ/ አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 8(1)/ሀ/፤

- ***የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-***

የፍ/ቤቱ ውሳኔ አመልካች በኪራይ የሰጡትን የእርሻ መሬት ይዞታ እንዲያጡ የሚያደርጋቸው ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማገኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው ከሚለው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን በመሆኑ በአመልካች የቀረበው አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል።

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  የጊምቢ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው ከሚለው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ነው፤ ስለሆነም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባውም።

**6. የአመልካች ወ/ሮ ሃና አድማሱ እና ተጠሪ ወ/ሮ የሻረግ ከበደ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**ወ/ሮ ሃና አድማሱ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - ወ/ሮ ሃና አድማሱ

  ተጠሪ - ወ/ሮ የሻረግ ከበደ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆንኩበትን ንብረት በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ ያጣሁ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 እና 37 መሠረት የእኩልነትና ፍትህ የማግኘት መብቴ ተጥሷል በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው።

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣ 25፣ 37፣ 40(1)፣ 78፣

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  አመልካች በፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ንብረት በአፈፃፀም ውሳኔ ማጣታቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ የቀረበው አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል።

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

አመልካች በዋናው ፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ንብረት በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ እንዲያጡ የተደረገበት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) የተደነገገውንና ዋስትና ያገኘውን የዜጎች የንብረት መብት የሚጥስ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም፡፡

7. **የአመልካች አቶ ሙየዲን ዮኒስ እና ተጠሪዎች እነ አቶ ናዚ አሊይ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ፡-**አቶ ሙየዲን ዮኒስ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - አቶ ሙየዲን ዮኒስ

  ተጠሪዎች - እነአቶ ናዚ አሊይ (2 ሰዎች)

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ፡-**

  አመልካች በአላባው እንዲጠቀም በማለት ለ1ኛ ተጠሪ የሰጡትን የጫት ተክል የሚገኝበት 6 ሄክታር የገጠር መሬት ይዞታ ለ2ኛ ተጠሪ ሸጦታል፡፡ በመሆኑም በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የመሬት ሽያጭ ውል ፈርሶ ይዞታው እንዲመለስላቸው ለመጠየቅ በፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ ፍርድ ቤቱ ይዞታው ሊመለስልህ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች፡-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣ 37፣ 40(3)፣ እና
  - የፍ/ብሔር ሕግ ቁ.1808(2)፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ፡-**

  በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የመሬት ሽያጭ ውል መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ከሚከለክለው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ አመልካች ከመሬት ሽያጭ ውሉ መፍረስ የሚያገኙትን ጥቅም አላረጋገጡም ብሎ የመሬት ሽያጭ ውሉ ሳይፈርስ እንዳለ እንዲቀጥል የወሰነው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) ጋር የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ፡-**

  የመሬት ሽያጭ ውሉ ሳይፈርስ እንዳለ እንዲቀጥል ጉዳዩን የተመለከተው የዶባ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውና በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የጸናው ውሳኔ የሕገ

መንግሥቱን አንቀጽ 40(3) የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም፡፡

8. **የአመልካች አቶ ነጋሽ ዱባለ ጉዳይ:-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**አቶ ነጋሽ ዱባለ

  - በፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች…አመልካች - አቶ ነጋሽ ዱባለ

  ተጠሪዎች - እነ የቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 17፣ ቀበሌ 20 ጽሕፈት ቤት

  ጣልቃ ገብ - የአዲስ አበባ ከተማ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች በተጠሪዎች የተያዘብኝ ቤት እንዲመለስልኝ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብቴን የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣ 40(1፣8)፣ እና
  - አዋጅ ቁ.47/67፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ በአፈፃፀም ከተረከቡ በኋላ ፍርዱ ሳይሻር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዱን ማምከኑ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  የሥራና ከተማ ልማት ቢሮው ካርታ የማምከን እርምጃ ከዚህ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ በተቃረነ ሁኔታ የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት ያሳጣ ሆኖ እያለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በፍርድ ባለመብት ሆነው እያለ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮው የአመልካችን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መሰረዙ በአግባቡ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል በሚል የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም፡፡

**9. የአመልካች ቄስ ወርቁ ዳዲሞስ እና ተጠሪዎች እነ ወ/ሮ ሰብለወንጌል ወርቁ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**ቄስ ወርቁ ዳዲሞስ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - ቄስ ወርቁ ዳዲሞስ

  ተጠሪዎች - 1. ወ/ሮ ሰብለ ወንጌል ወርቁ

  2. ወ/ሮ ማሚቴ ወሬራ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች የደቡብ ክልል እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በእኔ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 የተረጋገጠልኝን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሳጣ በመሆኑ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣34(3)፣ 40፣
  - የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1195፣1196፣ እና
  - የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት ውሳኔ ሕገ መንግሥቱ ለቤተሰብ ከሰጠው ከለላ አንጻር የሚቃረን ሆኖ ስለተገኘ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥቱ ለቤተሰብ ከሰጠው ጥበቃና ከለላ በተቃራኒ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ በጉዳዩ ላይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶችና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም፡፡

**10. የአመልካች አቶ ኪዳነ ማርያም ተክሉ እና ተጠሪዎች እነ አቶ ተ/ሚካኤል ክንደያ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**አቶ ኪዳነ ማርያም ተክሉ
    - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - አቶ ኪዳነ ማርያም ተክሉ

      ተጠሪዎች - እነ አቶ ተ/ሚካኤል ክንደያ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች ተጠሪዎች ይዘው የሚጠቀሙበት በገጠር የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታው የኔ ነው በማለት ይዞታው እንዲለቀቅላቸው በስር የወረዳ ፍርድ ቤት ላቀረቡት ክስ ፍርድ ቤቱ አመልካች ይዞታውን ለቀው በመሄዳቸዉ ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ለተጠሪዎች የተሰጣቸው ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ለመጠየቅ አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣ 40(4)፣
  - የትግራይ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ.239/2006 አንቀጽ 11፣

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  አመልካች ጧሪና ተንከባካቢ የሌላቸው አቅመ ደካማ ስለሆኑ የነበራቸውን በገጠር የሚገኝ የመሬት ይዞታ ቢለቁም በልዩ ሁኔታ በነበራቸዉ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚደነግገው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ውጭ ተጠሪዎች የመሬት ይዞታቸው በልማት ምክንያት በመወሰዱ የአመልካችን ይዞታ በምትክነት ይዘው እንዲጠቀሙ የተወሰነው የፍ/ቤቱ ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(4) ጋር ይቃረናል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም፡፡

### 11. የአመልካች ወ/ሮ እናት በለጠ እና ተጠሪ ወ/ሮ መብራት ቤዛ ጉዳይ:-

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**ወ/ሮ እናት በለጠ
    - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - ወ/ሮ እናት በለጠ

ተጠሪ - ወ/ሮ መብራት ቤዛ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች ተጠሪዋ ከሕግ ውጭ መሬቴን ስለያዘችብኝ ትልቀቅልኝ በማለት ላቀረቡት ክስ ጉዳዩን ያየው የወረዳ ፍርድ ቤት በይዞታው ላይ የቤተሰብ አባል ሆነው የተመዘገቡት ተጠሪና ልጆቻቸው በመሆናቸዉ ይዞታውን ሊለቁ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3) እና 40(4) በመጣስ ከይዞታዬ ያፈናቀለኝ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣ 40(3)(4)፣ እና
  - የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 6፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  አመልካችና ቤተሰባቸው አርሶ አደር መሆናቸውና መሬቱን ሲጠቀሙበት እንደነበረ ተረጋግጦ እያለ ፍርድ ቤት የሰው ማስረጃ በመስማት ብቻ የሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ከመሬት ያለመነቀል ሕገ መንግሥታዊ መብት ይቃረናል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም፡፡

12. **የአመልካች አቶ አንድነት ከበደ እና ተጠሪ የአፋር ብሔራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-** አቶ አንድነት ከበደ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - አቶ አንድነት ከበደ

    ተጠሪ - የአፋር ብሔራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች በክልሉ ፍትህ ቢሮ በቋሚነት ተቀጥረው ዓቃቤ ሕግ በመሆን ሲያገለግሉ የክልሉ ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ በሥነ ምግባር ጥፋት ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበቱ የወሰነ መሆኑን በመግለፅ አመልካችን በደብዳቤ ከሥራ ያሰናበታቸው ሲሆን

ውሳኔውን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመሆኑም አመልካች በክልሉ ዓቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጥፋት ቢኖርብኝ እንኳ ክስ ቀርቦብኝና ደርሶኝ፣ መልስና መከላከያዬን አቅርቤ ሳልከራከር በቀላጤ ደብዳቤ ብቻ ከሥራ ተሰናብተሃል ተብዬ መታገዴ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37፣ 41 እና 42 የተመለከቱትን መብቶቼን የሚቃረን በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-***

- የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣37፣ 41 እና 42፣ እና
- የአፋር ክልል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ደንብ ቁ. 12/2004 አንቀጽ 80(1)፣

- ***የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-***

  አመልካች በማያውቁትና ክስ ባልቀረበባቸው እንዲሁም የመከላከል መብት ባልተጠበቀላቸውና ከውሳኔ በጀመረው ሥነ ስርዓት ከሥራ እንዲታገዱ መደረጋቸው የክልሉ ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ደንብ ቁ.12/2004ን ያልተከተለና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 መሠረት ፍትህ የማግኘት መብትን የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- ***የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-***

  የአፋር ክልል ፍትህ ቢሮ ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም አመልካች ከሥራ እንዲታገዱ በደብዳቤ በማሳወቅ የሰጠው ውሳኔ የክልሉ ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ደንብ ቁ.12/2004ን ያልተከተለና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 መሠረት ፍትህ የማግኘት መብትን የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈፃሚነት የለውም፡፡

**13. የአመልካቾች እነ ውዴ ተስፋሁን እና ተጠሪ አቶ ለገሰ በላይ ጉዳይ፡-**

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-*** እነ ውዴ ተስፋሁን (3 ሰዎች)
  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካቾች - እነ ውዴ ተስፋሁን (3 ሰዎች)

    ተጠሪ - አቶ ለገሰ በላይ

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-***

አመልካቾች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚያቀርቡበት ጊዜ ስላለፈባቸው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ማስፈቀጃውን ተቀብሎ ይግባኛቸውን በአስር ቀናት ውስጥ እንዲያቀርቡ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በዚሁ መሠረት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ችሎት መቅረብ ሲገባው ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት በመቅረቡና ሰበር ሰሚ ችሎቱም ጉዳዩ መታየት የሚገባው በይግባኝ ሰሚው ችሎት ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ለሁለተኛ ጊዜ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት በማጣቱ አመልካቾች በሬጂስትራሩ ጥፋት ፍትሕ የማግኘትና የመሰማት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው መጣሱን ገልጸው የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ለመጠየቅ አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**
  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣37፣ 80(4)፣ እና
  - የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(2)፤
- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  አመልካቾች የይግባኝ ቅሬታቸውን ለይግባኝ ችሎቱ እንዳያቀርቡ መከልከላቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(1) መሠረት የተጠበቀውን የአንድ ዜጋን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚፃረር ውሳኔና ትእዛዝ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡
- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  ውሳኔው የአመልካቾችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**14. የአመልካች አቶ ሚልክያስ አየለ እና ተጠሪ የደምቢዶሎ ከተማ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ድርጅት ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**አቶ ሚልክያስ አየለ
  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - አቶ ሚልክያስ አየለ

    ተጠሪ - የደምቢዶሎ ከተማ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ድርጅት
- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው በሚል ተደንግጎ የሚገኘው ድንጋጌ ተጥሷል በሚል በአመልካች የቀረበን አቤቱታ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-***
  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣37(1)፣
  - የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 6፣
  - የኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 61/94 አንቀጽ 2(2)፣70፣ 71፣ 73(2)፣
  - የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት የከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 78/1996 አንቀጽ 20፣ እና
  - የኦሮሚያ ከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 40/1997 አንቀጽ 3፤
- ***የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-***

አመልካች በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳያቸውን ለመደበኛው ፍርድ ቤትም ሆነ ለክልሉ መንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርበው ማስወሰን ያልቻሉ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(10) የተጠቀሰው ፍትህ የማግኘት መብታቸው ተጥሷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው፡፡

***የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-***

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 37(1) ድንጋጌን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

**15. የአመልካች አቶ ታሪኩ መኮንን እና ተጠሪዎች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ጉዳይ፡-**

- ***የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-***አቶ ታሪኩ መኮንን
  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - አቶ ታሪኩ መኮንን

ተጠሪዎች - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ(2 ሰዎች)

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት አቤቱታዬን ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው አልቀበልም ማለቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37፣ እና
  - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 እና የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 24/2000፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጉዳይ ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው "አንቀበልም" ማለቱ አመልካች በጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ተብሎ ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ነው በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**16. የአመልካች አቶ ሕዝቅኤል ማራ እና ተጠሪ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንገዶች ባለስልጣን ጉዳይ:-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-** አቶ ሕዝቅኤል ማራ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - አቶ ሕዝቅኤል ማራ

    ተጠሪ - የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንገዶች ባለስልጣን

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

አመልካች በደረሰብኝ በደል ጉዳዬን ለፍርድ ቤት አቅርቤ የተወሰነልኝን ፍርድና በሙስና ትግል መነሻ የተሰጠኝን የሕግ ከለላ የሚያስፈፅም ባለመኖሩ ከሥራና ደሞዝ መታገዴ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37፣ 13(1)፣ 78(1) እና 80(1) ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም እንዲሰጥላቸው ለመጠየቅ አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**
  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣ 13(1)፣ 37፣ 78(1)፣ 80(1)፣
  - የፍትሐ ብሔር ስነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182፣ 183፣ 378፣ 372፣
  - የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39፣ 190(2)፣
  - የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4)፣ እና
  - የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግሥት ደንብ ቁ.126/2008 አንቀጽ 8(5)፤
- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

በአመልካች ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠበት በኋላ አመልካች የስር ፍርድ ቤት ፍርዱን እንዲያስፈፅምላቸው ሲጠይቁ ፍርዱን ማስፈፀም ሲገባው የመጨረሻው ውሳኔ በሰበር ደረጃ ከተወሰነ በኋላ አመልካች በዲስፕሊን ተሰናብተዋል የሚለውን የተጠሪ መ/ቤት ክርክር በመቀበል ፍርዱን ሳያስፈፅም መዝገቡን በብይን መዝጋቱ ሕገ መንግሥቱ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰጠው ስልጣን ጋር እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 ላይ ከሕገ መንግሥቱ የበላይነት ጋር እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ ከተደነገገው ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት ጋር የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- **የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

አመልካቹ ጉዳያቸውን በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶች እያቀረቡ ውሳኔ ማግኘታቸው እየታወቀ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ተጥሷል በሚል የአመልካች አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት የለውም::

17. **የአመልካች ወ/ሮ ራኒያ አህመድ ኢብራሂም እና ተጠሪ ዶ/ር ኢብራሂም መሀመድ ሀሰን ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ፡-**ወ/ሮ ራኒያ አህመድ ኢብራሂም
    - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - ወ/ሮ ራኒያ አህመድ ኢብራሂም

      ተጠሪ - ዶ/ር ኢብራሂም መሀመድ ሀሰን

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ፡-**

አመልካች በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 5 መሠረት በኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ግልጽ ፈቃዱን መስጠት እየተገባኝ ፈቃዴን በግልጽ ባልሰጠሁበት፣ እንደዚሁም በፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 5(2) መሠረት በቅድሚያ መጥሪያው በአግባቡ እንደደረሰኝ መረጋገጥ ሲገባው ሳይረጋገጥ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ በሌለሁበት ውሳኔ ከመስጠቱም በላይ የፍርድ አፈፃፀሙ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5፣ አንቀጽ 35(1፣ 2፣ 4፣ 7 እና 9) በፍርድ ቤቱ የተጣሱ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች፡-**
    - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣ 34(5)፣ 35(1፣2፣4፣7 እና 9)፣ እና
    - የአዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4፣ 5(1፣2)፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ፡-**

በሸሪዓ ፍ/ቤቱ አንደኛው ወገን በሀይማኖቱ ሕግ የመዳኘት ፍላጎት እንዳለው በአግባቡ ሳይረጋገጥ የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሊሰጥበት ይገባል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ፡-**

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የአመልካችን እና የተጠሪን ጉዳይ በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34 እና 35 የተደነገጉትን የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች እንዲሁም የሴቶች መብት ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

**18. የአመልካች ወ/ሮ አዜብ ቱፋ እና ተጠሪ አቶ አለማየሁ መንግሥቱ ጉዳይ:-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**ወ/ሮ አዜብ ቱፋ

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - ወ/ሮ አዜብ ቱፋ

  ተጠሪ - አቶ አለማየሁ መንግሥቱ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  ከተጠሪ ጋር በጋብቻ እያለን የተሰራ ቤት የጋራችን ሆኖ እያለ በአግባቡ እንኳ ባልተሰሙ የሰው ምስክሮች በመመስረት ቤቱ የተጠሪ የግሉ ነው በማለት በፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 35(1)፣ 25 እና 37 ይጥሳሉ በማለት አመልካች በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥላቸው አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣25፣34(1)፣ 35(1፣7)፣ 37፣ 79(3)፣
  - የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63(1)፣እና
  - የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79(1)፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(1)፣ 35(7) መሠረት አመልካች በጋብቻና በፍቺ ጊዜ ያላቸውን የእኩልነትና ንብረት የማፍራት መብት የሚጋፋና ፍርድ ቤቶች በግልጽ ድንጋጌ ባለመመራት የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 79(3) የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፤ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ ስለተገኘ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በየደረጃው ባሉ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም፡፡

**19. የአመልካች ህፃን ሱራፌል ዘውዱ ጉዳይ:-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:- የህፃን ሱራፌል ዘውዱ እናት እሙሃይ ገ/ኢየሱስ**

  - ተከራካሪ ወገኖች...አመልካች- የህፃን ሱራፌል ዘውዱ እናት እሙሃይ ገ/ኢየሱስ

    ተጠሪ - አቶ ዘውዱ መርሻ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36 የተመለከተው የሕፃናት መብትና ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብት ስምምነትን የሚጥስ ስለሆነ ይህ እንዲታረም በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት የአመልካቹ ህፃን ሱራፌል ዘውዱ እናት የሆኑት ወ/ሮ እሙሃይ ገ/ኢየሱስ አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣36(1)/ሐ/(2)፣ እና
  - የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 4፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሕጻኑ አባት አይደለም በማለት መወሰኑና ሰበር ሰሚ ችሎቱም የአመልካች አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉ በሞግዚቷ ስህተትና በስነ ስርዓታዊ ጉዳይ የሕፃኑን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ ውሳኔ መስጠቱ የሕፃኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም የሚጎዳና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1)/ሐ/እና(2) የተደነገገውን ሕፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት የሚጥስ ስለሆነ ጉዳዩ የልጁን ሕገ መንግሥታዊ መብት በሚያስጠብቅ መልኩ ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ስለሚገባ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1)/ሐ/ እና (2) የተደነገገውን ሕፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

20. **የአመልካች አቶ ብርሃኑ ረጋሳ እና ተጠሪ ወ/ሮ መስከረም ምትኩ ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**አቶ ብርሃኑ ረጋሳ
    - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካች - አቶ ብርሃኑ ረጋሳ

      ተጠሪ - ወ/ሮ መስከረም ምትኩ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍቃዴን ባልሰጠሁበት እና ባልተከራከርኩበት የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 31፣ 36(1)/ሐ/(2) የተደነገገውን የሚቃረን ነው በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው።

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)(4)፣13፣ 31፣34(5)፣ 36(1)/ሐ/(2)፣ 78(5)፣
  - የሸሪዓ ሕግ ክታብ ሙቅኒል ሙህታጅ 3ኛ ክፍል ከገጽ 452-455፣ እና
  - የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 4፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  ጉዳዩ በየደረጃው ቀርቦላቸው የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የወሰኑት ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 36(1)/ሐ/(2) ጋር የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል።

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤት እና በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም።

21. **የአመልካች ሲክስ ኮንቲኔንትስ ሆቴል ኢንክ (Six Continents HotelsInc.) እና ተጠሪ ክራውን ሆቴል (ባለቤት ወ/ሮ ዘውዲቱ መስፍን) ጉዳይ፡-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:**
    - ሲክስ ኮንቲኔንትስ ሆቴል ኢንክ (Six Continents Hotels Inc.)

- ተከራካሪ ወገኖች …. አመልካች - ሲክስ ኮንቲኔንትስ ሆቴልስ ኢንክ (Six Continents Hotels Inc.)

ተጠሪ - ክራውን ሆቴል (ባለቤት ወ/ሮ ዘውዲቱ መስፍን)

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  "CROWNE PLAZA" በሚል መጠሪያ የተመዘገበው የንግድ ምልክት የቀዳሚነት መብት ካለው "CROWN HOTEL" ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ "ክራውን" ከሚለው ቃል በኋላ አንዲት ፊደል በመጨመር "ክራውኔ" በማለት ተጠቃሚውን ህብረተሰብ በሚያሳስትና በሚያሳክር ሁኔታ በመቅረጽ የተጠሪን ሆቴል መልካም ስም የሚጎዳና ከፍተኛ ቁሳዊ ጉዳት የሚያደርስ ስለሆነ የአመልካች የንግድ ምልክት ሊፈርስ ይገባል በማለት ተጠሪ ባቀረቡት ክስ መነሻነት በተካሄደ ክርክር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የአመልካች "CROWNE PLAZA" የንግድ ምልክት ከተጠሪ "CROWN HOTEL" በሚል መጠሪያ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ መገኘቱ በአዋጅ ቁ. 501/98 አንቀጽ 7(1) መሠረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ እና ሕጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም በማለት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3)/ሀ/ መሠረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ከማረም የስልጣን ገደብ በማለፍ፣ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ሙያዊ እና አለም አቀፋዊ አሰራሮች ተፈትሾ የሁለቱ የንግድ ምልክቶች እንደማይመሳሰሉና እንደማያሳክሩ ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ ፍሬ ነገርን በመመልከት መወሰኑ ከተጠቀሰው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት በማለት አመልካች አቤቱታ ያቀረበበት ጉዳይ ነው።

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**
  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣41(4-7)፣ 43(1)፣ 80(3)/ሀ/፣
  - የአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 2(12)፣ 5፣ 6፣ 7(1)፣24፣
  - የአዋጅ ቁጥር 320/95 አንቀጽ 6፣ እና
  - የደንብ ቁጥር 273/2005 አንቀጽ 19(1)/3/፣

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3)/ሀ/ ከተሰጠው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን በማለፍ የአመልካች "CROWNE PLAZA" የንግድ ምልክት ከተጠሪ "CROWN HOTEL" በሚል መጠሪያ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በመገኘቱ በአዋጁ ቁ. 501/98 አንቀጽ 7(1) መሠረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ እና ሕጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም ሲል መወሰኑ የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ማከናወኑን ያረጋግጣል፤…በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሕጉን በጠባብ በመተርጎም ውሳኔ የሰጠበት አግባብ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ይህም ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**22. የአመልካቾች እነ አቶ ወሰን አለሙ እና ተጠሪዎች እነ የአማራ ብ/ክ/መ/ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም ጉዳይ:-**

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቅራቢ:-**እነ አቶ ወሰን አለሙ (2 ሰዎች)

  - ተከራካሪ ወገኖች … አመልካቾች - 1. አቶ ወሰን አለሙ

  2. አቶ ዳዊት ኦቲኖ

  ተጠሪዎች-1. የአማራ ብ/ክ/መ/ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም

  2. የአማራ ብ/ክ/መ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ:-**

  አመልካቾች ማየት የተሳናቸው በመሆናቸው በዳኝነት ወይም በዓቃቤ ሕግነት የሥራ ዘርፍ ለመሰማራት ከሌሎች ሰልጣኝ የሕግ ባለሙያዎች እኩል ዕጣ በማውጣት ሂደቱ እንዲካተቱ ላቀረቡት ጥያቄ ተጠሪዎች ከዓለም ዓቀፍም ይሁን ከአገር አቀፍ ልምድ አንፃር ማየት የተሳናቸውን በዳኝነት መደብ የማስራት ልምድ እንደሌለና እንደተቸገሩ በመግለፅ እንዲሁም የዳኝነት ሥራ ከአለው አስቸጋሪነት አንፃር ማየት የተሳናቸውን መድቦ ማሰራት ሊፈጥር የሚችለውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሻለው የሥራ ስምሪት ዓቃቤ ሕግ መሆኑን በመገንዘብ ወደ ዓቃቤ ሕግ ነት የመደቧቸው

መሆኑን በመግለፅ የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41(2) የተቀመጠው በመረጥነው ሙያ የመሰማራት መብታችን የጣሰ ነው በማለት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ነው፡፡

- **የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባስነሳው ጉዳይ የተጠቀሱ የሕግ ድንጋጌዎች:-**

  - የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1)፣25፣ 41(2)፣

  - የአዋጅ ቁጥር 568/2000 አንቀጽ 2(8)፣4፣እና

  - የአዋጅ ቁጥር 676/2002 አንቀጽ 27፤

- **የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ:-**

  በተያዘው ጉዳይ ከሥራው ባህርይ በሚል መነሻ በአሰራር የተጣለው ገደብ ኢትዮጵያ ከተቀበለችው ዓለም አቀፍ ስምምነትም ሆነ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ከወጣው አዋጅ በተለይ በሌሎች አገራት ካለው ተሞክሮ አንፃር በበቂ ጥናት ወይም ምክንያት ላይ የተመሰረተ እና የግድ አስፈላጊ በሆነ ቅድመ ሁኔታ ላይ መሠረት ያደረገ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ያሰራር ልማዱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41(2) የተጠቀሰውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚያጣብብ ነው፡፡ እንዲሁም አመልካቾች በአሰራር ልማዱ ልዩነት የተደረገባቸው በመሆኑ የተያዘው ልማድ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 "ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡" በሚል የሰፈረውን የእኩልነት መብት የሚጋፋ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው፡፡

- **የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ውሳኔ:-**

  ተጠሪዎች ተቀባይነት በሌለው ልማዳዊ አሰራር መሠረት የሰጡት ውሳኔ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 41(2) ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ ሥራውን እና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው በሚል የተደነገገውን እንዲሁም በአንቀጽ 25 የተደነገገውን የአመልካቾች ሕገ መንግሥታዊ የእኩልነት መብት የሚጋፋ በመሆኑ የተጠሪዎች የልማድ አሰራር እና ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

1. የፌ/ም/መ/ቁ 34/09

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካቾች፡-** እነ አቶ ረጋሳ ስዩም (17 ሰዎች)

**ተጠሪዎች፡-** እነ አቶ ሙስጠፋ ከድር (10 ሰዎች)

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የግጦሽ መሬትን ከመጠቀም መብት ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክር ሲሆን የክሱ ይዘትም ጪሞ ኡስማን ቀበሌ የሚገኝና ክርክር የተነሳበት 6 ሄክታር መሬት አዋሳኙን በመጥቀስ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ከተጠሪዎች ጋር ለግጦሽ በጋራ ስንጠቀምበት ቆይተን ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪዎች ስለያዙብን ይልቀቁልን በማለት ክስ ስላቀረቡ ነው፡፡

ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳውን የይዞታ መሬት ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በኛ እጅ የሚገኝ፣ ስንጠቀምበት የቆየንና የይዞታ ማረጋገጫ የወሰድንበት በመሆኑ በይዞታው ላይ መብት አለን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመመዘን

ተጠሪዎች ባለይዞታ መሆናቸውንና ያለተቃውሞ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆናቸውን ጠቅሶ ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ይዞታውን በሕጋዊ መንገድ ስለመያዛቸው በማስረጃ ባለማረጋገጣቸው እንዲሁም አመልካቾች ይዞታውን ሲጠቀሙ መቆየታቸውን በማስረጃ በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 25 መሠረት ይዞታውን አመልካቾችና ተጠሪዎች በጋራ እንዲጠቀሙበት ሲል ወስኗል፡፡

ይህም ውሳኔ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦ የፀና ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸው መሆኑን በማስረዳታቸው በይዞታው ላይ ባለመብት ናቸው በማለት የዞኑን ፍርድ ቤት እና የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ስልጣኑ ተመልክቶ ጉዳዩ አያስቀርብም ብሏል፡፡

አመልካቾች ሰኔ 9 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለጉባኤው ባቀረቡት ጥያቄ እኛ አመልካቾች ከፊል አርብቶ አደር በመሆን ለረጅም ጊዜ ለግጦሽ ስንጠቀምበት የቆየነውን የወል መሬት ፍርድ ቤቶች የተጠሪዎች የግል ይዞታ ናቸው በማለት መወሰናቸው የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 9፣ 40(5) እና 50 ስለሚጥስ ትርጉም እንዲሰጥልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቶች የሰጧቸውን ውሳኔዎች ከተጠቀሰው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን መሆን አለመሆኑን መርምሯል፡፡

አመልካቾች ተጣሰብን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በጋራ በመያዝ ለግጦሽ ሲጠቀሙበት የቆዩትን የገጠር መሬት ያለአግባብ አጥተናል የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ከፍርድ ቤቶች ውሳኔ ጋር በማጣመር እንደመረመርነው አመልካቾች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የመሬት ይዞታ በተመለከተ ጉባኤው በደብዳቤ ቁ.አጠ1436/03/08 በቀን 08/03/08 ዓ.ም ለክልሉ የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ቢሮ በጻፈው ደብዳቤ በአንድ ይዞታ ላይ ሁለት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዴት እንደተሰጠ አስተያየት እንዲሰጥበት ጠይቋል፡፡ በዚሁ መሠረት የክልሉ የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ቢሮም በቀን 02/06/08

ዓ.ም በቁ.BLBE-/1451/108 በጻፈው መልስ ክርክር ወደ አስነሳው ስፍራ ባለሙያዎችን በመላክ ማጣራት አድርጓል፡፡

በዚሁም መሠረት ክርክር የተነሳበት መሬት በ1996 ዓ.ም በተደረገ የመሬት ልማት የጋራ መሬት ተብሎ መለካቱን በተለያየ ወቅት ከነበሩ የቀበሌው የመሬት ልማት ኮሚቴዎችና የአካባቢ የሰፈር ሽማግሌዎች አነጋግረው ያረጋገጡ መሆኑን በሌላ በኩል እነ አቶ ሙስጠፋ ከድር (10 ሰዎች) አለን ብለው ያቀረቡት የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው የገጠር መሬት ምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያላለፈ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

በተጨማሪም በእጃቸው ይዘውት የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ስርዝ ድልዝ ያለው ተፍቆ የተሞላበት እና በወረዳው የገጠር መሬትና አካባቢ ጥበቃ ጽሕፈት ቤት የሚገኘው ቀሪ ማለትም የገጠር መሬት የሚመዘገብበት መዝገብ ላይም በተመሳሳይ መልኩ ተፍቆ የተሞላ እና የመሬት ልኬት ኮሚቴዎች በቀበሌው ደረጃ የሚዘጋጅ ቅጽ ላይ ያልፈረሙበት በመሆኑ ይህ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በዚህም መሠረት የተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሲታይ የገጠር መሬት ልኬትና ምዝገባ በዚሁ በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁ.130/99 አንቀጽ 15 መሠረት የሚከናወነው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬትና የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ ነው፡፡ ነገር ግን በያዝነው ጉዳይ የክልሉ የገጠር መሬትና አካባቢ ቢሮ የተጠሪዎች ማስረጃ ተቀባይነት እንደሌለው አረጋግጧል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(5) መሠረት የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበትን መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀም እና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው በማለት ይደነግጋል፡፡ የክልሉ የገጠር መሬት አካባቢ ጥበቃ ቢሮ በዚህ ጉዳይ ላይ ለአጣሪ ጉባዔው ከላከው ማስረጃ መረዳት እንደሚቻለው በይዞታው ላይ በተሰጠው ሁለት የይዞታ ማረጋገጫ ለተጠሪዎች በሕጉ መሠረት ያልተሰጠ እና ተፍቆ የተሞላ መሆኑን ስለሚያመለክት እንዲሁም ይዞታው በመሬት ልኬት ወቅት ለአካባቢው ህብረተሰብ በጋራ ለግጦሽ የሚውል መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

አመልካቾች ከፊል አርብቶ አደሮች በመሆናቸውና ክርክር ያስነሳው ይዞታ የወል የግጦሽ መሬት መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቶች ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መልኩ የአመልካቾችን ሕገ መንግሥታዊ መብትን በሚጥስ መልኩ ይዞታው የተጠሪዎች የግል ይዞታ ነው በማለት መወሰናቸው አመልካቾች ከጋራ የግጦሽ መሬት ይዞታቸው የሚያፈናቅልና ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(5) ጋር የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 131/07

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካቾች፡-** እነ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ተስፋጽዮን (2 ሰዎች)

**ተጠሪ፡-** የቦሌ ክ/ከ/ማ አስተዳደር

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

አመልካቾችና ተጠሪ ክርክር ውስጥ ሊገቡ የቻሉት 1ኛ አመልካች ባለቤታቸው ከሆኑት 2ኛ አመልካች ጋር ጋብቻ መስርተው በጋራ ካፈሯቸው ንብረቶች ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 17 ቀበሌ 19 የቤት ቁ.309 መኖሪያ ቤት፣ ሞዴል 190 የሰሌዳ ቁ.2-32548 ኢ.አ የሆነ ቶዮታ እና የሰሌዳ ቁ.2-35568 ኢ.አ የሆኑ መኪናዎችን 1ኛ አመልካች በባለቤትነት በመጠቀምና በማስተዳደር ላይ እያሉ ሌላ ሰው በመወከል ለህክምና ጉዳይ ከኢትዮጵያ ሲወጡ 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች ከሁለቱም አመልካቾች እና ከተወካያቸው ፈቃድ ውጭ ንብረቶችን ስለወሰዱ እንዲመልሱ ወይም ሸጠው ከሆነም ለመሸጥ የሚያስችል ስልጣን ስለሌላቸው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ወይም ለመሸጥ ህጋዊ

ምክንያት አላቸው ከተባለ ለ1ኛ አመልካች የመሸጥ መብቱ እንዲጠበቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው ክስ ስላቀረቡ ነው፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ንብረቶቹ ኤርትራዊ ዜግነት ባለው 2ኛ አመልካች አቶ ባህታ ትርፌ ስም የተመዘገበ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት መብት እንደሌላቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ390 ስለተጠቀሰ፣ በ1991 ዓ.ም ኤርትራዊያን ያላቸውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለኢትዮጵያውያን እንዲሸጡ ሲነገር ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ለ3ኛ ተጠሪ በጨረታ አሸናፊነት ተሸጦ ገንዘቡ በዝግ የባንክ ሂሳብ በ2ኛ አመልካች ስም በማስቀመጥ ስመ ንብረቱ የዞረ ስለሆነ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ ስለማይገባ በነፃ ልንሰናበት ይገባል ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት በክርክሩ ሲሳተፉ የሌሎች ተጠሪዎችን ክርክር ከማጠናከር በተጨማሪ አመልካች ንብረቱን በጋብቻ ውስጥ በጋራ ስለማፍራታቸው ማስረጃ ስላላቀረበ ክሱ ውድቅ እንዲደረግላቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊ ስለሆኑ የትዳር አጋራቸው የሆኑት የ2ኛ አመልካችን ኤርትራዊ ዜግነት ብቻ መሠረት ያደረገው ቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊነት የለውም፤ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ንብረቶች በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ የጋራ ስለሆኑ ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ሁኔታ የንብረት ድርሻ ክፍፍል ሊነሳ ስለማይችል ስመ ንብረቱ ቀደም ሲል በነበረበት በ2ኛ አመልካች ስም ተመዝግበው 1ኛ አመልካች እንዲረከቡ ሲል ወስኗል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአንድነት እና 3ኛ ተጠሪ ለብቻ ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ አጣምሮ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 3ኛ በቤቱ ላይ የባለሀብትነት መብት ያገኙት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1185 ሲሆን፤ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሽያጩን የፈፀሙት 2ኛ አመልካች አቶ ባህታ ትርፌ የውጭ አገር ዜጋ (ኤርትራዊ) በመሆናቸው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት መሆን ስለማይችሉ እና በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከኢትዮጵያ ውጭ በመሆናቸው ሕጉን ለማስፈፀም የተደረገ ሽያጭ ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ3ኛ ተጠሪ ተመዘገበው ስመ ንብረት ተሰርዞ ቤቱ በ2ኛ አመልካች እንዲመዘገብ ማዘዙ የፍ/ብ/ህ/ቁ.390 እና 391 በቀጥታ የሚቃረን ስለሆነ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

የ1ኛ አመልካች የሰበር ቅሬታን የመረመረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ውሳኔን አጽንቷል፡፡ አናሳው ድምጽ ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ የ1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊ ዜግነት መሰረታዊ ጭብጥ በማለፍ የባለቤታቸውን ኤርትራዊ መሆንና በኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዝ እንደማይችሉ ከያዙም በ6 ወር ውስጥ ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሰው የማስተላለፍ ግዴታ በፍ/ብ/ህ/ቁ.391 ተደንግጓል ሲል ወስኗል፡፡ ዳኝነት ጠይቀው ያቀረቡት 1ኛ አመልካች ሲሆኑ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ሃብት በመሆኑ የ1ኛ አመልካች የዜግነት ሁኔታና መብት በማለፍ የባለቤታቸውን ኤርትራዊ መሆን ብቻ በመመዘን የሰጠው ውሳኔ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት የጉዳዩ መሰረታዊ ጭብጥ አድርጎ ውሳኔ የሰጠበትን ነጥብ በመሸሽና በጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የሕግ ድንጋጌ በማጣቀስ የተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ሌላው በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 33(1እና 2) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከፍቃዱ ውጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱ ሊነፈግ እንደማይችል፣ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ኢትዮጵያዊ ዜግነት በሕግ በሚያገኘው መብት፣ ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት እንዳለው የተደነገገውን በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1 እና 2) የንብረት ባለቤትነት የመሆን መብት በሚጋፋ አኳኋን ባለቤታቸው በዜግነት ኤርትራዊ ስለሆኑ ብቻ ያለፍቃዳቸው የጋራ ንብረቱ መሸጡ ተገቢና ሕጋዊ አይደለም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ከአብላጫው መለየታቸውን ገልጸዋል፡፡

አመልካች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተወስኖ፣ በሰበር ሰሚው ችሎት አብላጫ ድምጽ የጸደቀው ውሳኔ ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እና በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1 እና 2) ስለንብረት መብት የተደነገገውን ስለሚቃረን የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥልኝ በማለት በዝርዝር ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን በየደረጃው የተላለፉትን የፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንዲሁም ለፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረት ከሆኑ ሰነዶች ውስጥ 1ኛ አመልካች ሐምሌ 17 ቀን 1990 ዓ.ም ወ/ሮ ሮዛ ካርሎ ለተባሉ ግለሰብ የአስተዳደራዊና ልዩ የውክልና ስልጣን መስጠታቸውን ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በቁ. አመ/ዞ3/934/249/93 በቀን 01/06/93 ዓ.ም አቶ ግዛው በረዲ ለተባሉ ግለሰብ ከ2ኛ አመልካች ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ስላልተሰጠዎት በዞኑ ለተቋቋመው ኮሚቴ ንብረቶችን መሸጥ እንዲቻል ቤቱን እና መኪኖቹን እንዲያስረክቡ በመጠየቅ በቀን 02/06/93 ዓ.ም የቤት ርክክብ ያደረገበትን ሰነድ ተመልክቷል፡፡

3ኛ ተጠሪ የሽያጩን ገንዘብ ለአዲስ አበባ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮ ገቢ ደረሰኝ ቁ.901651 በቀን 14/0693 ዓ.ም ቤቱን ያሸነፉትን የሽያጭ ዋጋ ማስገባታቸውን እና በሌላ በኩል በ1ኛና በ3ኛ ተጠሪ መካከል በክርክሩ የተገለፀውን ቤት በቀን 21/11/92 ዓ.ም በተከፈተ ጨረታ አሸናፊ በመሆናቸው ከቀን 24/11/92 ዓ.ም እስከ 24/12/92 ዓ.ም ያሸነፉበትን ገንዘብ ገቢ ሲያደርጉ የቤትና የሰነዶች ርክክብ እንዲደረግ፣ ክፍያው በዚህ ውስጥ ካልተፈፀመ ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ ገቢ በማድረግ ውሉ ቀሪ ተደርጎ ለሌላ ወገን እንደሚተላለፍ የተስማሙበት የቤት ሽያጭ ውል እንዲቀርብ ተደርጎ መመልከት ተችሏል፡፡

ጉዳዩ በጉባኤው ሲታይ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ኤርትራዊ ዜግነት ያላቸው ሰዎች ለአገር ደህንነት ሲባል ከኢትዮጵያ እንዲወጡ በመንግሥት ሲወሰን፤ የንብረታቸውን አስተዳደር በተመለከተ ሕጎች ወጥተው በኢ.ፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን በኩል እንዲፈፀም የተደረገበት አግባብ እንዳለ በማስታወስ ከተቋማቱ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከአገር እንዲወጡ ተደርገው የነበሩ ኤርትራዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው ንብረት ማግኘትና ማልማት እንዲችሉ ለማድረግ ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣውን መመሪያ ለዚህ ማስፈፀሚያ ነሐሴ 01 ቀን 2001 ዓ.ም የወጣውን መመሪያ በማስቀረብ መመልከት እንደሚያስፈልግ እነዚህ ሰነዶች በጉባኤው ጽሕፈት ቤት በኩል እንዲሰባሰቡ ተደርጎ ሰነዶቹ በማስቀረብ ለመመልከት ተችሏል፡፡

መመሪያዎቹ በ1990 ዓ.ም የኤርትራ ወረራ ተከትሎ ለኢትዮጵያ ደህንነት ከአገር የወጡ ኤርትራዊያንን ንብረት እስከማስተዳደርና እንዲሸጥ እስከመወሰን የወጣ ሳይሆን በተለያየ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ሰላማዊ ኤርትራዊያን ንብረታቸው የሚመለከት አግባብ የሚወስን ነው፡፡

ስለዚህ መመሪያው ከተያዘው ጉዳይ ጋር ሲታይ እንደ 1ኛ አመልካች አንዱ ተጋቢ ኢትዮጵያዊ ሌላኛው ተጋቢ እንደ 2ኛ አመልካች ኤርትራዊ ዜግነት ይዘው በጋብቻ በመጣመር በጋራ ባለቤትነት ስለሚያስተዳድሩት ንብረት የሚደነግግ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የኤርትራዊያን ድርሻ በሆነ ንብረት ላይ ስለሚኖረው የንብረት ማስመለስ የሚመለከት ነው፡፡

በተጨማሪም ንብረቶች በተጠሪዎች ውሳኔ እንዲሸጡ እና እንዲተዳደሩ የሚቻልበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሳይሆን በመንግሥት አስተዳደር ስር የሚገኙ ንብረቶች ባለቤት ለሆኑ ኤርትራዊያን እንዴት ባለ ሁኔታ እየተረጋገጠ እንደሚመለስ የሚወስን ከመሆኑ ባሻገር ማስፈፀሚያ መመሪያው አንቀጽ 6(2) ላይ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ባሉ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ወይም በዕዳ ምክንያት በተያዙ ወይም በተሸጡ ወይም አከራካሪ ይዞት ኖሯቸው ለፍርድ ቤት መቅረብ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ቅሬታ ማቅረብ አይቻልም በሚል ስለደነገገ የግራ ቀኙ ጉዳይ ከሚያዝያ 09 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሃምሌ 08 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ከላይ የሰፈሩት ክርክሮች እና ውሳኔዎች እየተሰጡ በመቆየታቸው በመመሪያው መሠረት ሊስተናገዱ እንደማይችል የሚደነግግ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ክርክሩን በተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የአመልካች ጋብቻ ከሚያዝያ 21 ቀን 1968 ዓ.ም ጀምሮ አሁን ድረስ ፀንቶ እንደሚገኝ፣ ንብረቱ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ እና በጋራ ባለቤትነት ሲተዳደር እንደነበር እንዲሁም በደኅንነት፣ ኤሚግሬሽንና ስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን የኢሚግሬሽን የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ በቁ.ኢ.ሚ/1492/362 በቀን 24/11/95 ዓ.ም የፓስፓርት እና የቪዛ ቁጥር በመጥቀስ ለፍርድ ቤት በሰጠው ምላሽ 1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

እነዚህ ፍሬ ነገሮችም ጋብቻው የተመሰረተው እና የጋራ ንብረቱ የተፈራው ኤርትራ እንደ ሉዓላዊ አገር ከኢትዮጵያ ከመገንጠሏ በፊት እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በዚህም

አመልካቾች ጋብቻቸውን ሲመሰርቱ በሁለት ኢትዮጵያዊያን መካከል የተመሰረተ እና ንብረቱም በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊያን ጥረት የተፈራ ሲሆን ይህም ያለውን ሕግ መሠረት ያደረገ እንጂ በቸልተኝነት ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተገለፀውን የፍ/ብ/ህ/ቁ 390 እና 391 በመተላለፍ አይደለም፡፡ ሆኖም የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁኔታ ባስከተለው ለውጥ ኢትዮጵያ እና ኤርትራ ራሳቸውን የቻሉ ሁለት አገር ሲሆኑ ዜጎችም በዚህ ሳይገደቡ በአመልካቾች መካከል የተፈፀመው ጋብቻ ፀንቶ ያለ እና ከላይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈሩና የሚገኙ መሆናቸው በፍርድ ቤቶች ክርክር የተረጋገጡ እውነታዎች ናቸው፡፡

ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠሏን ተከትሎ 2ኛ አመልካች ኤርትራዊ ዜጋ በመሆናቸው ወደ ኤርትራ ቢመለሱም ባለቤታቸው የንብረቶቹ የጋራ ባለቤትና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው 1ኛ አመልካች በባለቤትነት ሲያስተዳድሩና ሲጠቀሙ ተጠሪዎች የ2ኛ አመልካችን ኤርትራዊ ዜግነት ብቻ መነሻ በማድረግ የጋራ ንብረታቸውን በቀን 24/11/92 ዓ.ም ገዢ እና ሻጪ በመሆን የፈፀሙት የሽያጭ ውል ሕጋዊነት እንደሌለው ከቀን 09/08/93 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ፍርድ ቤት በማምራት የሚሞግቱ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ ዳኝነት ጠይቀው ክስ ያቀረቡት 1ኛ አመልካች በመሆናቸው የእርሳቸውን የዜግነት እና የንብረት መብት በማረጋገጥ ረገድ በዝምታ መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

ፍርድ ቤቱ በክርክሩ የ1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊ ዜግነት፣ ከ2ኛ አመልካች ጋር በ1968 ጀምሮ ፀንቶ የሚገኝ ጋብቻ መኖሩን እና ንብረቶች በጋራ የተፈሩ መሆናቸውን በክርክር ማረጋገጡ ያቀረቡትን ዳኝነት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እንደሚያስችል ታስቦ ሲሆን፣ በውሳኔው ግን ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ምላሽ በመስጠት ፋንታ የትዳር አጋራቸው የሆኑት 2ኛ አመልካች ላይ የተቀመጠውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት የመሆን መብት ያላቸውን የ1ኛ አመልካች መብትና ጥቅም መዘንጋቱን የሚያሳይ ውሳኔ ነው፡፡

1ኛ አመልካች በጊዜው ከኢትዮጵያ ውጭ መሆናቸውን በመጥቀስ የሽያጩን ሕጋዊነት ለማሳየት የተሰጠው ምክንያትም ሲታይ፣ እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 በመዘዋወር ነፃነት መብት መሠረት በፈለጉት ጊዜ ከአገር የመውጣት ነፃነት እና ወደ አገራቸው የመመለስ መብት መሠረት እንዳላቸው በግልጽ የሰፈረውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሕገ መንግሥታዊ መብት

መሠረት ከአገራቸው ለህክምና ወይም ላመናቸውም ሰላማዊ ፍላጎታቸው ስለንብረታቸው አስተዳደር ለተያዘው ጉዳይ ውክልና በመተው ከአገር የወጡ ሲሆን፤ ሳይወክሉ ከአገር ቢወጡም እንኳን የንብረቱ ባለቤቶች በኢትዮጵያ ውስጥ አለመገኘት ለንብረታቸው መሸጥ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ የሚችልበት በቂ ምክንያት የለም፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በሰጠው ውሳኔ 3ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1185 በተደነገገው መሠረት በተገኘ የባለሀብትነት መብት ቤቱን በስማቸው አስመዝግበው እንደሚገኝ ገልጿል፡፡ ነገር ግን የተጠቀሰው ድንጋጌ የማይንቀሳቀስ ንብረቶች ባላሃብትነት (ባለርስትነት) በውል ወይም በኑዛዜ ለማስተላለፍ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ ነው የሚል ነው፡፡

በሕጋዊ ተግባሮች በሆነ ሁኔታ በንብረት ባለሃብቶችም ሆነ በወኪሎቻቸው የሚደረግ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ ተግባር በማስመዝገብ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ እንጂ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት ወይም የውክልና ስልጣን ሳይኖራቸው ከ3ኛ ተጠሪ ጋር የፈፀሙትን ተግባር ስላስመዘገቡ ብቻ የተደረገውን ሽያጭ ዋጋ የሚያሰጥ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሽያጩ በመሠረቱ ከባለቤቶቹ ፈቃድ ወይም የውክልና ስልጣን ሳይኖር የሌላ ሕጋዊ ንብረትን በማስተላለፍ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገቡ ብቻ በሕገ ወጥ መንገድ ባለንብረት ለሆነ ሰዎች የሕጋዊነት ሽፋን የሚሰጥ መሆን የለበትም፡፡

ከላይ የቀረበው እንደተጠበቀ ሆኖ ለፍርድ ቤቶች ቀርበው ለውሳኔያቸው መሠረት ከሆኑት ሰነዶች ውስጥ ቤቱ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይዞታ ከመግባቱ በፊት ለ3ኛ ተጠሪ ስለመሸጡ እና የሽያጭ ዋጋውም መከፈል ከነበረበት ጊዜ እጅግ በዘገየ ሁኔታ ስለመከፈሉ የሚያስረዱ በመሆናቸው የሽያጩን ሕጋዊነትም ሆነ በእውነት ቤቱን አግባብ ባለው መንገድ የመሸጥ ሁኔታ የሚያጠራጥሩ በመሆናቸው በዚህ ረገድም ከላይ የቀረበውን ዝርዝር ሕገ መንግሥታዊ የመብት ጥሰት የመፈፀሙን ጉዳይ የሚያጠናክር ነው፡፡

ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የዜግነት መብት ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣምና የተሟላ አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ የ1922 የኢትዮጵያን የዜግነት ሕግ (እንደተሻሻለ) የሻረው የኢትዮጵያ የዜግነት አዋጅ ቁ.378/1996 አንቀጽ 21 የኢትዮጵያ ዜግነት ማጣት በዚያ

ሰው የትዳር ጓደኛና ልጆች ዜግነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት አይኖርም በሚል በግልጽ ደንግጎ የሚገኝ ሆኖ እያለ በ1ኛ አመልካች ላይ የተላለፈው ውሳኔ ከዚህ በሚቃረን ሁኔታ መወሰኑ የ1ኛ አመልካችን የዜግነት እና የንብረት ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ ነው፡፡

በተጨማሪም ሌሎች የክርክር ንብረቶች የሆኑ የማይንቀሳቀሱ ነገር ግን ልዩ ተንቀሳቃሽ ተብለው በሕግ የሚታወቁ ንብረቶች ውስጥ ሁለት መኪናዎች የሚገኙበት ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ምክንያት በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች መያዛቸውን በመቀበል 1ኛ አመልካች እንዲረከቡ ቢወስንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ምክንያቱን ሳይሰጥ በተመሳሳይ የማይንሳቀስ ንብረትን በተመለከተ በውጭ አገር ዜጎች ላይ የተጣለውን ከላይ የተመለከተውን ዓይነት ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የተቀመጠ ገደብ ሳይኖር የሰጠው ውሳኔ ከተጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ባሻገር ፍርድ ቤቱ ለውሳኔው መሠረት ያደረገውን የፍትሐ ብሔር ሕግ የሚቃረን ነው፡፡

ምክንያቱም ለኢትዮጵያዊ ዜጋም ሆነ ለሌላ አገር ዜጋ እንደ መኪና ዓይነት ተንቀሳቃሽ ንብረት ባለቤትነት መብት ላይ የተቀመጠ ገደብ በሌለበት ሁኔታ እንኳን ምላሽ አለመስጠቱ በግልጽ የ1ኛ አመልካች በቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጥሰዋል በሚል የተመለከተውን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ያለ ምክንያት ጭምር መጣሳቸውን ያረጋግጣል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የ1ኛ አመልካችን መብትና ጥቅም አጣጥሞ ለመሄድ ያስችል ዘንድ በውሳኔው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 32፣ 33 እና 40 ላይ የመዘዋወር፣ የዜግነት እና የንብረት መብቶች ድንጋጌ አጣምሮ በማየት ማስታረቅ ይገባው ነበር፡፡ በተለይ 1ኛ አመልካች ኢትዮጵያዊ መሆናቸው፣ ከ2ኛ አመልካች ጋር ጋብቻ መኖሩንና ንብረቶቹ በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ የጋራ ሀብቶች መሆናቸውን በማጣራት የተገኘው ውጤት ውሳኔ ሲሰጥ መዘንጋቱ ለመብት መጣስ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች አንፃር ውሳኔው ማንኛውም ኢትዮጵያዊት በፈቃዷ ውጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነቷን ልትገፈፍ አትችልም፡፡ ኢትዮጵያዊት ዜጋ ከሌላ

አገር ዜጋ ጋር የምትፈጽመው ጋብቻ ኢትዮጵያዊ ዜግነቷን አያስቀርም፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊት ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት በሕግ የሚያስገኘውን መብት፣ ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አላት የሚል ሰፊ ይዘት አለው፡፡

ይህ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ ኢትዮጵያዊት የሆነች ዜጋ ዜግነት ሳይወስናት የፈለገችውን ሰው የማግባት የጋብቻ ነፃነት የሚያረጋግጥ ሲሆን ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ውሳኔ ጋር ሲታይ ዜግነት በተግባርና በሁኔታ የሚገለፀው አንድ ሰው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር በአንድ መብት ላይ እኩል ሲታይ እንጂ በመሰረተው ጋብቻ ምክንያት ከውጭ ዜጋ ጋር ባለው የጋብቻ ግንኙነት በመመዘን አይደለም፡፡

ውሳኔው ግን ኤርትራዊ ዜግነት ካላቸው 2ኛ አመልካች ጋር 1ኛዋ አመልካች ጋብቻ በመፈፀማቸው በኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት የማፍራትና ባለቤት መሆን ለእነዚህ ንብረቶች አግባብነት ያለው ጥበቃ የማግኘት፣ በሕግ የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል የተወሰነ ገደብ በሌለበት፤ ተጠሪዎች ንብረታቸውን በመያዝ እና በመጠቀም እንዲሁም በሽያጭ በማስተላለፍ ከፍቃዳቸው ውጭ ንብረታቸው የተሸጠበት ውል ዋጋ በመስጠት ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ ያለውን የንብረት ባለቤትነትና የዜግነት መብታቸውን የከለከለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ሲጠቃለል ከፍ ብለን ባየናቸው ምክንያቶች በተጠሪዎች መካከል የተደረገው ቤት ሽያጭ ውል በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የይዞታ ውስጥ ሁለት መኪናዎች ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸውን የ1ኛ አመልካች የዜግነት እና የንብረት መብትና ጥቅም የያዘ ስለሆነ ፈቃዳቸውን በስምምነት ሳያገኝ የመንግሥት አካል ትዕዛዝ መስጠት ስለማይችል ከተሰጠም ሕገ መንግሥታዊ ስላልሆነ ቤቱ ላይ የተደረገው የሽያጭ ውልና የመኪናዎችን መያዝ ተግባሮች በፍርድ ቤት ውሳኔ ተቀባይነት ያገኘበት ሁኔታ ከተጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር ስለሚቃረን ተፈፃሚነት እንዳይኖረው በማድረግ ለንብረቱ ባለቤት 1ኛ አመልካች ንብረቶችን በመመለስ የንብረቶቹን ስመንብረት በስማቸው በማስመዝገብ የተጣሰውን ሕገ መንግሥታዊ መብት ማረም ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.08/08 የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** እማሆይ ባንቺ አምላክ ደርሶልኝ፣ ወኪል የአማራ ብ/ክ/መንግሥት የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ

**ተጠሪ፡-** አቶ አበባው ሞላ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የአቤቱታው መነሻ ጉዳይ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 (3 እና 4) የተደነገገውን «መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው፤ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው» ተብሎ የተደነገገውን ሕገ መንግሥታዊ መብትን የሚጥስ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሆኖ በአመልካች አቤቱታ ላይ በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት የፌዴሬሽን ምክር

ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የውሳኔ ሐሳብ በማቅረቡ ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 29 ቀን 2004 ዓ.ም በወኪላቸው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ አማካኝነት ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ተጠሪው በአማራ ክልል በደቡብ ጎንደር ዞን በምሥራቅ እስቴ ወረዳ የሚገኝ የመሬት ይዞታዬን በመያዝ 900 ብር(ዘጠኝ መቶ ብር) ካበደረኝ በኋላ የተበደርኩትን ብር መልሼ ይዞታዬን እንዲመልስልኝ ብጠይቀው እምቢተኛ በመሆኑ በሚል ሰኔ 10 ቀን 1996 ዓ.ም በአመልካች የቀረበለትን ክስ በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጥር 23 ቀን 1997 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አመልካች ልጆቼን ለመፈለግ ስል ከተጠሪ ብር 900 ተብድሬ በመያዣነት ቤቱንና አትክልቱን አስይዤ ሄድኩኝ ትበል እንጂ ቤቱንና አትክልቱን ለመሸጧ በቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ አረጋግጧል፡፡

ከዚያም በኋላ ሐምሌ 18 ቀን 1990 ዓ.ም አመልካች ብሩን ከጥቅምት 30 ቀን እስከ ጥር 30 ቀን 1990 ዓ.ም ድረስ ልትመልስ፣ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ሆነው በሽማግሌዎች እርቅ ያደረጉና አመልካች ገንዘብ ባትመልስ ግን ተጠሪ ቤቱንና አትክልቱን ሊረከብ ተዋውለው ከዚያም አመልካች እንደ እርቁ ባለመፈፀሟ የተነሳ የካቲት 5 ቀን 1991 ዓ.ም የሽማግሌ ዳኞች እንደ እርቁ እንዲፈፀም ውሳኔ መስጠታቸው ታውቋል፡፡

ክሴን ለደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀርብም ፍርድ ቤቱ መሬትሽን እና አትክልቱን ከሸጥሽ በኋላ እንደገና በመያዣነት ነው የሰጠሁት ብለሽ ከተጠሪ ጋር ሽምግልና ይዘሽ ገንዘቡን የምትመልሽበት ጊዜ ቢሰጥሽም መመለስ ስላልቻልሽ በሽማግሌዎች ላይ በፈፀምሽው ስምምነት መሠረት መሬቱ አይገባሽም በሚል ጥር 23 ቀን 1997 ዓ.ም ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡

ውሳኔው የሕገ መንግሥት ጥሰት ያለው በመሆኑ ክሴን በወኪሌ የምሥራቅ እስቴ ወረዳ ፍትህ ጽሕፈት ቤት የፍትህ ብሔር ዐቃቤ ሕግ አማካኝነት እንደ አዲስ ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ለምሥራቅ እስቴ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀርብም ጉዳዩ ቀደም ብሎ በፍርድ ያለቀ ነው በሚል ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡

በውሳኔው ላይ ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ባቀርብም በተመሳሳይ በብይን የተዘጋ በመሆኑ በውሳኔው ላይ የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቤ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በሚል በመወሰኑ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 (3 እና 4) ተጥሷል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች ተጥሷል ሲሉ የጠቀሷቸው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች አንቀጽ 40(3እና4) ናቸው፡፡ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) ‹‹የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡›› በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) ‹‹የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል›› በሚል ተደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በገጠማቸው ጊዜያዊ ችግር ምክንያት ልጆቻቸውን ለመፈለግ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄዱ በይዞታቸው ላይ ያለውን ቤት እና አትክልቱን ለተጠሪ አስይዘው ብር 900(ዘጠኝ መቶ ብር) ተብድረው የነበረ ሲሆን ከሄዱበት ሲመለሱ ይዞታቸውን ተጠሪ እንዲመልስላቸው ጠይቀው ተጠሪ እምቢተኛ በመሆኑ ክሳቸውን ለፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካች በይዞታቸው ላይ ያለውን ቤት እና አትክልት ሸጠው ስለመሄዳቸው የቀረበው የሰነድ ማስረጃ እንደሚያስረዳ በመጥቀስ በሌላ በኩል አመልካች አከራካሪውን ይዞታ በተመለከተ ከተጠሪ ጋር በሽማግሌዎች ፊት ተደራድረው የተበደሩትን ገንዘብ የሚመልሱበት ጊዜ ተቆርጦ የተሰጣቸው ሲሆን በተሰጣቸው ጊዜ ገንዘቡን

የማይመልሱ ከሆነ ይዞታውን ሊያስረክቡ ተስማምተዋል በማለት ስምምነቱ እንዲፈፀም ወስኗል፡፡

በመሆኑም ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ በኩል አከራካሪው ይዞታ መሸጡን ያረጋገጠ ሲሆን በሌላ በኩል በይዞታው ላይ የተደረገውን የመያዣ ውል ስምምነት አጽድቆታል፡፡ ይህን የፍርድ ቤቱን ውሣኔ ይዞታው ከተወሰነለት አጠቃቀም፣ ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሰው የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች አንፃር መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

አመልካች ቅሬታቸውን ለጉባኤው አያይዘው ሲያቀርቡ ኅዳር 3 ቀን 2001 ዓ.ም የታደሰ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የይዞታው አጠቃቀም ለእርሻ የተወሰነ መሆኑን ያሰረዳል፡፡ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁ.133/98 በአንቀጽ 19 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የገጠር መሬት ይዞታን የመጠቀም መብት በዋስትና ማስያዝ የተፈቀደው የገጠር መሬት ይዞታን ለማልማት በሊዝ የያዘን ሰው የሚመለከት ነው፡፡

በመሆኑም በወረዳው አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንደተጠቀሰው አከራካሪው ይዞታ ለእርሻ የሚውል (የተመደበ) ሲሆን በዚህ ዓይነት ይዞታ ላይ አትክልት እና ቤት አለው በሚል ምክንያት የሚደረግ የሽያጭም ሆነ የመያዣ ውል መሬቱን ከመሸጥ ወይም ከማስያዝ የተለየ ውጤት አይኖረውም፡፡

ከላይ በተጠቀሰው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ድንጋጌ መሠረት ደግሞ በአከራካሪው የመሬት ይዞታ ላይ ያለን የመጠቀም መብት በመያዣነት ማስያዝ ለአመልካች የሚፈቀድ አይደለም፡፡

ይህ የአዋጁ ድንጋጌ መሬት በመያዣ ሰበብ እንዳይሸጥ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ፣ አርሶ አደሩ ከይዞታው እንዳይፈናቀል የሚከለክል እና ሕገ

መንግሥቱ በአንቀጽ 40(3) ላይ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ያስቀመጠውን ዓላማ የሚያሳካ ነው፡፡ በመሆኑም አከራካሪውን መሬት መሸጥ በግልጽ የተቀመጠውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚፃረር ሲሆን በመያዣ ውል መስጠትም ቢሆን በአዋጁ ያልተፈቀደ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚደረግ ሽያጭ በመሆኑ በውጤቱ የሕገ መንግሥት ጥሰት ያለው ነው፡፡

በመሆኑም ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር ስምምነት በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በሚል የተደነገገውን ሕገ መንግሥታዊ ክልከላ የጣሰ እና አመልካችን ከይዞታቸው ያፈናቀለ በመሆኑ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3እና4) የጣሰ ነው፡፡

በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው በዚህ ጉዳይ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኗ አመልካች ከሳሽነት እና በአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽነት መነሻነት ለቀረበለት የሁከት ይወገድልኝ (የመሬት ይዞታዬን ይለቀቅልኝ) እና የመሬት አላባ ይከፈለኝ ክስ ፍርድ ቤቱ በተከሳሹ በኩል የቀረበለትን በአመልካችና ተጠሪ መካከል በቀን 04/06/89 ዓ.ም ተደርጓል ተብሎ የቀረበውን የሽያጭ ውልና ሐምሌ 18 ቀን 1990 ዓ.ም ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበውን የዕርቅ ስምምነት ተቀብሎ በማጽደቅ ከሳሽ (የአሁኗ አመልካች) ቤቱንና የአትክልቱን ቦታ አስይዤ ብር 900 (ዘጠኝ መቶ ብር) ገንዘብ ተበድሬ ሄድኩኝ ትበል እንጂ ቤቱንና አትክልቱን ለመሸጧ የቀረበው የጽሑፍ ማስረጃ አረጋግጧል፤ ከዚያም በኋላ በመያዣነት ነው የሰጠሁት በማለት በእርቅ እንዲፈፀም ድርድር ገብታ በሽማግሌዎች እርቅ ተፈጽሞ በዕርቁ መሠረትም በተወሰነው ጊዜ ገንዘቡን ለተከሳሽ (የአሁኑ ተጠሪ)

መልሳ ቤቱንና አትክልቱን መረከብ ስላልቻለች በእርቁ መሠረት እንዲፈፀም በማለት የሰጠው ውሳኔ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3እና4) ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

በመሆኑም በደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3እና4) ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ 08/07**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም**

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐሳይ ዶዬ

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ትንሳኤ ኩታሌ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የአቤቱታው መነሻ አመልካች ጥቅምት 27 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያቀረቡት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲሆን አቤቱታቸው ባለቤቴ ከሞቱ በኋላ ለተጠሪዎች በአካባቢ ባህል መሠረት በቃል ስምምነት በጋራ አርሰን ምርቱን በጋራ ለመጠቀም ተዋውለን ድርሻዬን በማስቀረታቸው የእርሻ መሬት ይዞታዬ እንዲለቁልኝ በፍርድ ቤቶች ክስ ብመሰርትም ለተጠሪዎች የተወሰነ በመሆኑና በውሳኔውም ከይዞታዬ ያለመነቀል ሕገ መንግሥታዊ መብቴ ስለተጣሰ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጠኝ የሚል ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡፡

በጉዳዩ ላይ በገዜ ጎፋ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች ልጆች በአምስት ሰዎች ላይ የመሰረቱት ክስ ይዞታቸውን ከተጠሪዎች ጋር በጋራ ለመጠቀም ተስማምተው ከያዙ በኋላ አሁን አንለቅም በማለታቸው ለፍርድ ቤቱ ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በተናጠል ባቀረቡት መልስም ከፊሉን ይዞታ በግዥና ሌላውን በኪራይ ይዘውት ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበት እንደቆዩ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመመዘን የሰጠው ውሳኔ ተከሳሾች ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙና ግብር ሲከፍሉበት የቆዩ ስለሆነና የአመልካች ልጆችም በይዞታው ሲጠቀሙ ያልቆዩ በመሆኑ ይዞታው የተከሳሾች ነው ሲል ወስኗል፡፡

ጉባዔውም በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ ያጠራ ሲሆን በዚህም መሠረት ክርክር ያስነሳው የእርሻ መሬት ከስምምነቱ በፊት የወ/ሮ ሐሳይ ዶዮ እና ባለቤታቸው ይዞታ መሆኑ ፍርድ ቤት የቀረቡ ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡

በፍርድ ቤት በተደረገ የቃል ክርክርም ከፊሎቹ ተጠሪዎች መሬቱን ከአመልካች ከብዙ ዓመታት በፊት በኪራይ እና አትክልት ያለበትን ቦታ ደግሞ በግዥ መረከባቸውን ሲገልፁ የተቀሩት ደግሞ ከሌላ ሦስተኛ ወገን በኪራይ መያዛቸውን ገልፀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የመሬት ሽያጭ ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር መሆኑን ገልፆ ይህንን ሕገ ወጥ ተግባር የፈፀሙት ሁለቱም ወገኖች ስለሆኑና ተጠሪዎች ከ10 ዓመት በላይ ግብር እየከፈሉ የቆዩትን መንጠቅ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ስለሚያስከትል በፍ/ሕ/ቁ.1845 መሠረት በይርጋ የሚታገድ እና በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ.110/1999 አንቀጽ 2(7) መሠረት ወራሾች (የአመልካች ወኪል) መሬቱን እየተጠቀሙ የቆዩ ስላልሆኑ ተጠሪዎች ይዞታቸውን መልቀቅ የለባቸውም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በጥልቀት ስንመረምረው አመልካች ከፊሉን ይዞታ ለተጠሪዎች በሽያጭ ማስተላለፋቸውን የሚያሳይ ማስረጃ በፍርድ ቤት መቅረቡን መረዳት የተቻለ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የደረሰበት መደምደሚያ ሕገ ወጥ ድርጊቱን የፈጸሙት ሁለቱም ወገኖች በመሆናቸውና ተጠሪዎች በይዞታው ለረጅም ጊዜ በመጠቀም ቋሚ አትክልቶች በማፍራታቸው ይዞታውን እንዲለቁ ቢደረግ ከሚያመጣው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አንጻር ተጠሪዎች ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3) መሬት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና የመንግሥት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ መሬት መሸጥና መለወጥ በሕገ መንግሥቱ የተከለከለ ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቱ ይህንን ጭብጥ ትኩረት ሳይሰጥ ማለፉ አግባብ አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(2) እና 13(1) መሠረት ሕገ መንግሥቱን የማስከበር ግዴታ ስለተጣለባቸው የመሬት ሽያጭ ግልጽ ሆኖ ሲታይ ፍርድ ቤቱ በእራሱ ተነሳሽነት ተገቢውን ማጣራት ማድረግና መወሰን ሲገባው ሕገ ወጥ ለሆነ የመሬት ሽያጭ ውል ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ውሳኔ ማሳለፍ ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሕገ መንግሥቱን የሚፃረሩ ሕጎች፣ ደንቦች፣ የሕግ አስፈፃሚ አካላት ውሳኔዎችና ሌሎች ድርጊቶች ከመጀመሪያውም እንዳልተፈፀሙ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በሽያጭ ለተጠሪዎች የተላለፈው መሬት ላይ ያስተላለፈው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ባለመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው ይህ ክርክር የተነሳበት የይዞታ መሬት የአመልካች መሬት መሆኑንና ልጆቻቸውም በቤተሰብ አባልነት የተመዘገቡበት መሆኑን በፍርድ ቤት ተያይዞ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ከማረጋገጡም በላይ ይህ እውነታ በተከሳሾችም አልተካደም፡፡

አራቱ ተከሳሾች በስር ፍርድ ቤት በግልጽ ባቀረቡት መቃወሚያ በቀን 15/6/95 ዓ.ም በተጻፈ ውል ክስ የተመሰረተበትን የይዞታ መሬት እና አትክልት ከአመልካች ወ/ሮ ሐሳይ ዶዮ በገንዘብ የገዙ መሆናቸውን የሚያስረዳውን የጽሁፍ ማስረጃ በማያያዝ አቅርበው እንደተከራከሩ የቀረበው ሰነድ ያስረዳል፡፡

ሌላው ተከሳሽ ደግሞ የአመልካችን መሬት ከማይመለከተው ግለሰብ በ8 ዓመት ኮንትራት ወስደው መያዛቸውን ገልጸው ማስረጃዬ ነው ብለው ያቀረቡት በቀን 6/3/94 ዓ.ም የተጻፈ ሲሆን መሬቱን በብር 225 ላልተወሰነ ጊዜ ሊጠቀሙበት የወሰዱ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህም በተጠሪዎች የታመነ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች መሬቱን ገዝተው ለአመታት የያዙት በመሆኑ ይዘው ይጠቀማሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 (3) መሠረት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የገዜ ጎፋ ወረዳ ፍርድ ቤት የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3) ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ 913/05**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም**

**አመልካች፦** ወ/ሮ አለሚቱ ገብሬ

**ተጠሪ፦** አቶ ጫኔ ደሳለኝ

*የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡*

**ውሳኔ፣**

የዚህ አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የሆነው ግለሰብ የአመልካች ይዞታ የሆነውን የእርሻ መሬት ለሃምሳ ዓመታት በኪራይ የያዝኩት ነው በማለት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያወጣበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የስር ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን ክስ የይርጋ ጊዜን መሠረት በማድረግ ውድቅ በማድረጉ ለአጣሪ ጉባኤው የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት በመቅረቡ ነው።

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በ1989 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረኩት የኪራይ ውል ስምምነት በገጠር የሚገኝ 2 ሄክታር የእርሻ መሬት ይዞታዬን ለ5 ዓመት እንዲጠቀም ነው ያከራየሁት ቢሉም ተጠሪ ግን ከአመልካች ጋር የኪራይ ውሉን የተፈራረምነው ለ5 ዓመት ሳይሆን ለ50 ዓመት ነው በማለት በይዞታው ላይ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቶ ግብር እየከፈለ የሚጠቀምበት በመሆኑ የዚህ ይዞታ ባለመብት መሆኑ ተረጋግጦ እንዲወሰንለት በወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ሲሆን አመልካች በ1989 ዓ.ም በተደረገ የውል ስምምነት 2 ሄክታር የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታቸውን ለተጠሪ ያከራዩት ለ50 ዓመት ሳይሆን ለ5 ዓመት በመሆኑ እና የኪራይ ጊዜውም ያለቀ ስለሆነ መሬቱ ይመለስልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የገጠር መሬት ኪራይ ውል ለ5 ዓመት ሳይሆን ለ50 ዓመት ነው፤ ተጠሪም ከአመልካች በኪራይ ባገኘው የገጠር መሬት ይዞታ ላይም ለ16 ዓመት ግብር በመገበር የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር ወስዶበታል በማለት የአመልካች ክስ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ.1168(1) እና 1845 በይርጋ ይታገዳል በማለት ወስኖ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አያስቀርብም በሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ውሳኔው ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) እና አንቀጽ 35(7) ድንጋጌዎች ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉባኤው በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች እና ተጠሪ ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝና ግብሩም በማን እንደሚገበር በተደረገው ማጣራት መሠረት የከፋ ዞን የጊምቦ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽሕፈት ቤት በቁ.3443/Q-32 በቀን ሰኔ 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ክርክር ከተነሣበት 2 ሄክታር የመሬት ይዞታ ውጭ 6.4 ሄክታር የመሬት ይዞታ ለአመልካች የተሰጣቸውና የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር በስማቸው የተመዘገበ እና ግብርም የሚገብሩት አመልካች መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡

ተጠሪ ደግሞ ክርክር የተነሳበትን 2 ሄክታር ጨምሮ 4 ነጥብ 2 ሄክታር የመሬት ይዞታ ያለው እና በዚህ ይዞታ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቶበት ግብር የሚገብር መሆኑን አረጋግጦ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን 2 ሄክታር ይዞታ ጨምሮ በ4 ነጥብ 2 ሄክታር ላይ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር ሊሰጠው የቻለውም ክርክር የተነሳበት ይዞታ በ1997 ዓ.ም ሲለካ አመልካች ተቃውሞ ባለማንሳታቸው መሆኑን ገልፆአል፡፡

ተጠሪ ከአመልካች ላይ በ1989 ዓ.ም በኪራይ በወሰደው የገጠር መሬት ይዞታ ላይ በስሙ የባለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የወሰደበት መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(3) መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው ተብሎ የተደነገገ ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ዋና ዓላማ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸውን ለማረጋገጥ የተደነገገ መሆኑን ስንመለከት ምንም እንኳ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረገው የ50 ዓመት የእርሻ መሬት የኪራይ ውል የሽያጭ ውል ነው ባይባልም አንድ አርሶ አደር ለ50 ዓመት ያህል መሬቱን ማከራየቱ አርሶ አደሩን ከመሬቱ የሚያፈናቅለው ተግባር ነው፡፡

በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ.110/99 አንቀጽ 8(1) ፊደል /ሀ/ ላይ አርሶ አደር ለአርሶ አደር መሬቱን ሲያከራይ እስከ 5 ዓመት ይሆናል የሚለውን ድንጋጌ ስንመለከት አርሶ አደሮች መሬታቸውን በማከራየት ሰበብ ከመሬታቸው እንዳይፈናቀሉ ጥበቃ ለማድረግ የተደነገገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሲታይ ተጠሪ በ1989 ዓ.ም ከአመልካች ላይ ለ50 ዓመት በኪራይ በወሰደው የገጠር መሬት የእርሻ ይዞታ ላይ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቼበታለሁ በማለቱ አመልካች በኪራይ የሰጡትን የእርሻ መሬት ይዞታ እንዲያጡ የሚያደርጋቸው ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማገኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው ከሚለው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን በመሆኑ በአመልካች የቀረበው አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ የውሳኔ ሐሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በማድርግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ተጠሪ ከአመልካች ላይ ለሃምሳ ዓመታት በኪራይ የእርሻ መሬት ተከራይቻለሁ በማለት የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ከሚደነገገው ውጭ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቼበታለሁ በማለቱ ብቻ ይዞታቸውን እንዲያጡ እና እንዲፈናቀሉ የሚያደርጋቸው ነው፡፡

በመሆኑም የጊንቦ ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ጉዳይ የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው ከሚለው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.016/08**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የሥራ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣**

**ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም፣**

**አመልካች፡- ወ/ሮ ሃና አድማሱ**

**ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሻረግ ከበደ**

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.79679 ሚያዝያ 17 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠውና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.103454፣ በ15/07/2007 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37፣ 25 እና 78 የተመለከተውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ለአጣሪ ጉባኤው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሚያዝያ 26 ቀን 2007 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.79679 ሚያዚያ 17 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው እና እስከ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.103454፣ በ15/07/2007 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9፣ 37፣ 25 እና 78 የተመለከተውን ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ጉዳዩም የፍትሐ ብሔር ፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ የቤት ቁ.423 አካል የሆነው ማዕድ ቤት ተጠሪ ይዘው ስለሚገኙ ይልቀቁልኝ፣ ኪራዩንም ይክፈሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ቤቱን በስጦታ ውል ያገኘውትና ማዕድ ቤቱን አፍርሼ ሁለት ክፍል ዛኒጋባ ቤት የሠራሁ በመሆኑ ቤቱ የራሴ ነው፤ ልለቅ አይገባኝም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ቤት ለአሁን አመልካች እንዲለቁ፤ ማዕድ ቤቱን አስፋፍተው ለመሥራት ያወጡት ወጪ ካለ ዳኝነት ከፍለው የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካችም የፍርድ አፈጻጸም ክስ አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፍርድ አፈጻጸም መምሪያው በውሳኔው መሠረት ለአሁን አመልካች አስረክቧል፡፡ ተጠሪም በፍርድ አፈጻጸም መምሪያው ውሳኔ ላይ ለፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት ቅሬታ በማቅረባቸው የፍርድ አፈጻጸም መምሪያው ያስረከበው ቤትና ንብረት በዋናው ፍርድ ያልተመለከተ ንብረት ስለሆነ ተጠሪ አዲስ የተሰሩትን ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ለአመልካች እንዲያስረክቡ መደረጉ ትክክል አይደለም በማለት ተጠሪ ለአመልካች ማዕድ ቤቱን እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

ፍሬ ሃሳቡ ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ሲሆን አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆንኩትን ንብረት በአፈጻጸም ጊዜ ያጣሁ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 እና 37 መሠረት የእኩልነትና ፍትህ የማግኘት መብቴ ተጥሷል በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡ ከጉዳዩ አመጣጥ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነው የቤት ቁ.423 በውርስ አግኝተዋል፡፡ አመልካች በመሰረቱት ክስ የቤቱ አካል የሆነውን ማዕድ ቤት ተጠሪ በስጦታ ውል አግኝቼዋለሁ በማለት ይዘውት ስለሚገኙ ይልቀቁልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክርክሩን ሰምቶ ተጠሪ በዋናው ክስ ክርክር ቤቱን በስጦታ ስላገኘሁ በቦታው የነበረውን ማዕድ ቤት በማፍረስ አስፋፍቼ አዲስ ዛኒጋባ ቤት ሰርቻለሁ ቢሉም ይህ የስጦታ ውል በፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁ.00691 በፍርድ ስለተሰረዘ ተቀባይነት የለውም በማለት ተጠሪ ያወጡትን ወጪ ከፈለጉ ዳኝነት ከፍለው መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን ገልጾ ክርክር የተነሳበትን ቤት ግን ለአሁኗ አመልካች እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት በዋናው ውሳኔ በመ/ቁ.22011 የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክር ያስነሳውን ቤት በአራቱም አቅጣጫ አዋሳኞቹን በመግለጽ የአሁን ተጠሪ ለአመልካች ይልቀቁ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የዚህ ውሳኔ ክፍልም እስከ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ድረስ ስለፀና አመልካች የፍርድ አፈፃፀም ክስ መስርተዋል፡፡ የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ የቤት ቁ.423 አካል በሆነ የመሬት ይዞታ በፍርዱ በተገለፀው በምሥራቅ መንገድ፤ በምዕራብ የመንግሥት ቤት፣ በደቡብ ወንዝ፣ በሰሜን ቁ.423 የሆነው ዋና ቤት እና መንገድ የሚያዋስኑትን አዲስ የተሰሩ ቤቶችንና ዛፎችን ተጠሪ ለአመልካች እንዲያስረክቡ ወስነው አስፈጽመዋል፡፡

ተጠሪ በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ውሳኔ ላይ ለፌ/መ/ደ/ፍርድ ቤት ቅሬታ በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱም የአፈፃፀም መምሪያው በዋና ውሳኔ ያልተካተተውን ንብረት ከተጠሪ ወስዶ ለአመልካች ማስረከቡ ስህተት ነው በማለት ተጠሪ ማዕድ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡

ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔም ስንመለከት በዋናው ውሳኔ ተጠሪ ማዕድ ቤቱን አፍርሰው የሰሩትን አዲስ ቤት ለአመልካች ለቀው ከፈለጉ ያወጡትን ወጪ ዳኝነት ከፍለው መጠየቅ ይችላሉ ተብሎ የተወሰነውን ፍርድ የሚቃረን ይሆናል፡፡ ተጠሪ ማዕድ ቤቱን ያስረክቡ በማለት የተሰጠውም የአፈፃፀም ውሳኔ ማዕድ ቤቱ ፈርሶ አዲስ ቤት በመሰራቱ ምክንያት በተጨባጭ መሬት ላይ ያለው ሌላ ነገር በመሆኑ ሊፈፀም የማይችል ውሳኔ ያደርገዋል፡፡ በዚህ የአፈፃፀም ውሳኔ በሰ/መ/ቁ.103454 በሀሳብ የተለዩት አንድ ዳኛ እንዲህ በማለት የልዩነት ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል፡፡ "ተጠሪዋ በስረ ነገር ክርክር ጊዜ በተከሳሽነት ቀርበው በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች ተገቢ ነው የሚሉትን ክርክር ሁሉ አቅርበው በይዞታው ላይ አስፋፍቼ ሰርቻለሁ በሚሉት ዛኒጋባ ቤት ላይ ያጡትን መብት ባለዕዳ ሆነው በተከራከሩበት በአፈፃፀም ክርክር እንዲጎናፀፉ ማድረጉ በሕጉ አግባብ የተሰጠውን የሥረ

ነገር ፍርድ ዋጋ አልባ የሚያደርገው በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አላገኘሁትም" ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል እንዲጣራ ለጽሕፈት ቤቱ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ለጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ማኔጅመንት ጽሕፈት ቤት **በደብዳቤ ቁ.አጠጉ** 392/2008 **በቀን** 29/02/08 **ዓ.ም** በተጻፈ ደብዳቤ የተጠየቀ ሲሆን፣ የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት በቁ.ጉ/ክ/ከ/ው/ይ/ሬ/ፕ/ዴስክ 197/2008 በቀን 28/7/2008 ዓ.ም ለጉባኤው በላከው መረጃ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ማዕድ ቤትና ሰርቪስ ቤት 6 ክፍል ተጠሪ የሰሩ መሆኑንና ቤቶቹ ግን የሚገኙት በአመልካቿ 530 ካ.ሜ. የመሬት ይዞታ ውስጥ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

ተጠሪ ማዕድ ቤቱን አፍርሰው አዲስ ቤት ሰርቻለሁ ብለው የተከራከሩት ማዕድ ቤቱን በስጦታ ውል አግኝቻለሁ በሚል ሲሆን ይህ ክርክር በዋናው ፍርድ የስጦታ ውሉ በሌላ መዝገብ ሕገ ወጥ ውል ነው ተብሎ ስለተሰረዘ ክርክሩ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የዋናው ቤት አካል በሆነው ይዞታ ላይ ተጠሪ መብት የላቸውም ከፈለጉ ቤቶችን ለማስፋፋት ያወጡትን ወጪ ዳኝነት ከፍለው መጠየቅ ይችላሉ ተብሎ በፍርድ የተወሰነውንና አመልካች በፍርድ ባለመብት ሆነው በአፈጻጸም የተረከቡትን ቤት እንዲመልሱ መወሰኑ በዋናው ፍርድ የተወሰነውን ውሳኔ ዋጋ አልባ የሚያደርገው ነው፡፡

ስለዚህ አመልካች በፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ንብረት በአፈፃፀም ውሳኔ ማጣታቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ የቀረበው አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የተስማማ ሲሆን የውሳኔ ሃሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲቀርብ በሙሉ ድምጽ ተስማምቷል የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው ክርክር የተነሳበት ቤትና ቤቱ የተሰራበት ቦታ አመልካች ከእናቷ በውርስ ተላልፎላቸው ያገኙት መሆኑን በማስረጃ

የተረጋገጠ ሲሆን ተጠሪ ግን በቤቱ እና በቦታው ላይ መብት እንደሌላቸው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች  በማስረጃ ተጣርቶ ተወስኗል፡፡

ምክር ቤቱም የደረሰበት መደምደሚያ አመልካች በዋናው ክርክር የፍርድ ባለመብት በመሆን እንደ ፍርዱ እንዲፈጸምላቸው ለፍርድ አፈጻጸም መምሪያ አመልክተው እንደ ፍርዱ ከተፈጸመላቸው በኋላ በተጠሪ ቅሬታ አቅራቢነት በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከፍርዱ ውጭ የሰጡት የአፈጻጸም ትዕዛዝና ውሳኔ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በዋናው ፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ንብረት በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ እንዲያጡ ያደረገበት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(1) የተደነገገውንና ዋስትና ያገኘውን የዜጎች የንብረት መብት የሚጥስ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.017/08**

**የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የሥራ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም**

**አመልካች፡- አቶ ሙየዲን ዮኒስ**

**ተጠሪዎች፡- 1አቶ ናዚ አሊይ**

**2. አቶ አሊይ አብዶ**

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች ለተጠሪዎች የሰጠሁት ይዞታ መሬት እንዲለቀቅልኝ በፍርድ ቤት ስጠይቅ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ይዞታውን ማስለቀቅ ሲገባው ተጠሪዎች የሰጡትን መልስ ተመልክቶ ይዞታው ሊመለስልህ አይገባም ብሎ መወሰኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 26 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ ለጉባኤው አቅርበዋል፡፡ በማመልከቻቸውም ለተጠሪዎች የሰጠሁት ይዞታ መሬት እንዲለቀቅልኝ በፍርድ ቤት ስጠይቅ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማስረጃ አጣርቶ ይዞታውን ማስለቀቅ ሲገባው ተጠሪዎች የሰጡትን መልስ ተመልክቶ ይዞታው ሊመለስልህ አይገባም ብሎ መወሰኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች 1ኛ ተጠሪ ከሚስቱ ጋር በመሆን በአላባው እንዲጠቀም የሰጡትን የጫት ተክል የሚገኝበት 6 ሄክታር የገጠር መሬት ይዞታ ለ2ኛ ተጠሪ ሸጧል በማለት በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የመሬት ሽያጭ ውል ፈርሶ ይዞታው እንዲመለስላቸው በፍርድ ቤት ክስ መስርተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ይዞታ አመልካች በአደራ ይዞ እንዲጠቀም የሰጠሁት ሲሆን ኑሮ ሲከብደው ለ2ኛ ተጠሪ በኪራይ መልክ በብር 1000.00 /አንድ ሺ ብር/ የሰጠ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ይዞታውን ለመመለስ ፈቃደኛ አይደለም ብሎ ሲከራከር 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ክርክር የተነሳበትን የመሬት ይዞታ 1ኛ ተጠሪ ከሚስቱ ጋር በመሆን በ1988 ዓ.ም በብር 1400.00 /አንድ ሺ አራት መቶ ብር/ የሸጠላቸው በመሆኑ እና ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ይዞታውን መመለስ አይገባኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው የመሬት ይዞታ የማን እንደሆነ ተጣርቶ ለምዕራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበው ሪፖርት ላይ ክርክሩን ያስነሳው ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ሚስት አባት መሆኑን፤ የ1ኛ ተጠሪ ሚስትም ክርክሩን ያስነሳውና በውርስ ከአባትዋ የተላለፈላትን የመሬት ይዞታ ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠች ሲሆን ክርክር የተነሳበት ይዞታ የአመልካች እንዳልሆነ ተረጋግጧል፡፡

በኦሮሚያ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሠረትም ቋሚ ንብረት ሽያጭን የሚከለክል ቢሆንም የመሬት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የሚጠይቀው ወገን ከውሉ መፍረስ የተነሳ ጥቅም ያለው ሰው ብቻ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1808 ንዑስ አንቀጽ 2 ስለሚደነግግ

አመልካች የመሬት ሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችልም በማለት የተወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

መዝገቡ አመልካች ካቀረቡት አቤቱታ ጋር ተጣምሮ ተመርምሯል፡፡ ጉዳዩ ለጉባኤው የቀረበው አመልካች የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ላይ ከንብረት መብታቸው ጋር የሚቃረን መሆኑን በመግለጽ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጣቸው በጠየቁት አቤቱታ መነሻነት ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች እንዲመለስላቸው የሚጠይቁት በገጠር የሚገኝ የመሬት ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠች መሆኑ ቢረጋገጥም አመልካች በዚህ ይዞታ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን አላስረዱም በማለት የወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ  መረዳት ተችሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ሲመለከት ክርክር የተነሳበትን የመሬት ይዞታ የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠች መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የመሬት ሽያጭ ውሉም መፍረስ አይገባውም ያለው አመልካች ከውሉ መፍረስ የሚያገኙትን ጥቅም አላረጋገጡም በሚል ምክንያት ነው፡፡

ነገር ግን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) ላይ በገጠርም ሆነ በከተማ መሬት እና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው የሚለውን ድንጋጌ ስንመለከት በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪዎች መካከል የተደረገው የመሬት ሽያጭ ውል መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ከሚከለክለው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ  አመልካች ከመሬት ሽያጭ ውሉ መፍረስ የሚያገኙትን ጥቅም አላረጋገጡም ብሎ የመሬት ሽያጭ ውሉ ሳይፈርስ እንዳለ እንዲቀጥል የወሰነው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) ጋር የሚቃረን መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የተስማማ ስለሆነ ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው ክርክር የተነሳበት ይዞታ መሬት

የአመልካች የይዞታ መሬት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ከአባቷ በውርስ ተላልፎላት ለ2ኛ ተጠሪ በብር 1400.00 /አንድ ሺ አራት መቶ ብር/ የሸጠችለት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ መብትና ጥቅም የለህም ተብሎ የአመልካች ጥያቄ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ውድቅ መደረጉን ነው፡፡ ይህም ቢሆን የመሬት ሽያጭ ውል መኖሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ ውሉ ሳይፈርስ መታለፉ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) መሠረት በገጠርም ሆነ በከተማ መሬት እና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው፤ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ ስለተገኘ በፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ አመልካች በይዞታው ላይ መብት የለውም መባሉ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ቢሆንም የመሬት ሽያጭ ውሉ ሳይፈርስ እንዳለ እንዲቀጥል ጉዳዩን የተመለከተው የዶባ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውና በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የጸናው ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3) የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የውሳኔውን አፈጻጸም ውጤት በተመለከተ በአጣሪ ጉባኤው የተባለ ነገር ባይኖርም ከክርክሩ ሒደት አመልካች ክርክር በተነሳበት መሬት ላይ ባለመብት እንዳልሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ የመሬት ይዞታው በፍርድ ቤቱ በማስረጃ ተረጋግጧል በተባለው መሠረት የ1ኛ ተጠሪ ሚስት ቢሆንም ባለመብቷ በሕገወጥ የሽያጭ ውል የተላለፈው መሬት እንዲለቀቅላቸው ባለመጠየቃቸው ምክንያት 2ኛ ተጠሪ በሕገ ወጥ የሽያጭ ውል ገዝተው በያዙት መሬት ተጠቃሚ ሊሆኑ ስለማይገባ በመሬቱ ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን ጠይቆ እስኪረከብ ድረስ መሬቱ በሚመለከተው የመሬት አስተዳደር ስር እንዲቆይ ተወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.020/08**

**የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የሥራ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም**

**አመልካች፡- አቶ ነጋሽ ዱባለ**

**ተጠሪ፡- አዲስ አበባ ቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 17 ቀበሌ 20**

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2006 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.22719 የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብቴን የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ለአጣሪ ጉባኤ በማመልከታቸው ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች ነሐሴ 07 ቀን 2006 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.22719 የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብቴን የሚቃረን በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአቤቱታውም ፍሬ ነገር በአጭሩ ሲታይ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ በወረዳ 17 ቀበሌ 20 በካርታ ቁ.32221 እና የባለቤትነት ደብተር ቁ.17/31791 የተመዘገበ ቁጥራቸው 1304፣ 1305 እና 1306 የሆኑ በአንድ ጣሪያና ግድግዳ ተያይዘው የተሰሩ ቤቶች የቀበሌው ጽሕፈት ቤት ቤቱን አለአግባብ ለሦስት ግለሰቦች አከራይቷል በማለት አመልካች በቀበሌው ጽሕፈት ቤትና በተከራዮቹ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ መስርተው የሥራና ከተማ ልማት ቢሮም ጣልቃ ገብቶ ተከራክሮ ፍርድ ቤቱም አመልካችን የቤቱ ባለቤት /ባለመብት/ በማድረግ ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ወስኗል፡፡

ውሳኔው እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለፀና አመልካችም የፍርድ አፈጻጸም ከፍተውና ቤቱን ተረክበው በእድሳት ላይ እያሉ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤቶቹን ካርታና ደብተር እንዲመክን በማድረጉ በፍርድ አፈጻጸም ተገደው የወጡት ግለሰቦችም ቤቱን በኃይል እንዲይዙባቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት አመልካች ካርታው አለአግባብ መምከን የለበትም በማለት የሰነዱ ሕጋዊነት እንዲቀጥልና ሦስቱም ግለሰቦች ቤቱን እንዲለቁ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እና በሃይል ቤቱን በያዙት ግለሰቦች ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ መስርተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የቤት ማረጋገጫ ሰነድ ያለ በቂ ምክንያት ሊሰረዝ አይገባም፣ ቤቱም በአዋጅ ቁ.47/67 መሠረት ለመወረሱ የቀረበ ማስረጃ የለም፣ አመልካች ቤቱን በፍርድ አፈጻጸም ከተረከቡ በኋላ ሰነዱን ማምከኑ አላግባብ ነው፣ እንዲሁም አመልካች ሌላ ቤት ነበረው የሚባለው ክርክር በወቅቱ አዋጅ ቁ.47/67 ሥራ ላይ ሲውል እንጂ አሁን አይደለም በማለት ያመከነውን የቤት ሰነድ ካርታ ቁ.32221 እና የደብተር ቁ.17/31791 በቤት ቁ.1304፣ 1305 እና 1306 በሆኑት ላይ ተፈጻሚነታቸው እንዲቀጥል ሲል ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔውን ያፀደቀ ሲሆን

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መስጠት፣ መከልከልና መሰረዝ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን ስለሆነ አመልካች ይህንን የባለቤትነት ማረጋገጫ በእጁ ሳያስገባ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረቡ አላግባብ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡ አመልካችም በሕገ መንግሥቱ የተመለከተው የንብረት ባለቤትነት መብቴ ተጥሶ በፍርድ አፈጻጸም የተረከብኩትና በአዋጅ ቁ.47/67 ያልተወረሰ ቤቴን ግለሰቦች በኃይል ይዘው እየተጠቀሙበት ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካችን አቤቱታና የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እንደመረመርነው አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቤቶች በፍርድ ባለመብት ሆነው በአፈጻጸም ከተረከቡ በኋላ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩንና የቤቶቹን ካርታ ማምከኑ እንዲሁም በፍርድ አፈጻጸም ተገደው የወጡ ግለሰቦች እንደገና ተመልሰው ቤቱን በኃይል መያዛቸው ከቀረበው የውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሰነዱን ለመሠረዝ ምክንያት ያደረገው አመልካች ከአሁኑ ቤት ሌላ የራሱ የሆነ ቤት የነበረው ስለሆነ ቤቱ በአዋጅ ቁ.47/67 በትርፍነት ተወርሷል በማለት ነው፡፡ ክርክር የተነሳበት ቤት በአዋጅ ቁ.47/67 ያልተወረሰ ነው በማለት በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሳይሻር የሥራና ከተማ ልማት የቤቱን ሰነድ የማምከኑን አግባብነት መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

አመልካች በቀበሌ ጽሕፈት ቤትና ቤቱን ያለአግባብ ይዘዋል ብለው በመሠረቱባቸው ክስ ላይ የሥራና ከተማ ልማት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ቢያመለክትም እስከ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጥያቄው ውድቅ ሆኖበታል፡፡ ቤቱም ለአመልካች እንዲመለስ ሲወሰን በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም እስከ መጨረሻው ውሳኔው ፀድቆ የፍርድ አፈጻጸም ተከፍቶ እንደ ፍርዱ ተፈጽሞ እያለ ሰነዱ መምከኑ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ የሕግ የበላይነት ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች አንዱ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ሲከበሩና ሲፈፀሙ ነው፡፡ ተጠሪ ከዚህ በተቃራኒ ክርክሩ በፍርድ ቤት ውድቅ ሲደረግበት ስልጣኑን በመጠቀም የቤቱን ሠነድ ማምከኑ ፍርዱ እንዳይከበርና ተፈፃሚነት እንዳይኖረው አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች አቤቱታውን እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ የቤትና አፈር ግብር እየከፈሉበት መሆኑን እንደ ተጨማሪ ማስረጃ የተለያዩ ደረሰኞችን ከአቤቱታው ጋር አያይዘው አቅርበዋል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

1ኛ. ከ1968 እስከ 1984 ዓ.ም የከፈሉበት፣

2ኛ. ከ1987 እስከ 1992 ዓ.ም የከፈሉበት፣

3ኛ. ከ1997 እስከ 2006 ዓ.ም የከፈሉበትን የቤትና የቦታ ግብር ደረሰኞች ለማስረጃ አቅርበዋል፡፡

ጉባኤው ቤቱ ከሚገኝበት ቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አስፈላጊው ማጣራት እንዲደረግ ለጽ/ቤቱ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት የጉባኤው ጽሕፈት ቤት በደብዳቤ ቁ.646/01/07 በቀን 17/02/2007 እና አጠጉ /634-06-08 በቀን 17/06/08 ዓ.ም ለጉባኤ ጽሕፈት ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ለቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የቤቱ ማህደር ታይቶ አስፈላጊው መረጃ እንዲሰጥ ጠይቋል፡፡ ለቦሌ ክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት በደብዳቤ ቁ.ቦ/ክ/ከ/7836/08 በቀን 01/09/2008 ዓ.ም ለጉባኤው ጽሕፈት ቤት በሰጠው መልስ በአመልካች ስም የቤት ካርታና የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጠበትን ጊዜ የሚመለከት በማህደሩ ውስጥ የሌለ መሆኑንና በቁ.17/31791 የተመዘገበ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሁም የ1988 ዓ.ም የገበሩበት የግብር ደረሰኝ በማህደሩ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን፣ በአሁኑ ሰዓት የማያገለግልና አዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሌለው መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔው እንዳተተው የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የመስጠትም ሆነ የመሰረዝ ሥልጣን አለው ቢልም ቢሮው የአንድ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መሠረዝ የሚችለው በበቂ ምክንያት እንጂ ከያዝነው ጉዳይ አንጻር አመልካች በፍርድ ባለመብት በሆኑበት ጉዳይ ላይ ሊሆን አይችልም፡፡ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ አለአግባብ ሊነጠቅ ወይም ሊሰረዝ አይገባም፡፡

የኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(8) መሠረት የግል ንብረት ባለቤትነት መብት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግሥት ለመወሰድ የሚችልበት አግባብ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የተጠሪ ድርጊት ከዚህ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ በተቃራኒ የአመልካች የንብረት ባለቤትነት መብትን ያሳጣ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች የቤቱ ባለቤት መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ በአፈፃፀምም ከተረከቡ በኋላ ፍርዱ ሳይሻር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዱን ማምከኑ በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚቃረን ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ አመልካች ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ቤት ላይ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ክርክር አካሒደው በመጨረሻም ባለቤት መሆናቸው በፍርድ ተረጋግጦ እያለና በአፈፃፀምም በፍርድ ኃይል ከተረከቡ በኋላ ፍርዱ ሳይሻር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በክርክሩ ቢረታም የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዱን በራሱ ውሳኔ ማምከኑ በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1) የተመለከተውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚቃረን መሆኑን ተረድቷል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ መሥሪያ ቤት ካርታ የማምከን እርምጃ ከዚህ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ በተቃረነ ሁኔታ የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት ያሳጣ ሆኖ እያለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በፍርድ ባለመብት ሆነው እያለ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮው የአመልካችን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ መሰረዙ በአግባቡ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል በሚል የተደነገገውን የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ.022/08

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የሥራ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ

ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም

**አመልካች፡- ቄስ ወርቁ ዳዲሞስ**

**ተጠሪዎች፡- 1 ወ/ሮ ሰብለ ወንጌል ወርቁ**

**2. ወ/ሮ ማሚቴ ወሬራ**

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች የካቲት 04 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለጉባኤው ያቀረቡት ጥያቄ የደቡብ ክልል እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በእኔ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 የተረጋገጠልኝን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሳጣ በመሆኑ ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት ለአጣሪ ጉባኤው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች የካቲት 04 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለጉባኤው ያቀረቡት ጥያቄ የደቡብ ክልል እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በእኔ ላይ ያስተላለፉት ውሳኔ በሕገ

መንግሥቱ አንቀጽ 40 የተረጋገጠልኝን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሳጣ በመሆኑ ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ሲሆን ይዘቱም እናቴ ለሆኑት 2ኛ ተጠሪ ገንዘብ ከአውስትራሊያ በመላክ በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ ሂጣታ ቀበሌ በስማቸው ቤት ገዝተውልኝ እኔም በመመላለስ ቤቱን ስሰራ ቆይቼ ቤቱን እና ሰነዱን ሊያስረክቡኝ ስላልቻሉ በፍርድ ሀይል ያስረክቡኝ የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ቤቱ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን አምነው መልሳቸውን የሰጡ ቢሆንም አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ በመግባት ቤቱ የተገዛው 2ኛ ተጠሪ እና እኔ በጋብቻ ወቅት ያፈራነው እና ከብር 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር በላይ አውጥተን አሻሽለን በመሥራት አከራይተን እየተጠቀምንበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አከራካሪው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት የወሰነ ሲሆን የዚሁ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት 1ኛ ተጠሪ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው በመሆኑ ጉዳዩ በፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሚታይ ነው በማለት ጉዳዩን ሳይመለከተው ቀርቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ሰበር ችሎቱም ቤቱ የተሰራው በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ መሆኑን በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን በመጥቀስ በፍ/ሕ/ቁ.1195 መሠረት የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ያለው ሰው የቤቱ ባለቤት እንደሆነ ግምት ቢወስድም በፍ/ሕ/ቁ.1196 መሠረት ግምቱ በማናቸውም ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት ወስኗል፡፡

ጉባዔውም የአመልካችን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች በአቤቱታቸው ተጣሰብኝ በማለት የገለፁት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ በነበርንበት ወቅት ያፈራነውን የጋራ ንብረት ፍርድ ቤቶች የ1ኛ ተጠሪ ንብረት ነው በማለት መወሰናቸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ላይ የተረጋገጠልኝን የንብረት መብቴን ይጥሳል የሚል ነው፡፡

በአመልካችና ተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር በሚስት ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው ወይስ የ1ኛ ተጠሪ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች በክርክር ወቅት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ከ1949 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ መቆየታቸውን፣ 1ኛ ተጠሪን ጨምሮ 11 ልጆች ማፍራታቸውን እና አሁን ክርክር ያስነሳውንና በሚስት ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት በጋራ ካገኙነው ገቢ የተገዛ በመሆኑ የጋራ ንብረት ነው በማለት ምስክሮችን ያቀረቡ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤት ቤቱ የአመልካች ሚስት በሆኑት በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ ይገኝ እንጂ ቤቱ የተገዛውና ማሻሻያ የተደረገበት በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ በመሆኑ አከራካሪው ቤት የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ይህንን የፍርድ ቤት ውሣኔ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 34(3) ላይ ለቤተሰብ ከሰጠው ከለላ እና ከአመልካች ሕገ መንግሥታዊ የንብረት መብት አንፃር በመመርመር የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የተከተለ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ማየት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሠረት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(3) ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረታዊ መነሻ መሆኑን እና ከሕብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ይህንን ድንጋጌ መሠረት አድርገው የወጡ የፌዴራልና የክልል የቤተሰብ ሕጎችንም ስንመለከት ለቤተሰብ ተገቢውን ጥበቃ እንደሚያደርጉ መረዳት ይቻላል፡፡ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.79/1995 ላይም በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ንብረት የግል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ካልተመዘገበ በስተቀር የጋራ ነው የሚል የሕግ ግምት ያስቀመጠበት ምክንያት ይህንኑ ሕገ መንግሥታዊ ከለላ ለማጠናከር ነው፡፡

የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች በተመሳሳይ መልኩ ቤቱ የተገዛውና ማስፋፊያ የተደረገበት በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህም ውሳኔ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ የተቀመጠውን የሕሊና ግምት መነሻውን አድርጎ የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮች ይህንን የሕሊና ግምት ማስተባበል ያለማስተባበላቸውን ሳይመረመር መተላለፉ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ሲመለከት በፍ/ሕ/ቁ.1195 ላይ ያለው የባለሀብት የህሊና ግምት ሊስተባበልባቸው የሚችሉባቸው ሁኔታዎች በፍ/ሕ/ቁ.1196

ላይ ተዘርዝረው ሳለ አንዱም ሁኔታ ሳይሟላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናቱ ተገቢ ካለመሆኑም በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠን ባለሀብትነት በምስክሮች ሊስተባበል የማይችል መሆኑን የሚደነግገውን የማስረጃ መርህ ከግምት ያስገባ አይደለም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አከራካሪው ቤት የተገዛው ተጠሪ ከአውስትራሊያ በላኩት ገንዘብ ቢሆን እንኳን የተላከው ገንዘብ እንደ ስጦታ ከሚቆጠር በስተቀር 2ኛ ተጠሪ የቤቱ ባለመብት መሆናቸውን ሊያስተባብል አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ውሳኔው በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችም በጋብቻ ውስጥ የተፈራን የጋራ ንብረት ለማሸሽ ዕድል የሚፈጥር እና የሕብረተሰብ መሠረት መሆኑ እውቅናና ከለላ የተሰጠውን ቤተሰብ ህልውና የሚጎዳ ነው፡፡

ይህ ደግሞ በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተቀመጠው የሕሊና ግምት ባልተስተባበለበት ሁኔታ ከተጋቢዎች የአንደኛው የግል ንብረት ከመሆን አልፎ የሦስተኛ ወገን የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት ውሳኔ ሕገ መንግሥቱ ለቤተሰብ ከሰጠው ከለላ አንጻር የሚቃረን ሆኖ ስለተገኘ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው የፌዴራልና የክልል የቤተሰብ ሕጎችም ለቤተሰብ ተገቢውን ጥበቃ እንደሚያደርጉ ግልጽ ሲሆን የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.79/1995 ላይም በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ንብረት የግል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ካልተመዘገበ በስተቀር የጋራ ነው የሚል የሕግ ግምት ያስቀመጠበት ሁኔታ አለ፡፡

በተጨማሪም በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠን ባለሀብትነት በምስክሮች ሊስተባበል የማይችል መሆኑን የሚደነግገውን የማስረጃ ሕግ መርህ ከግምት ባለማስገባት በአጠቃላይ በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተቀመጠው በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ንብረት የግል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ ካልተመዘገበ በስተቀር የጋራ ነው የሚል የሕግ የሕሊና ግምት በበቂ የምዝገባ ማስረጃ ባልተስተባበለበት ሁኔታ ከተጋቢዎች የአንደኛው የግል ንብረት ከመሆን አልፎ የሦስተኛ ወገን የሚሆንበት አግባብ ባለመኖሩ በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች

ያስተላለፉት ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ የንብረት መብት የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም በላይ ሕገ መንግሥቱ ለቤተሰብ ከሰጠው ጥበቃና ከለላ በተቃራኒ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ በጉዳዩ ላይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ፍርድ ቤቶችና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 38/09

**የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም፣**

**አመልካች፡-** አቶ ኪዳነ ማርያም ተክሉ አድራሻ ትግራይ ክልል፣

**ተጠሪዎች፡-** እነ አቶ ተ/ሚካኤል እንደያ አድራሻ ትግራይ ክልል፣

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ በገጠር ከሚገኝ መሬት ይዞታ ጋር ተያይዞ የተጀመረ ክርክር ሲሆን አመልካች በአቤቱታቸው ተጠሪዎች ይዘው የሚጠቀሙበት በገጠር የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታው የኔ ነው በማለት ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ተጠሪዎች በዶግዓ ተምቤን ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

ተጠሪዎችም አመልካች ክርክር የተነሣበትን የገጠር ቀበሌ ለቀው በመሄዳቸውና የነሱ የመሬት ይዞታ በልማት ምክንያት ለመንገድ ሥራ ተብሎ በመንግሥት በመወሰዱ በሕጋዊ መንገድ የተሰጣቸው ምትክ የመሬት ይዞታ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ክርክር በተነሣበት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ማን ባለመብት እንደሆነ በቀበሌው መስተዳድር ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማዘዝና በማጣራት ክርክር የተነሣበትን የገጠር መሬት ይዞታ አመልካች ለቀው በመሄዳቸዉ ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ለተጠሪዎች የተሰጣቸው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የትግራይ ክልል የደቡባዊ ምሥራቅ ዞን ማዕከላዊ ፍርድ ቤት  የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያጸናው ሲሆን ጉዳዩ በሰበር የቀረበላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ሰበር ሰሚ ችሎት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ታህሣሥ 7 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ ለጉባኤው በማቅረብ ጧሪ የሌለኝ የ78 ዓመት ሽማግሌ ስሆን እኔ መቀሌ ከተማ ብቀመጥም ክርክር የተነሳበትን የገጠር መሬት እንድጠቀም የወጣውን አዋጅ በሚቃረን ሁኔታ ይዞታዬን ለተጠሪዎች እንዲሰጥ በፍርድ ቤት  መወሰኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የፍርድ ቤቱ  ውሳኔ አመልካች ተጣሰብኝ በማለት ከጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 4 ጋር የሚቃረን መሆን ያለመሆኑ በጉባኤው ተመርምሯል፡፡ ጉዳዩን አጣርቶ ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለመስጠት እንዲቻል አመልካች ክርክር የተነሳበትን በገጠር የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታ በምን ምክንያት እንደተወሰደባቸው፣ ይዞታው በማን እጅ ተመዝግቦ እንደሚገኝ እና የአመልካች መተደደሪያ ምን እንደሆነ በሚመለከተው አካል ተጣርቶ ውጤቱ እንዲገለጽ በጉባኤው ታዟል፡፡

በዚሁ መሠረት በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማ አይደር ክፍለ ከተማ በቀን 28/07/08 ዓ.ም በቁ.562/4/ደ/11/08 በተፃፈ ደብዳቤ አመልካች በቀበሌያቸው ውስጥ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ነዋሪ መሆናቸውን፣ መተዳደሪያቸውም የቀን ሰራተኛ እና እድሜያቸውን 75 ዓመት መሆኑን ሲገልጽ የትግራይ ክልል የዱግዓ ተንቤን የአካባቢና የገጠር መሬትና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ደግሞ በቀን 09/02/09 ዓ.ም ቁ.752/መ2.01 በተፃፈ ደብዳቤ ክርክር የተነሳበት የገጠር መሬት ይዞታ ከ2005 ዓ.ም በፊት የአመልካች ይዞታ እንደነበር ከ2005 ዓ.ም በኋላ የተጠሪዎች ይዞታ በልማት ምክንያት በመንግሥት ሲወሰድ የአመልካች ይዞታ የነበረው በምትክ ለተጠሪዎች መስጠቱንና አሁን ይዞታው በተጠሪዎች ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

አመልካች ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት ይዞታ የሚገኝበትን የገጠር ቀበሌ ለቀው መቀሌ ከተማ የገቡት በ1981 ዓ.ም ቢሆንም እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ በዚሁ ይዞታቸው

ይጠቀሙ የነበረና አመልካች በ75 ዓመታቸው የቀን ሥራ እየሰሩ የሚተዳደሩ ጧሪና ተንከባካቢ የሌላቸው አቅመ ደካማ መሆናቸውን ከደብዳቤዎቹ ይዘት መረዳት ተችሏል፡፡

የተሻሻለው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ.239/2006 አንቀጽ 11 ንኡሰ አንቀጽ 1 በዚህ አዋጅ ከተፈቀዱ ምክንያቶች ውጭ ከሚኖሩበት ቀበሌ ከሁለት ዓመት በላይ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ከተማ የለቀቀ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን ያጣል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል ብሎ የሚደነግግ ቢሆንም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 5 (በ) ላይ ጧሪና ተንከባካቢ አጥተው ቀበሌአቸውን ቢለቁም በነበራቸው የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸው የተጠበቀ እንደሚሆን ከድንጋጌው መረዳት ተችሏል፡፡

አመልካች ክርክር በተነሳበት የገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸው የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) «የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል» በማለት ከተደነገገው እና ከሕገ መንግሥቱ ጋር በሚጣጣም መልኩ አመልካች ጧሪና ተንከባካቢ የሌላቸው አቅመ ደካማ ስለሆኑ የነበራቸውን በገጠር የሚገኝ የመሬት ይዞታ ቢለቁም በልዩ ሁኔታ በነበራዉ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚደነገገው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ውጭ ተጠሪዎች የመሬት ይዞታ በልማት ምክንያት በመወሰዱ የአመልካችን ይዞታ በምትክነት ይዘው እንዲጠቀሙ የተወሰነው የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(4) ጋር ይቃረናል፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገመንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 39/09

**የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እናት በለጠ አድራሻ በአ/ብ/ክ/መ/ ምዕራብ ጐጃም ዞን ጃቢ ጠህናን ወረዳ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መብራት ቤዛ በአ/ብ/ክ/መ/ ምዕራብ ጐጃም ዞን ጃቢ ጠህናን ወረዳ፣

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ይመለከታል፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምዕራብ ጎጃም ዞን በጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ከሳሽነት ሲሆን የክሱ ይዘትም በአጭሩ ባለቤቴ እና የባለቤቴ እናት ሲሞቱ ተጠሪ ከሕግ ውጭ መሬቱን ስለያዘችብኝ ትልቀቅልኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪም በበኩላቸው በይዞታው ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገብነው እኔ እና ልጆቼ ስለሆንን ይዞታውን የእኔ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት የወረዳውን አካባቢ ጥበቃ እና መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤትን አዟል፡፡ የአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤትም በሰጠው ምላሽ በይዞታው ላይ በቁ. 4 (አራት) የሚሆኑ ሰዎች የተመዘገቡ ቢሆንም ስም ዝርዝራቸውን በሚመለከት በጽሕፈት ቤቱ በኩል ምንም ማስረጃ እንደሌለ ተገልጿል፡፡

ፍርድ ቤቱ ይህንን በማድረግ በስም ዝርዝር ያልተጠቀሱ አራት ሰዎችን ማንነት በተመለከተ በተጠሪ በኩል የቀረበ የሰው ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በይዞታው ላይ የቤተሰብ አባል የሆኑት ተጠሪና ልጆቻቸው በመሆናቸው ይዞታውን ሊለቁ አይገባም በማለት

ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በይግባኝ ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጸንቷል፡፡

አመልካች በወረዳው ዐቃቤ ሕግ አስወክለው እንደገና 10/02/2005 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በሀሰት ምስክሮች የተሰጠ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ይሻርልኝ በማለት ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የተሰጠ ማስረጃ በመያዝ አመልክተው የጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍርድ ቤትም የቀድሞውን ውሳኔ በመሻር እንደገና አከራክሮ ይዞታው የአመልካች ነው ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ባይ በፍትሀ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.6 መሠረት መስፈርቱን ማሟላታቸውን ሳያስረዱ የቀድሞ ውሳኔ መሻሩ አግባብ አይደለም በማለት ለተጠሪ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፀንቷል፡፡ ጉዳዩን በሰበር ስልጣናቸው የቀረበላቸው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በጉዳዩ ላይ መሠረታው የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ወስነዋል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የካቲት 5 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ ለጉባኤው ያቀረቡት ጥያቄ ከሟች ባለቤቴ እናት ጋር በ1989 ዓ.ም በተደረገው የመሬት ሽግሽግ በቤተሰብ አባልነት ተመዝግቤ እስከ 2001 ዓ.ም የተጠቀምንበትን መሬት የሟች ባለቤት እህት የሆነችው ተጠሪ ይዞታዬን ያለአግባብ ስለያዘች እንድትልቅልኝ በፍርድ ቤት ክስ ብመሰርትም ፍርድ ቤቶች ለተጠሪ ወስነዋል፡፡ ይህ ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 40(3) እና 40(4) በመጣስ ከይዞታዬ ያፈናቀለኝ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጠኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) እና 40(4) በማጣመር ሲመረመር አከራካሪው ነጥብ በመሬት ሽግሽግ ወቅት በይዞታው ላይ በቤተሰብ አባልነት የተመዘገቡት አራት ሰዎች እነማን ናቸው? የጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍርድ ቤት እነዚህን አራት ሰዎች እነማን ናቸው? የሚለውን ፍሬ ነገር በሰው ምስክር አጣርቶ ለተጠሪ ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሠረት የቀድሞ ውሳኔ እንዲሻር ያቀረቡት ምክንያት ተጠሪ ቀድሞውኑ ያሰወሰኑት በሀሰት የምስክርነት ቃል እና የወረዳው የአካባቢ

ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አዲስ ማስረጃ ከማህበረሰቡ አግኝቻለሁ ያሉትን በመያዝ ሲሆን ይህንን አዲስ ማስረጃ መሠረት በማድረግ የዞኑና የወረዳ ፍርድ ቤት በድጋሚ ማስረጃዎችን ከመረመሩ በኋላ መሬቱ ለአመልካች ተወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ውሳኔው እንደተገለጸው ምስክሮቹ በሀሰተኛ ምስክርነታቸው በመወንጀል ያልተቀጡ በመሆናቸውና አዲስ ማስረጃ የቀረበው በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ የቤተሰብ አባልነትን አጣርቶ የመወሰን ስልጣን ያልተሰጠ አካል በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት  የቀድመው ውሳኔ የሚሻርበት ምክንያት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

አጣሪ ጉባኤው ይህንን ጉዳይ መርምሮ ለመወሰን እንዲችል ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ አዋሳኙን በመጥቀስ ቀድሞ ይዞታው የማን እንደነበር? ማን ሲጠቀምበት እንደቆየና የአመልካችና ተጠሪ መተዳደሪያ ምን እንደሆነ? አመልካችና ተጠሪ አርሶ አደር መሆን አለመሆናቸውን፣ እንዲሁም የየግል የመሬት ይዞታ ያላቸው ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ተጣርቶ እንዲቀርብ ባዘዘው መሠረት በአማራ ክልል ምዕራብ ጐጃም ዞን ጃቢ ጠህናን ወረዳ የአካባቢ ጥበቃና መሬት አስተደደር ጽሕፈት ቤት መረጃ እንዲሰጥ ተጠይቋል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምዕራብ ጐጃም አስተዳደር ዞን የፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር የግብርና አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የሥራ ሂደት የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም በቁ.097/13/2009 አንድ ገጽ ሽኚ ደብዳቤና አራት የጽሑፍ ማስረጃዎች ሰጥቷል፡፡

በዚሁ ማስረጃ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው አዋሳኝ የተጠቀሰው ይዞታ ቀድሞውኑ የአመልካች ባለቤት እናት የሆኑት የወ/ሮ አስላ ገ/እግዚእ ሲሆን ሲጠቀሙበት የቆዩትም ወ/ሮ አሰላ ገ/እግዚአ ከነቤተሰቦቻቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ተጠሪዋ በ1989 ዓ.ም 20 በ25 የሆነ መሬት በራሷ ስም የተደለደለች መሆኑን፣ በ1989 ዓ.ም ከወ/ሮ አሰላ ገ/እግዚእ ጋር አሁን ክርክር ያነሳነው የገጠር መሬት ላይ በቤተሰብነት የተቆጠሩት ወ/ሮ እናት በለጠ ከሟች ባለቤታቸው እና ከልጆቻቸው ጋር መሆኑን አረጋግጧል፡፡

አመልካች በፍኖተ ሰላም ግብርና ጽሕፈት ቤት ለአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር የሥራ ሂደት እና ለመልካም አስተዳደር ኮሚቴ በተሳሳተ ማስረጃ በተሰጠ ውሳኔ መሬቱን

ያለአግባብ ተነጠቅሁ በማለት በተደጋጋሚ በአመለከቱት መሠረት የዞኑ የመልካም አስተዳደር ኮማንድ ፖስት አቤቱታቸውን በማየት የቀረበውን አቤቱታ ወደ ቀበሌው ህዝብ ወርዶ ተጣርቶ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍትህ ጽሕፈት ቤት ቀርቦ ክስ እንዲመሠረትና መሬታቸውን በህግ ውሳኔ የሚመለስበት ሁኔታ እንዲመቻች የፍኖተ ሰላም ከተማ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር አጠቃቀም የሥራ ሂደት ባለሙያዎችና የሚመለከታቸው አመራሮች ወደ ቀበሌው ወርደው መረጃውን አጣርተው እንዲያቀርቡ በማለት ትዕዛዝ አስተላልፎ የምዕራብ ጐጃም ዞን የመልካም አስተዳደር ኮሚቴ 07/11/2007 ዓ.ም 7 አባላት ያሉት ኮሚቴ ቀበሌ ወርዶ በርካታ ህዝብ ከአወያየ በኋላ በ1989 ዓ.ም አዋሳኙ የተጠቀሰውን መሬት አመልካች በቤተሰብ አባልነት የተቆጠሩና በኋላም የተመሩት ወ/ሮ እናት በለጠ እና ቤተሰቦቻቸው እንጂ ተጠሪ በወቅቱ ራሷን ችላ የምትኖር በራሷ መሬት የተመራች መሆኑን በህዝቡ በማረጋገጥ ነገር ግን ይህንን ጉዳይ ህጋዊ አድርጐ ወደህግ አካል ለማቅረብ እና ለመከራከር መረጃው ህዝብ በተገኘበት ተጣርቶ ለሚመለከተው የህግ አካል ቀርቦ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዲመቻች ለፍ/ሰላም አስተዳደር ግብርና ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ ተጽፎላቸው መረጃው እንዲጣራ በማለት ልዩነት በሌለው ድምጽ የወሰነበትን ሰነድ ልኳል፡፡

በዚሁ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት እያረሱ ሲጠቀሙበት የነበሩት እንዲሁም ይዞታው ላይ የተቆጠሩት ወ/ሮ እናት በለጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም የራሷ 20*25 የሆነ መሬት በራሷ መደልደሏ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም በቁ.በአ2734/04/09 በቀን 24/06/2009 በኢ.ብ.ክ.መ ምዕራብ ጎጃም ዞን በፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደር የባህል አባጥር የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በሰጠው ምላሽ አመልካችና ተጠሪ አርሶ አደር መሆናቸውን አረጋግጦ ጽፏል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3-4) መሠረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የመንግሥትና የህዝብ መሆኑ በተደነገገው መሠረት የክልሉ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ሕጐች የገጠር መሬት ይዞታ የሚተላለፍባቸው ሁኔታዎች ደንግጓል፡፡ በያዘነው ጉዳይ አመልካች ከባለቤታቸው እና ከባለቤታቸው እናት ከወ/ሮ አስላ ገ/እግዚ ጋር በባለቤትነት የተቆጠሩት ለመሆናቸው የዞኑ የአካ/ጥ/ የመሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በሰጠው ማስረጃ የሚያረጋግጥ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ1989 ዓ.ም አመልካችና ቤተሰባቸው አርሶ

አደር መሆናቸውና መሬቱን ሲጠቀሙበት እንደነበረ ተረጋግጦ በፍርድ ቤት የሰው ማስረጃ በመስማት ብቻ የሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ከመሬት ያለመነቀል ሕገ መንግሥታዊ መብት ይቃረናል፡፡

ስለዚህ የፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(4) የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 31/09

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** አቶ አንድነት ከበደ፣

አድራሻ አፋር ክልል ሰመራ ከተማ፣

**ተጠሪ፡-** የአፋር ብሔራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ፣

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ትርጉም ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ በዲሲፕሊን ምክንያት ከተሰጠ የሥራ ስንብት ውሳኔ ጋር በተያያዘ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን መነሻውም አመልካች በአፋር ብሔራዊ ክልል ፍትህ ቢሮ በዐቃቤ ሕግነት በቋሚነት ተቀጥረው በክልሉ የሰነዶች፣ ጠበቆችና ማህበራት ምዝገባ ዓቃቤ ሕግ በመሆን ሲያገለግሉ የክልሉ ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ በሥነምግባር ጥፋት ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበቱ የወሰነ መሆኑን በመግለጽ በቁ. 1769/75 በቀን 10/10/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አመልካችን ከሥራ በማገዱ ነው፡፡

አመልካችም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይላቸው ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ቢያመለክቱም ጉባኤው በክልሉ ዐቃቤያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አንድ ጊዜ የሰጠውን ውሳኔ በድጋሚ የማየት ስልጣን የለውም በማለት ዘግቶታል፡፡ አመልካች አሁንም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢጠይቁም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል በማለት ይግባኙን አልተቀበለውም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የአመልካች “ዋና ቅሬታም በክልሉ ዐቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጥፋት ቢኖርብኝም ክስ ቀርቦብኝና ክሱ ደርሶኝ መልስና መከላከያዬን አቅርቤ ሳልከራከር በቀላጤ ደብዳቤ ብቻ ከሥራ ተሰናብተሃል ተብዬ መታገዴ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37፣ 41 እና 42 የተመለከቱትን መብቶቼን የሚቃረን ነው” የሚል ነው፡፡

ጉባዔውም የቀረበውን አቤቱታና የተሰጠውን ውሳኔ እንደተመለከተው አመልካች የዲስፕሊን ክስ ቀርቦባቸው ክሱ ደርሷቸው ተከራክረው ውሳኔ ስለመስጠቱ የሚገልጽ ነገር ባለመቅረቡ አመልካች ከሥራቸው የተሰናበቱት በአግባቡ ነው ወይስ ሕገ መንግሥቱን በሚቃረን መልኩ ነው የሚለውን ጉዳይ ለማጣራት የክልሉ ፍትህ ቢሮ ይህንን መረጃ እንዲልክ በደብዳቤ ቁ.አጠጉ/148/12/07 በቀን 01/12/2007ዓ.ም በደብዳቤ ቁ.1351/07 በቀን 01/06/2008 ዓ.ም እና በደብዳቤ ቁ.1351/07 በቀን 09/03/2009 ዓ.ም የጠየቀ ሲሆን የክልሉ ፍትህ ቢሮ በደብዳቤ ቁ.491/09 በቀን 20/03/2009 ዓ.ም የተጻፈ 7 ገጽ የያዘ የውሳኔ ግልባጭ ያለውን ለጉባዔው ልኳል፡፡

ከተላከው መረጃ መረዳት እንደተቻለው የክልሉ ፍትህ ቢሮ የዐቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ፣ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ውሳኔ ላይ 6 ሰዎች አመልካች በማስጠንቀቂያ እንዲታለፍ፣ ሰባት ሰዎች ደግሞ እንዲባረር ድምጽ የሰጡና አንድ ሰው በድምጽ ተአቅቦ የወሰኑ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ከዚህ ስብሰባ በኋላ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ደብዳቤ ቁ. 1769/05 በቀን 10/10/2005 አመልካች በፈፀሙት የሥራ ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣትና በታየባቸው የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ከሥራ እንዲሰናበቱ የወሰነባቸው መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፏል፡፡

በተጨማሪም በደብዳቤ ቁ.101153/2006 በቀን 26/7/2006 ዓ.ም አመልካች ጉዳዩ እንደገና እንዲታይላቸው ለዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ያቀረቡት አቤቱታ ጉባዔ አንድ ጊዜ የወሰነውን ነገር በድጋሚ የማየት ስልጣን ስለሌለው አቤቱታው ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ተያይዟል፡፡ አመልካች በክልሉ ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢጠይቁም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አላቀረቡም ተብሎ በይርጋ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የአፋር ክልል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ደንብ ቁ.12/2004 አንቀጽ 80/1/ መሠረት የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ መከላከያ መልሱን አዘጋጅቶ መቅረብ እንዲችል የቀረበበትን ክስ በዝርዝር የሚገልጽ የክስ ጽሑፍ፣ ክሱን ለማረጋገጥ የቀረበበትን ማስረጃ፣ መልስ የሚሰጥበትን ቀንና ቦታ ከሚያመለክት መጥሪያ ጋር እንዲደርሰው ማድረግ የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ከጉዳዩ ለመረዳት እንደተቻለው የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ቃለ ጉባዔ አመልካች መከሰሳቸውንም ሆነ ክሱ በአግባቡ ደርሷቸው ቀርበው መከራከራቸውን አይገልጽም፡፡ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይላቸው አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በማያውቁትና ክስ ባልቀረበባቸው እንዲሁም የመከላከል መብት ባልተጠበቀላቸውና ከውሳኔ በጀመረው ሥነ ስርዓት ከሥራ እንዲታገዱ መደረጋቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህ የአፋር ክልል ፍትህ ቢሮ ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም አመልካች ከሥራ እንዲታገዱ ወስኖ በደብዳቤ ቁ.1769/05 በቀን 10/10/2005 ዓ.ም አመልካችን ያሳወቀው የክልሉን የአቃቤ ሕግ አስተዳደር ደንብ ቁ.12/2004ን ያልተከተለና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 መሠረት ፍትህ የማግኘት መብትን የሚቃረን ነው፡፡ የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** እነ ውዱ ተስፋሁን (3 ሰዎች)

**ተጠሪ፡-** አቶ ለገሰ በላይ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ የተጀመረው በትግራይ ክልል፣ ምእራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የስር ከሳሾች እነ ውዱ ተስፋሁን (3 ሰዎች) በወልቃይት ወረዳ ዓዲ ረመጽ ከተማ የሚገኘውን የመሬት ይዞታችንና ቤታችንን አቶ ለገሰ በላይ ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅልን ይወሰንልን ሲሉ ክስ በማቅረባቸው ሲሆን ከሳሾች የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ስለሆኑ በአዋጅ ቁ.25/1988 አንቀጽ 5(2) መሠረት መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ የፍትሀ ብሔር ክርክሮች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን መሆኑ የተደነገገ ስለሆነና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የፌዴራሉን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን ደርበው እንደሚሰሩ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(4) የተደነገገ በመሆኑ የትግራይ ክልል ምእራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮና ምስክሮቻቸውን ሰምቶ የመሬት ይዞታውና ቤቱ የእነ ወ/ሮ ውዱ ተስፋሁን (3 ሰዎች) ነው በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የስር ተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) አቶ ለገሰ በላይ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የምእራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የመሬት ይዞታውና ቤቱ የአሁን ተጠሪ የአቶ ለገሰ በላይ ነው በማለት ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የአሁን አመልካቾች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን

ሰበር ሰሚ ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ እንደማይችል በመግለጽ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በመቀጠል የአሁን አመልካቾች እነ ውዴ ተስፋሁን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን የሚያቀርቡበት ጊዜ ስላለፈባቸው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ማስፈቀጃውን ተቀብሎ ይግባኛቸውን በአስር ቀናት ውስጥ እንዲያቀርቡ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመቅረቡና ሰበር ሰሚ ችሎቱም ጉዳዩ መታየት የሚገባው በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በመሆኑም ለሁለተኛ ጊዜ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት በማጣቱ ሬጅስትራሩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ በመሆኑ የአመልካቾች የይግባኝ መብት፣ ፍትህ የማግኘትና የመሰማት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው መጣሱን ገልጸው የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የአመልካቾችን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 የተደነገገውን ፍትህ የማግኘት መብትን ይቃረናል፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** አቶ ሚልክያስ አየለ

**ተጠሪ፡-** የደምቢዶሎ ከተማ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ድርጅት

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የአቤቱታው መነሻ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" የሚለው ድንጋጌ ተጥሷል በማለት በአቶ ሚልክያስ አየለ አቤቱታ አቅራቢነት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት በሰጠው የውሳኔ ሀሳብ ለምክር ቤቱ በመቅረቡ ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ኅዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሳብ ተጠሪ ድርጅት ከመንግሥት መሥሪያ ቤትነት ተለውጦ በቦርድ የሚተዳደር ኢንተርፕራይዝ ሆኖ እያለ ካለአንዳች ምክንያት ከሥራዬ እና ደሞዜ ስላፈናቀለኝ ክሴን ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርቤ ነበር፡፡

ፍርድ ቤቱም ወደ ሥራዬ እንድመለስ እና የተለያዩ ክፍያዎችን በጥቅሉ ብር 19,630(አሥራ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰለሳ) ብር እንዲከፍለኝ ወስኗል። ውሣኔውንም የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያፀናውም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ መሥሪያ ቤት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስለሆነ የስር ፍርድ

ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የላቸውም በማለት ውሳኔያቸውን በመሻር የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ የተሰጠኝን ፍትህ የማግኘት እና የመሥራት መብቴን ይጥሳል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ በአመልካች ክስ አቅራቢነት የተመለከተው የሰዮ ወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር በመ/ቁ.13251 መጋቢት 8 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.61/94 አንቀጽ 70 እና 71 መሠረት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው በሚል ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ፍርድ ቤቱ የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ከአመልካች በቀረበለት ቅሬታ መሠረት በደብዳቤ ቁ.375/SSBG-55/03 ታህሳስ 11 ቀን 2003 ዓ.ም  በተፃፈ ደብዳቤ አስፈላጊውን መመሪያ ለተጠሪ መስጠቱን በመጥቀስ ይህ አካል ‹‹የመንግሥት አካል እና ከኦሮሚያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና መልካም አስተዳደር ባገኘው ውክልና ለሰራተኞች መብት የተቋቋመ ከሆነ የአሁን ከሳሽ (ተጠሪ) ከሕግ አግባብ ውጭ ከሥራ የተገለለው እልባት እንዲያገኝ የሰጠው መመሪያ ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁ.61/1994 አንቀጽ 73/2/ መሠረት ለማስፈፀም ስልጣን አለው›› በማለት ተጠሪ በጥቅሉ ብር 19,630 (አሥራ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ሰለሳ ብር) ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፍልና አመልካችን ወደ ሥራው እንዲመልስ ሲል ወስኗል፡፡ ውሳኔውን የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት  አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አጽንቶታል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.128890 የካቲት 19 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ አዋጅ ቁ.61/94 አንቀጽ 73/2/ በሚያዘው መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት ስልጣን የኦሮሚያ ክልል የመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማስፈፀም እንጂ የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር የፃፈውን ደብዳቤ የሚመለከት አለመሆኑን በመጥቀስ በተጠሪ ድርጅት ስነ ምግባር ኮሚቴ ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት  ባለመሻሩና የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ መመልከትም የማይችል መሆኑን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ ለቄለም ወለጋ ዞን አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር አመልካችን ይመለከታል በሚል በቁ.BA18/M-98318/1/2 በቀን 30/11/2004 የአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኛ በሚል በተፈረመ ደብዳቤ፣ ተጠሪ ድርጅት ‹‹በራሱ በጀት የሚተዳደር፣ መዋቅሩም ከመንግሥት መሥሪያ ቤት የተለየ እና በቦርድ የሚተዳደር ስለሆነ በአዋጅ ቁ.16/89 የመንግሥት ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር የሚተዳደር መሆኑን ተረድተናል›› በማለት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን እንደሌለው ገልጿል፡፡

አመልካች ከላይ የተጠቀሰውን ደብዳቤ በመያዝ ክሳቸውን ለቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ.090319 በቀን 20/02/05 በሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ነው ቢልም የአስተዳደሩ ፍርድ ቤቱ ግን ከላይ በተጠቀሰው ደብዳቤ ስልጣኑ የኔ አይደለም ማለቱን በመጥቀስ ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ በመሆኑ ስልጣኑ የወረዳው ፍርድ ቤት ነው በማለት የአመልካችን መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡

የሰዮ ወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ለአመልካች ‹‹ባሉበት›› በሚል ኅዳር 6 ቀን 2005 ዓ.ም በፃፉት ደብዳቤ አንደኛ ቀደም ሲል ፍ/ቤታችን አመልካች ወደ ሥራ እንዲመለሱ ወስኖ የነበረ በመሆኑ መልሰን ጉዳዩን ለማየት የሚደግፈን ሕግ የለም፡፡ ሁለተኛ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እስካልተሸረ ድረስ የኦሮሚያ ክልል ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ በስሩ ለተዋቀረው መሥሪያ ቤት በጻፈው ደብዳቤ በማሳወቁ ብቻ ጉዳዩን ተቀብለን ለማየት አንችልም በማለት አመልካች በጉዳዩ ላይ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መመሪያ እንዲሰጥበት መጠየቅ እንደሚችሉ በማስገንዘብ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል ውሳኔውን በሰጠበት በመ/ቁ.128890 ላይ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.6 መሠረት አዲስ ማስረጃ እንዳገኙ ጠቅሰው ያቀረቡትን ማመልከቻ በመቀበል ጥር 20 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች አገኘሁ ብለው ያቀሩበት ማስረጃ ‹‹የሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤትና መልካም አስተዳደር የመልስ ሰጪውን (የአሁን አመልካች) እና የአሁን ተጠሪን ጉዳይ በተመለከተ የሚታየው በወረዳ ፍርድ ቤት ላይ ነው እንጂ እኔ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን መመሪያ መሆኑን ይህ

ችሎት አይቷል›› በማለት ማስረጃውን ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.6 አንፃር በመመርመር አመልካች እና ተጠሪ ፍርድ ቤቱ ስልጣን አለው ወይስ የለውም በሚለው ሲከራከሩበት የነበረ እና የሚያውቁት ነገር መሆኑን በመጥቀስ እንዲሁም የተጠሪ ሕገ ወጥ ድርጊት ስለመኖሩ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለኝም ማለቱ የራሱ ውሳኔ ከመሆኑ ባሻገር  የሚሰጠው መመሪያ ይህ ችሎት ከዚህ በፊት ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ መሰረቱን የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

በተጨማሪም አመልካች አግኝቻለሁ ያለውን አዲስ ማስረጃ ባገኘ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያላቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ተጣሰብኝ ሲሉ የጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ አንቀጽ 37(1) የተመለከተ ፍትህ የማግኘት መብት ነው፡፡

ፍትሕ የማግኘት መብት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(1) “ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው›› በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች፣ ተጠሪ ከሥራ ገበታዬ አፈናቅሎኛል ሲሉ ክሳቸውን ለፍርድ ቤት  አቅርበው ጉዳዩን የተመለከቱት የወረዳና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች አመልካች ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ እና ያልተከፈላቸው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉዋቸው ሲሉ ወስነዋል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የመንግሥት ሰራተኛ መሆናቸውን ጠቅሶ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የመንግሥት ሰራተኛን በተመለከተ የመንግሥት መ/ቤቱ የስነ ምግባር ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ ለመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ቀርቦ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ለአፈፃፀም ሲቀርብለት ከማስፈፀም በቀር ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ መወሰን እንደማይችል በመግለጽ የወረዳና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች የኦሮሚያ ክልል ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር ቢሮ ለቄለም ወለጋ ዞን አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስና መልካም አስተዳደር አመልካችን በሚመለከት በፃፈው ደብዳቤ

ጉዳያቸውን ማየት እንደማይችል መግለፁን በመረዳታቸው ጉዳዩን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው የመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ነው ቢልም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ግን ስልጣኑ የመደበኛ ፍርድ ቤት ነው ማለቱን በመጥቀስ ጉዳዩን አስቀድሞ ማየት ያለበት የወረዳው ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት ይዘው ቢቀርቡም የወረዳው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በፃፉት ደብዳቤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ባልተለወጠበት እንዲሁም ጉዳዩን በድጋሚ ለማየት የሕግ አግባብ በሌለበት ጉዳዩን ማየት አንችልም በማለታቸው አመልካች በደብዳቤ ጉዳያቸው እንዳይታይ ተከልክሏል፡፡

አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.6 መሠረት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለኝም ማለቱን በመጥቀስ አዲስ ማስረጃ እንዳገኙ በመግለጽ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይላቸው ቢያቀርቡም አቤቱታቸው የድንጋጌውን መስፈርት አያሟላም በሚል ተቀባይነት አላገኙም፡፡

ተጠሪ መሥሪያ ቤት የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት “የከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.78/1996›› ተብሎ በሚጠቀስ አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ተከትሎ በወጣ ‹‹የኦሮሚያ ከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁ.40/1997›› ተብሎ በሚጠቀስ ደንብ አንቀጽ 3 ስር በተራ ቁ.57 ላይ ተጠቅሶ የተቋቋመ እና በአዋጁ አንቀጽ 20 የፋይናንስ /የገንዘብ/ ምንጮች በሚለው ርዕስ ስር «ድርጅቱ በራሱ ገቢ ይተዳደራል፣ የድርጅቱ የገቢ ምንጮች፣ ከውሃ ሽያጭና ከፍሳሽ አገልግሎት ሥራዎች የሚገኝ፣ በብድር የሚገኝ፣ በእርዳታና እና በስጦታ የሚገኝ ንብረትና ገንዘብ፣ በከተማው አስተዳደር የሚመደብለትና ከማናቸውም ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚገኝ ውሃ፣ አገልግሎቶችን ለማቋቋምና ለማስፋፋት የክልሉ መንግሥት አቅማቸውን አጥንቶ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይችላ» በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ከድንጋጌው መረዳት እንደሚቻለው ድርጅቱ በሙሉ ወይም በከፊል ሊባል በሚችል መልኩ ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር አይደለም፡፡

በክልሉ የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.61/94 አንቀጽ 2/2/ መሠረት አንድ ድርጅት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሊባል የሚችለው በሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ሲሆን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በአደረጃጀቱ ጭምር በመንግሥት መሥሪያ ቤትነት የሚመደብ አይደለም፡፡ አመልካችም በክልሉ የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ የሚሸፈኑ የመንግሥት ሰራተኛ ተብለው ሊጠቀሱ የማይችሉ በመሆኑ የክልሉ የመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ያለመዳኘቱ አግባብነት ያለው ነው፡፡ የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አመልካችን እንደ የመንግሥት ሰራተኛ በመቁጠር ለተጠሪ መመሪያ መስጠቱ በተሳሳተ መነሻ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

የሰዮ ወረዳ ፍርድ ቤትም አመልካችን እንደ የመንግሥት ሰራተኛ በመቁጠር የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የሰጠውን መመሪያ እያስፈፀምኩ ነው በሚል የአመልካችን ክስ በቀጥታ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ፣ እንዲሁም የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳን ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በተሳሳተ መነሻ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎች ናቸው፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች በሕግ የመንግሥት ሰራተኛ ሊባሉ የማይችሉ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቶችን የተሳሳተ መነሻ ባለማረም አመልካችን እንደ መንግሥት ሰራተኛ በመቁጠር የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በሌላ አግባብ በመሻር የሰጠው ውሳኔ አመልካችን ላልተገባ ውጣ ውረድ የዳረገ እና ፍትህ የማግኘት መብታቸውን ያጣበበ ነው፡፡

በመሆኑም አመልካች በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳያቸውን ለመደበኛው ፍርድ ቤትም ሆነ ለክልሉ መንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርበው ማስወሰን ያልቻሉ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(1) የተጠቀሰው ፍትህ የማግኘት መብታቸው ተጥሷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር በቱ እንደተረዳው በዋናነት የሰዮ ወረዳ ፍርድ ቤት የቄለም ወለጋ ዞን ሲቪል ሰርቪስ እና መልካም አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የሰጠውን መመሪያ እያስፈጸምኩ ነው በሚል የአመልካችን ክስ በቀጥታ በመቀበል ያሳለፈው ውሳኔና ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማጽናቱ በተሳሳተ መነሻ ላይ የተመሰረተ መሆኑን እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አመልካች በሕግ የመንግሥት ሠራተኛ ሊባሉ የማይችሉ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቶችን ስህተት ባለማረም አመልካችን እንደ የመንግሥት ሠራተኛ በመቁጠር የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ የግለሰቡን ፍትሕ የማግኘት መብት ያጣበበ ውሳኔ መሆኑን ተገንዝበናል፣ አመልካችም በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳያቸውን ለመደበኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ለመንግሥት ሰራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርበው እንዳያስወስኑ መደረጉን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(1)"ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው" በሚል የተደነገገው ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው በመጣሱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም፡፡

በመሆኑም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 37(1) ድንጋጌን በሚቃረን መልኩ የሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.018/08**

**ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም**

**አመልካች፡- አቶ ታሪኩ መኮንን**

**ተጠሪዎች፡- 1.በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ**

**2. በአ/አበባ ትምህርት ቢሮ የየካ ክፍለ ከተማ ት/ጽሕፈት ቤት**

*የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡*

**ውሳኔ፣**

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት አቤቱታዬን ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው አልቀበልም በማለቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ተብሎ ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥላቸው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ለጉባዔው አቅርበዋል፡፡ በአቤቱታቸውም በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ቀጣሪነት ከጥቅምት 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ መጋቢት 19 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ በኮከበ ጽባህ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በፊዚክስ መምህርነት ተቀጥሬ ሳገለግል የየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች አዋጅ ቁ.6/2000 እና የአፈፃፀም መመሪያ ቁ.24/2000 ድንጋጌዎችን ባላገናዘበ መልኩ በቀን 19/07/2004 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከሥራ አሰናብቶኛል፡፡

ሥነ ስርዓቱን ሳይጠብቅ በጽሑፍ የተሰጠኝን የስንብት ደብዳቤ በመቃወም ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት ባቀርብም የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ቅሬታዬን በቃል አልቀበልም በማለቱ አቤቱታየን ለሲቪል ሰርቪስ ዳይሬክተር፣ ለከንቲባ ጽሕፈት ቤት እና ለአቅም ግንባታ ቢሮ ባቀርብም ተገቢው ምላሽ ያልተሰጠኝ በመሆኑ በመጨረሻ አቤቱታየን ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አቅርቤያለሁ፡፡

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በቁ. 231/48-81/482/4 በቀን 07/05/05 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አመልካች የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል የሚባል ከሆነ አዋጅና ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት የዲስፕሊን ክስ ተመስርቶባቸው መልስ የመስጠት እና የመከራከር መብታቸው ተጠብቆ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ የሚቀጡ ከመሆኑ በስተቀር በደብዳቤ ብቻ ከሥራ መሰናበታቸው አግባብ ያለመሆኑን ገልፆ ሥነ ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ ጉዳዩ ታይቶ ውጤቱን በ30 ቀን ውስጥ እንዲያሳውቅ ለየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ቢጽፍም እስካሁን መፍትሔ ያላገኘሁ ስለሆነ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብቴ ተጥሷል በማለት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በኮከበ ጽባህ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት በፊዚክስ መምህርነት እያገለገሉ ባሉበት ወቅት ከየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት በቁ.የካ/ት/ጽ/434/2004 በቀን 19/07/2004 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በት/ቤት ያሉ መምህራንን በማስተባበር የሥራ ማቆም አድማ እንዲመታና የመማር ማስተማሩ ሥራ እንዲቆም፣ ተማሪዎች እንዲበተኑ በማድረግ ተማሪዎች ለጉዳት እንዲዳረጉ፣ የትምህርት ቤቱ ሃብት እንዲባክን በማድረጋቸው ከዚህ በፊት ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ከጥፋታቸው ሊታረሙ አልቻሉም በሚል ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበቱ በተፃፈባቸው ደብዳቤ መነሻነት የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቹም የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽመዋል የሚባሉ ከሆነ ሥርዓቱ ተጠብቆ የዲስፕሊን ክስ ተመስርቶባቸው ለተከሰሱበትም የዲስፕሊን ክስ መልስ በመስጠት የመከራከር መብታቸው ሳይጠበቅ በአንድ ግለሰብ ውሳኔ ብቻ ከሥራ መሰናበታቸው እና ይኸው የመብት ጥሰትና የሥነ ሥርዓት አካሄድ እንዲታይላቸው ጉዳያቸውን ለሚመለከተው አካል ማለትም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ የአመልካችን ጉዳይ በመቀበል ፋይል ያልከፈተላቸው በመሆኑ

አመልካች በየደረጃው ላሉ ለክቡር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት እና ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ካመለከቱበት እና የሕዝብ የዕንባ ጠባቂ ተቋምም ለአመልካች መፍትሔ እንዲሰጣቸው ከፃፈው ደብዳቤ መረዳት ይቻላል፡፡

የሕዝባ እንባ ጠባቂ ተቋም ለየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት አመልካች የሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረት በማድረግ ለሚቀርብባቸው ክስ የመከራከርና መልስ የመስጠት መብታቸውን ጠብቆ ውሳኔ በመስጠት የተደረሰበትን ውጤት እንዲገለጽለት ለየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት የመፍትሔ ሀሳብ ጽፏል፡፡

የየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤት የሕዝባ እንባ ጠባቂ ተቋም ለፃፈው ደብዳቤ ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን ጉዳዩን ለማጣራት ያመች ዘንድ ትምህርት ጽ/ቤቱ ለአመልካች የስንብት ደብዳቤ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳያቸው በዲስፕሊን ኮሚቴ ታይቶ የተወሰነ መሆን ያለመሆኑ ተረጋግጦ ምላሽ እንዲሰጥ ተጠይቋል፡፡

የየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤትም ነሐሴ 04 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከአመልካች ጋር የተሰናበቱ መምህራን ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ስለጠየቁ ወደ ሥራቸው የተመለሱ ሲሆን አመልካችም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቤሮ በኩል ከሙያ ማህበሩ ጋር በመሆን ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ተደርጎላቸው ከተላኩ ክፍት ቦታና በጀት ካለ ብቻ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆናችንን እንገልፃለን የሚል ደብዳቤ ልኳል፡፡

ከዚህ ደብዳቤም መረዳት የሚቻለው አመልካች የዲስፕሊን ክስ ሳይመሠረትባቸውና ሳይከራከሩ በትምህርት ቤቱ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በተፃፈ ደብዳቤ ብቻ ከሥራ የተሰናበቱ መሆናቸውን ነው፡፡

በጉባኤው በኩል ጉዳዩን አጣርቶ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ያመች ዘንድ አመልካች በወቅቱ ለነበረው የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር የይግባኝ ማመልከቻውን ማቅረብ ያለማቅረባቸውን እና አንድ ጉዳይ በዲስፕሊን ኮሚቴ ሳይታይ በሥራ ኃላፊ በተፃፈ ደብዳቤ ብቻ የተሰናበተ ሰራተኛ የስንብት ደብዳቤውን በመያዝ የይግባኝ ፋይል ለማስከፈት ቢፈልግ የይግባኝ መዝገብ መክፈት አለመክፈቱ ተጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥበት ተጠይቆ ኅዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በወቅቱ የነበረው ሬጅስትራር የለቀቀ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ምላሽ መስጠት የማይቻል መሆኑን እንዲሁም አንድ ጉዳይ

በዲስፕሊን ኮሚቴ ሳይታይ በሥራ ኃላፊ በተፃፈ ደብዳቤ ብቻ የተሰናበተ ሰራተኛ የስንብት ደብዳቤውን በመያዝ የይግባኝ ፋይል ለማስከፈት ቢፈልግ የይግባኝ መዝገብ የሚከፈትለት መሆኑን በመግለጽ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

አመልካችም የስንብት ደብዳቤ በተሰጣቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻውን ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆናቸውን ለጉባኤው ካቀረቡት አቤቱታ ጋር በማስረጃነት ካያያዟቸው ሰነዶች መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጉዳይ ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው ‹‹አንቀበልም›› ማለቱ አመልካች በጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ተብሎ ከተደነገገው ድንጋጌ ጋር የሚቃረን መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የተስማማ ስለሆነ ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስናል የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ አመልካች የስንብት ደብዳቤ በተሰጣቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆናቸውን ለጉባኤው ካቀረቡት አቤቱታ ጋር በማስረጃነት ካያያዟቸው ሰነዶች በግልጽ ተረድቷል፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት የአመልካችን ጉዳይ ተቀብሎ ማስተናገድ ሲገባው ‹‹አንቀበልም›› ማለቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው ተብሎ የተደነገገውን የሚቃረን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ነው በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 094/07

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣

መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም

**አመልካች፡-** አቶ ሕዝቅኤል ማራ

**ተጠሪዎች፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንገዶች ባለስልጣን፣

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

አመልካች ሚያዝያ 17 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ ለጉባኤው አቅርበዋል፡፡ በማመልከቻቸውም ሙስናና ሙሰኝነትን በዜግነት ድርሻዬ በመታገሌ ከ20 ቢሊዮን ብር በላይ በሙስና የተጠረጠሩበትን ጉዳይ ለመንግሥት በማሳወቁ በደረሰብኝ በደል ጉዳዬን ለፍርድ ቤት አቅርቤ የተወሰነልኝን ፍርድና በሙስና ትግል መነሻ የተሰጠኝን የሕግ ከለላ የሚያስፈጽም ባለመኖሩ ከሥራና ደመወዝ መታገዴ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37፣13 (1)፣ 78(1)እና 80 (1) ጋር ይቃረናል በማለት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በአጭሩ ስንመለከተው አመልካች ተጠሪ በሆነው መሥሪያ ቤት የሕግ አገልግሎት ኃላፊ ሆነው እየሰሩ እያለ ተጠሪ ከሕግ ውጭ የሥራ ውሌን አቋርጧል በማለት ያልከፈላቸውን ክፍያ ከፍሎአቸው ወደ ሥራቸው እንዲመልሳቸው በስር የሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መስርተዋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አመልካችና ተጠሪን ካከራከረ በኋላ ተጠሪ አመልካችን ያሰናበታቸው ከሕግ ውጭ ስለሆነ ወደ ነበሩበት የሥራ መደብ እንዲመለሱ እና ያልተከፈላቸው ክፍያ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ ውሳኔው እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደርሶ ውሳኔው ፀንቷል፡፡

ጉዳዩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደርሶ ውሳኔው ከፀና በኋላ አመልካች ፍርድ እንዲፈፀምላቸው ጉዳዩ በተጀመረበት የሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ፋይል ከፍተው ከተጠሪ ጋር የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ አመልካች ወደ ቀድሞው የሕግ አገልግሎት የሥራ ኃላፊነታቸው እንዲመለሱ የተወሰነላቸው ቢሆንም የሕግ አገልግሎት ኃላፊ የሥራ መደብ በሹመት ሆኖ ስለመጣ በሥራ መደቡ ላይ ሊመደቡ አይችሉም በማለት ያቀረበውን ክርክር ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ አመልካች እንዲመደቡ

በሚጠይቁበት የቀድሞው የሥራ መደብ በሆነው የሕግ አገልግሎት ኃላፊ ላይ መመደብ አይችሉም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ጉዳዩን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካች ከተጠሪ መሥሪያ ቤት የተሰናበቱት ከሕግ ውጭ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ከተወሰነ በኋላ በአፈፃፀም ደረጃ የአመልካች የቀድሞ የሥራ መደብ የሆነው የሕግ አገልግሎት ኃላፊ የሥራ መደብ በሹመት የሚሰጥ ነው በማለት ተጠሪ ያነሳው ክርክር ፍርዱን ላለመፈፀም አዲስ ያቀረበው መከራከሪያ ሃሳብ ነው፡፡

ስለዚህ ተጠሪ በፍርዱ መሠረት አመልካች ወደ ቀድሞ የሕግ አገልግሎት ኃላፊ ሥራቸው መልሶ ያልከፈላቸውን ክፍያና ጥቅማ ጥቅም በመክፈል እንደ ፍርዱ ይፈፀም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ የአፈፃፀም ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ታይቶ በውሳኔ ፀንቷል፡፡

አመልካችም በአፈፃፀሙ ላይ በተወሰነላቸው መሠረት ፍርዱ እንዲፈፀምላቸው በድጋሚ የስር ፍርድ ቤቱን የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በቅጽ 13 የሰበር መ/ቁ.69471 በሥራ ላይ በሌለ መዋቅር መሠረት የተሰጠ ፍርድ ማስፈፀም አይቻልም በማለት ትርጉም የተሰጠበትን ውሳኔ በመጥቀስ ለአመልካች የተፈረደውን ፍርድ ማስፈፀም አይቻልም ብሎ ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በአፈፃፀሙ ላይ በተሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት ጉዳያቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ የአንድ የፍርድ ይዘት አሻሚ ሆኖ ተገቢ ያልሆነ ክርክር እንዳይነሳ ተገቢው ሙግት በስርአቱ ቀርቦ ከተጠናቀቀ በኋላ ፍርድ እንዴት ሊሰጥ እንደሚገባው እና ምን ምን ሁኔታዎችን ማካተት እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182 እና 183 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ይህ የፍርድ አሰጣጥ ስርአት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ለሚመለከተው ፍርድ ቤትም ሆነ ለበላይ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የፍርድ አሰጣጥ ሥርዓት ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮችም ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 190(2) እና ከሌሎች ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ሲሆን የአሰሪና

ሰራተኛ ጉዳይን የሚመለከት የዳኝነት አካል ደግሞ የአንድን የሥራ ክርክር ውጤት በተመለከተ ዳኝነት ሲሰጥ መሠረት ሊያደርጋቸው የሚገባቸውና ተለይተው ሊወሰኑ የሚገባቸው የመፍትሔ ዓይነቶች በአዋጁ አንቀጽ 39 እና በተከታይ ድንጋጌዎች ተመልክተዋል፡፡

በዚህ አግባብ የተሰጠ ፍርድ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 372 መሠረት ስልጣን ያላቸው የአፈፃፀም ችሎቶች ስለ ፍርድ አፈፃፀም የተዘረጉትን በመከተል የሚፈፀም ነው በማለት አመልካች ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ የተሰጠው ውሳኔ ከደንብ ቁ.126/2008 8(5) ድንጋጌ አንፃር መፈፀም ያለበት የሕግ አገልግሎት የሥራ መደብ በአዲሱ አደረጃጀት ምክንያት ወደ ተለወጠው የሕግ ድጋፍ የሥራ ሂደት ባለቤት የሥራ መደብ እንዲመለሱ በማድረግ ሳይሆን ለዚሁ የሥራ መደብ ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ መደብ ላይ ተመድበው መብትና ጥቅም እንዲያገኙ በማድረግ ነው በማለት የቀድሞ ፍርዱን በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካችም መጨረሻ በተወሰነላቸው ውሳኔ መሠረት ፍርዱ እንዲፈፀምላቸው በስር ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ፋይል አስከፍተው ከተጠሪ ጋር የተከራከሩ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካች መመደብ አለብኝ በማለት በሚጠይቁት የሕግ አገልግሎት ኃላፊ ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ መደብ ላይ ተመድበው እንዲሰሩ ከተወሰነላቸው በኋላ ከተጠሪ መሥሪያ ቤት በዲስፒሊን ከሥራ የተሰናበቱ በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ ለመመልከት ስልጣን ላለው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ በማለት አመልካች ወደ ሥራ ለመመለስ ካቀረቡት አቤቱታ ጋር አያይዘው ያቀረቡትን ጥያቄ ባለመቀበል የወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት ለጉባኤው የቀረበበት ምክንያት ከአሰሪና ሰራተኛ ክርክር ጋር ተያይዞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀድሞ አመልካች ወደ ሕግ አገልግሎት የሥራ ኃላፊነታቸው እንዲመለሱ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል አዲስ በተለወጠው የሥራ መደብ ተመጣጣኝ በሆነ የሥራ መደብ ላይ ተመድበው መብትና ጥቅም እንዲያገኙ በማለት ከተወሰነ በኋላ ይህ ፍርድ እንዲፈፀምላቸው የስር ፍርድ ቤትን ሲጠይቁ አመልካች ከተጠሪ መሥሪያ ቤት በዲስፒሊን የተሰናበቱ ስለሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ለመመልከት ስልጣን ላለው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ በማለት መዝገቡ በብይን መዝጋቱ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(1) አንቀጽ 37 ጋር የሚቃረን መሆን ያለመሆኑ ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም አመልካች ከተጠሪ መሥሪያ ቤት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የሥራ ውላቸው የተቋረጠ መሆኑ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ከተወሰነላቸው በኋላ ከየካቲት ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ በቃል ከሥራ አግዶ ያሰናበታቸው መሆኑን ለጉባኤው ያመለከቱና ይኸው አቤቱታቸውን በቃለ መሀላ ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተጠርቶ ባለመቅረቡ አመልካች ያመለከቱት አቤቱታ ተቀባይነት ማግኘቱን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎች ከሰጠው ትእዛዝ መረዳት ተችሏል፡፡

አመልካች ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ተወስኖ ወደ ሥራቸው ተመልሰው ድጋሚ ከተጠሪ መሥሪያ ቤት ደመወዝ ተከልክለው በቃል እስከታገዱበት ጊዜ ድረስ እንዲመደቡ የተወሰነላቸው የሥራ መደብ በሹመት የሚሰጥ ስለሆነ ሊመደቡ አይገባም በማለት ተጠሪ የሚያቀርበው ክርክር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ሰኔ 06 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ወደ ሕግ አገልግሎት የሥራ ኃላፊነታቸው እንዲመለሱ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል አዲስ በተለወጠው የሥራ መደብ ተመጣጣኝ በሆነ የሥራ መደብ ላይ ተመድበው መብትና ጥቅም እንዲያገኙ በማለት የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቶ የወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻውን ውሳኔ እስኪወስን ድረስ አመልካች ከየካቲት ወር 2008 ዓ.ም ጀምሮ በቃል ከሥራ ታግደው ደመወዝ የተከለከሉ ሲሆን የመጨረሻው ፍርድ ከተሠጠ በኋላ ፍርዱ እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት የሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም ተጠሪ የሆነውን መሥሪያ ቤት አስቀርቦ ሲጠይቅ አመልካች ከታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም ለ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት፣ ከየካቲት 13 ቀን 2008 ዓ.ም እስከ 21 ቀን 2008 ዓ.ም በአጠቃላይ ለ13 የሥራ ቀናት ከሥራ ስለቀሩ ሰኔ 23 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በዲስፕሊን ከሥራ ተሰናብተዋል በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ ሰበር ሰሚ ችሎት በመጨረሻ የወሰነውን ውሳኔ ሳይቀበል መዝገቡን በብይን የዘጋው መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3)/ሀ/ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ተብሎ በተደነገገው መሠረት የፌዴራል ፍርድ

ቤቶች አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁ.454/97 አንቀጽ 2(4) ላይ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ ተደንግጓል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሕገ መንግሥቱ ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በአመልካች ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠበት በኋላ አመልካች የስር ፍርድ ቤት ፍርዱን እንዲያስፈጽምላቸው ሲጠይቁ ፍርዱን ማስፈፀም ሲገባው የመጨረሻው ውሳኔ በሰበር ደረጃ ከተወሰነ በኋላ አመልካች በዲስፒሊን ተሰናብተዋል የሚለውን የተጠሪ መሥሪያ ቤት ክርክር በመቀበል ፍርዱን ሳያስፈጽም መዝገቡን በብይን መዝጋቱ ሕገ መንግሥቱ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰጠው ስልጣን ጋር እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9 ላይ ከሕገ መንግሥቱ የበላይነት ጋር እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ ከተደነገገው ፍትሕ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት ጋር የሚቃረን መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የተስማማ ስለሆነ ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ከኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፣ እንደመረመረውም አመልካች አቶ ሕዝቅኤል ማራ ከተጠሪው መሥሪያ ቤት ያለ አግባብ ተሰናብቻለሁ በማለት በሀዋሳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሥሪያ ቤቱን ውሳኔ በመሻር አመልካቹ ወደ ሥራ እንዲመለሱ፣ ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲከፈላቸው ወስኗል፣ ይህ ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶችም ጸንቷል፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸምላቸው ሲጠይቁ ቀደም ሲል ሲሰሩበት የነበረው የህግ አገልግሎት ሃላፊ የሥራ መደብ የሹመት የሥራ መደብ እንዲሆን በመወሰኑ በዚህ የሥራ መደብ ላይ አመልካችን መመደብ እንደማይችል ተጠሪው መሥሪያ ቤት ለፍርድ ቤቱ አስረድቷል፡፡ ይሁንና በተደረገው ማጣራት ተጠሪው መሥሪያ ቤት አመልካቹን በሌላ የሥራ መደብ ላይ መድቦ ሲያሰራቸውና ደመወዝም ሲከፍላቸው መቆየቱ ተረጋግጧል፡፡

አመልካች በፍርድ ቤት ያገኙትን ውሳኔ በፍርድ ቤት እስከ መጨረሻው በአፈጻጸም ሂደው ማስፈጸም ሲገባቸው ወደ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በመሄድ በአቋራጭ ለማስፈጸም የሄዱበት አካሄድ ተገቢነት የለውም፡፡ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤም ጉዳዩን ተቀብሎ ከተመለከተ በኋላ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ አልነበረበትም፡፡

ሆኖም አመልካቹ በሹመቱ የሥራ መደብ ላይ መመደብ አለብኝ በማለት በአፈጻጸም መዝገቡ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በመውሰድ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረጋቸውን፣ ለአጣሪ ጉባኤው ሚያዚያ 17 ቀን 2008 ዓ.ም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ማቅረባቸውን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሰኔ 6 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካቹ የሹመት የሥራ መደብ በሆነው የሕግ ድጋፍ የሥራ ሂደት ባለቤት የሥራ መደብ ላይ ይመደቡ ማለት ተገቢ እንዳልሆነ ገልጸ አመልካቹ ቀደም ሲል ይሰሩበት ከነበረው የሕግ አገልግሎት ሃላፊ የሥራ መደብ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ የሥራ መደብ ላይ ሊመደቡ ይገባል በማለት የቀድሞ ውሳኔውን በማሻሻል መወሰኑን እንዲሁም በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸምላቸው ለሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪው መሥሪያ ቤት አመልካቹ በየካቲት እና በመጋቢት ወር 2008 ዓ.ም ከሥራ ገበታቸው በመቅረታቸው በዲሲፕሊን ከሥራ የተሰናበቱ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ያስረዳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በዲስፕሊን ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችሉ በመግለጽ መዝገቡን መዝጋቱን ከቀረበው መዝገብና ከተደረገው ተጨማሪ ማጣራት መገንዘብ ተችሏል፡፡

አመልካቹ በተለያየ ጊዜ ጉዳያቸውን በየደረጃው ለሚገኙ የክልሉ እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በማቅረብ ውሳኔ አግኝተው እያለ አጣሪ ጉባኤው የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የአመልካችን ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠው ውሳኔ አለመፈጸሙ የሕግ የበላይነትን የሚቃረን ነው በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም አመልካቹ ጉዳያቸውን በየደረጃው ላሉ ፍርድ ቤቶች እያቀረቡ ውሳኔ ማግኘታቸው እየታወቀ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ተጥሷል በሚል የአመልካች አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት የሕገ መንግሥት ጉዳዩች አጣሪ ጉባኤ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተቀባይነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.08/09**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ራኒያ አህመድ ኢብራሂም

**ተጠሪ፡- ዶ/ር ኢብራሂም መሀመድ ሀሰን**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**ውሳኔ፣**

የጉዳዩ መነሻ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 እና 35 የተደነገጉትን የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች እንዲሁም የሴቶች መብትን የሚመለከት ሲሆን የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በሙሉ ድምጽ የውሳኔ ሐሳብ በመስጠት ለምክር ቤቱ በመላኩ ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 8 ቀን 2007 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረን ስንኖር የነበረ ሲሆን ተጠሪ እኔን ወደ አሜሪካን ሀገር ለእረፍት እንድሄድ ካደረጉ በኋላ ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የፍቺ አቤቱታቸውን በማስገባት ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ለታህሳስ 2 ቀን 2006 ዓ.ም እንድቀርብ የሚገልጽ የጥሪ ማስታወቂያ በማውጣትና በተንኮል ጥሪው እንዳይደርስኝ በማድረግ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34(5) መሠረት በኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ግልጽ ፈቃዴን መስጠት እየተገባኝ ፈቃዴን በግልጽ ባልሰጠሁበት፣ እንዲሁም የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁ.188/92 አንቀጽ 5(2) መሠረት በቅድሚያ መጥሪያው በአግባቡ እንደደረሰኝ መረጋገጥ ሲገባው ሳይረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በመመልከት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን አላግባብ በመጠቀም ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም የፍቺ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በፍቺው ውጤት ላይ በቀጠለው የንብረት ክርክር በተጠሪው ለቀረበው ማመልከቻ ተቃውሞዬን ባቀርብም ተቃውሞዬ ታልፎ ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጓል። መስከረም 19 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ጉዳዩ ለሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለሕገ መንግሥት

ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ እንዲላክ ብጠይቅም በአቤቱታዬ ላይ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ጉዳዩ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(5)፣ አንቀጽ 35 (1)፣ አንቀጽ 35(2)፣ አንቀጽ 35(4)፣ አንቀጽ 35(7) እና (9) በፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተጣሱ በመሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጥልኝ ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም ከአመልካች ጋር የነበራቸውን አለመግባባት ለመፍታት ጥረት አድርገው ያልተሳካ በመሆኑ አመልካችን የፈቱ መሆኑን ገልጸው አመልካችም ከዚህ በኋላ በራሳቸው ፈቃድ ወደ ውጭ ሀገር ሄደዋል በማለት ፍቺው እንዲጸድቅላቸው የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተጠሪ ያቀረቡትን የፍቺ አቤቱታ በመቀበል አመልካች ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እትም ጥሪ እንዲተላለፍ በማድረግ በጥሪው መሠረት አመልካች ሊቀርቡ አልቻሉም በማለት አመልካች በሌሉበት የፍቺ ውሳኔውን ሰጥቷል፡፡ ይህም የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ አመልካቿ ጉዳዩ ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይቅረብልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ባለመቀበል ጉዳዩን ማየት መቀጠሉን ያረጋግጣል፡፡

ፍርድ ቤቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በቀጠለው የፍቺ ውጤት ክርክር የካቲት 18 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 አስተዳደር በቤት ቁ.427 የሚገኙ የቤት ቁሳቁሶችን ቆጥራችሁ እና ገምታችሁ ለግራ ቀኙ እንድታካፍሉ የሚል እንዲሁም አመልካች ለተጠሪ የሚያስረክቧቸውን የንብረት ዝርዝር በመጥቀስ ትዕዛዙን ሰጥቷል፡፡ ውጤቱንም ለመጋቢት 8 ቀን 2007 ዓ.ም ለመጠባበቅ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት በማየት ላይ ባለው ጉዳይ ቀደም ብሎ ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው የፍቺ ውሳኔ የተከተለው የሕግ አግባብ ፍርድ ቤቱ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁ.188/92 አንቀጽ 5(1እና2) ላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች መሠረት አድርጎ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ከአጠቃላይ የውሳኔው አሰጣጥ መረዳት የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ የድንጋጌዎቹን ይዘት መመርመሩ ተገቢ ሆኖ ይታያል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 5(1) "ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት አቤቱታ ሲያቀርብ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሌላው ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፍቃደኛ መሆን አለመሆኑን ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ቅጽ መሠረት ቀርቦ እንዲያረጋግጥ መጥሪያ ይላክለታል፡፡" የሚል ሲሆን፣ የአዋጁ አንቀጽ 5(2) ደግሞ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሠረት የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ ተከራካሪ ወገን ተቃውሞውን ወይም ፈቃደኛነቱን ለፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ቀርቦ ካላረጋገጠ ተቃውሞ ለማቅረብ እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል፡፡" የሚል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም ፍርድ ቤቱ ታህሳስ 10 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው የፍቺ ውሳኔ "ተጠሪ (የአሁን አመልካች) ለቀረበባቸው ክስ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ በማለት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ 73ኛ ዓመት ቁ.80፣ ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም ዕትም ገጽ 19 ላይ ግልጽ የሆነ ጥሪ ቢያደርግም ተጠሪ ሊቀርቡ አልቻሉም" በማለት አመልካች በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃዳቸው እንደሆነ በመውሰድ ውሳኔውን መስጠቱን መረዳት ተችሏል፡፡

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34(5) ላይ "ይህ ሕገ መንግሥት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በኃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል" በሚል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የአዋጁ አንቀጽ 5(2) ድንጋጌ በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃዱን ሰጥቷል ተብሎ የሚገመተው ወገን በአግባቡ መጥሪያው ሊደርሰው እንደሚገባ ያስረዳል፡፡ ድንጋጌው መጥሪያው ባግባቡ መድረስ እንዳለበት ሲያስቀምጥ በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መሆን እንዳለበት የደነገገ በመሆኑ ከዚሁ ንዑስ አንቀጽ ይዘት አንጻር አግባብነቱ ሲታይ መጥሪያው ከአዋጁ ጋር ተያይዞ ከሚገኘው ቅጽ ጋር ለተጠሪው ተከራካሪ ወገን ደርሶት ፈቃደኛ መሆንና አለመሆኑን ሊገልጽ እንደሚገባ የሚያስቀምጥ በመሆኑ በዚሁ መሠረት መጥሪያው ባግባቡ ደርሷል ለማለት አያስችልም፡፡ አግባብነቱ ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንጻር ቢፈተሽ እንኳ ተጠሪ ህዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም የፍቺ አቤቱታቸውን አቅርበው ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም በጋዜጣ የጥሪው ማስታወቂያ እንዲወጣ መደረጉን ስናይ አመልካች በውጭ የሚገኙ መሆኑ በተጠሪ እየተጠቀሰ በቂ ጊዜ እንኳ አለመሰጠቱ

አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ መጥሪያው በአግባቡ ለአመልካች ደርሷቸዋል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡

በድንጋጌው የተቀመጠው በአግባቡ መጥሪያው የመድረስ ፍሬ ነገር መረጋገጥ የአንደኛውን ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት የመፍቀድን ሕገ መንግሥታዊ መብት ፍሬ ነገር የማረጋገጥ ውጤት ያለው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ትጋት የፍሬ ነገሩን መሟላት ማረጋገጥ እንዳለበት በቀላሉ መረዳት የሚቻል ነው፡፡

በመጨረሻም የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(5) የተከራካሪዎች በኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት የመዳኘት ፍላጎት መረጋገጥ እንዳለበት ከሚያስቀምጠው አስገዳጅ ሁኔታ አንጻር መጥሪያ አላላኩ እንደ መደበኛው የፍትሐ ብሔር ክርክር የመሰማት መብትን ለማስከበር ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ የተከራካሪ ወገኖችን ፍላጎት የማግኘት ዓላማ ተደራቢ ግብ መሆኑን ጭምር መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም በሸሪዓ ፍርድ ቤቱ አንደኛው ወገን በኃይማኖቱ ሕግ የመዳኘት ፍላጎት እንዳለው በአግባቡ ሳይረጋገጥ የተሰጠው ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለው በመሆኑ ጉባዔው በጉዳዩ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሊሰጥበት ይገባል በሚል በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ የውሣኔ ሃሳቡ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመለክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ በቀረበለት የጋብቻ ፍቺ አቤቱታ ክስ ላይ ተከሳሽ (የአሁኗ አመልካች) በሌሉበት ጉዳዩን በማየት ውሳኔ የሰጠበት አግባብ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34(5) “ይህ ሕገ መንግሥት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ **በተከራካሪዎች ፈቃድ** በኃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች

መሠረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" ተብሎ የተደነገገውንና ይህን ተከትሎ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁ.188/92 አንቀጽ 4(2) እንዲሁም አንቀጽ 5(1እና2) ድንጋጌዎች መሠረት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች በእስልምናው ሃይማኖት ስርዓት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸው መርጠው የቀረቡ ብቻ እንደሆነ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍርድ ቤት ሌላው ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን ቀርቦ እንዲያረጋግጥ መጥሪያ ሊልክለት እንደሚገባና የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት… የተደነገገውን የተከተለ ወይም ያከበረ ውሳኔ አለመሆኑ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ምክንያቱም የአሁኑ ተጠሪ የፍቺ አቤቱታውን ያቀረቡት ሕዳር 16 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ሲሆን የአሁኗ አመልካች ወደ ውጭ ሀገር (አሜሪካ) መሄዳቸው እየታወቀ ለቀረበባቸው ክስ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ… የሚለው የፍርድ ቤቱ የጥሪ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ የተደረገው ከ4 (አራት) ቀን በኋላ ሕዳር 20 ቀን 2006 ዓ.ም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ መሆኑ ሲታይ ሌላው ተከራካሪ ወገን የፍርድ ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑ መረጋገጥ እንዳለበት በሕግ የተደነገገውን ስርዓት እንኳ ያከበረ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 35 ድንጋጌዎች መሠረት ሕገ መንግሥቱ ባረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድና በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት ያላትን የአሁኗን አመልካች መብት ለማስጠበቅ ወደ ውጭ ሀገር መሄዷ እየታወቀ ተመልሳ መጥታ በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኗ ቀርባ እንድታረጋግጥ ብሎም ለቀረበባት ክስ መልስ ለመስጠት የሚያስችላት በቂ ጊዜ እንድታገኝ የሚያስችላት ረዘም ያለ ቀጠሮ መስጠት ሲገባው ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሕግ የተሰጠውን ስልጣን የአንዱን ተከራካሪ ወገን መብት ለማስከበር ብቻ ከቅን ልቦና ውጭ ያለ አግባብ የተጠቀመበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሆኑም የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት የአመልካችን እና የተጠሪን ጉዳይ በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34 እና 35 የተደነገጉትን የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች እንዲሁም የሴቶች መብት ድንጋጌዎችን በሚቃረን መልኩ የሰጠው

ውሳኔ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰት ያለበት በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.015/08**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የሥራ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣**

**ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም**

**አመልካች፡- ወ/ሮ አዜብ ቱፋ**

**ተጠሪ፦አቶ አለማየሁ መንግሥቱ**

**የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**ውሳኔ፣**

የዚህ ጉዳይ መነሻ አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ እያለን የተሰራ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ በካርታ ቁ.4495/94 የተመዘገበ፣ የ180 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት የጋራችን ሆኖ እያለ በአግባቡ እንኳ ባለተሰሙ የሰው ማስረጃዎች በመመስረት ቤቱ የተጠሪ የግሉ ነው በማለት በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 35(1)፣ 25 እና 37 ይጥሳሉ በማለት ለሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 5 ቀን 2008 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሳብ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ እያለን ተጠሪ ከጋብቻችን በፊት ከመንግሥት ባገኘው ባዶ ቦታ ላይ ከተጋባን በኋላ በጋራ ገንዘባችን የተሰራ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኝ በካርታ ቁ.4495/94 የተመዘገበ፣ የ180 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት የጋራችን ሆኖ ተጠሪም ይህን አውቆ በመንግሥት ሰራተኞች የሀብት ምዝገባ ወቅት በፌዴራሉ ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አስመዝግቦ እያለ ባግባቡ እንኳ ባለተሰሙ የሰው ማስረጃዎች በመመስረት በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 35(1)፣ 25 እና 37 ይጥሳሉ ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ከላይ በአመልካች ቅሬታ ላይ የተጠቀሰውን ቤት እና በሌላ በማይንቀሳቀስ እና በሚንቀሳቀሱ ሌሎች ንብረቶች ላይ ክፍፍል እንዲደረግ ባቀረቡት አቤቱታ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካች አከራካሪውን ቤት በሚመለከት ባቀረቡት ክርክር ተጠሪ ቀደም ብሎ ባዶ መሬት የተረከበ ቢሆንም ለዚሁ የተሰጠው ማስረጃ ተሰርዞ በቀን 17/11/2005 ዓ.ም ካርታ ተሰጥቶናል፣

ቤቱን በጋብቻችን ወቅት ነው ሰርተን ያጠናቀቅነው፣ ተጠሪም ይህን ስለሚያውቅ ነው በፌዴራሉ የስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና  ኮሚሽን የጋራ ነው ሲል ያስመዘገበው በሚል ያቀረቡት ክርክር በመሆኑ የግሌ ነው በሚል ያቀረበውን ክርክር ሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ በቀረቡ የሰው ማስረጃዎች ጋብቻቸው በ1999 ዓ.ም የተመሰረተ መሆኑን በመለየት፣ አከራካሪው ቤት ከጋብቻ በፊት ተሰርቶ የተጠናቀቀ ሆኖ በጋብቻ ውስጥ ደግሞ ለሴቶች የውበት ሳሎን አገልግሎት የሚውል አንድ ክፍል መሰራቱ ተረጋግጧል በማለት አከራካሪው ቤት የተጠሪ የግል ነው ብሏል፡፡ በጋብቻ ውስጥ የተሰራውን አንድ ክፍል ቤት በተመለከተ ተገምቶ የግምቱን ግማሽ የገንዘብ መጠን ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ በተጨማሪ ንብረቱ በፌዴራሉ ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን መመዝገቡ የጋራ አያስብለውም ሲል ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስቀርበው ከመረመሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማጽናት ወስነዋል፡፡ በጉዳዩ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

ጉባዔው በጽሕፈት ቤቱ በኩል ለአዳማ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ጉዳዩን አስመልክቶ ደብዳቤ በመፃፍ ተጨማሪ ማጣራት አድርጓል፡፡ ኤጀንሲው በቁ.01/78/39 በቀን 29/06/2003 ዓ.ም ጉዳዩ ስለ ወ/ሮ አዜብ ቱፋ እና አቶ አለማየሁ መንግሥቱ ይመለከታል በሚል ርእስ በፃፈው ደብዳቤ፡-

‹‹ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በደብዳቤ ቁ.አጣጉ 643/06/08 ቀን 25/06/2008 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ቀበሌ 01 በካርታ ቁ.4495/94 በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ አጣርተን እንድንገልጽላችሁ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ከላይ የተጠቀሰው ካርታ ቁጥር በአቶ አለማየሁ መንግሥቱ በአዳማ ከተማ በካርታ ቁ.4495/94 በቀን 21/10/1994 ዓ.ም ከ01 ቀበሌ 180 ካሬ ሜትር የመኖሪያ ቤት ለመሥራት መሬት የወሰዱ ሲሆን፣ የቤት ግንባታ ሥራ ፈቃድ ቁ.1/01/135/18618 በቀን 21/10/1994 ዓ.ም ወስደው በ2005 ዓ.ም በቀን 17/12/2005 ዓ.ም የንብረት ካርታ ቁጥር 4495/1994 በሆነው ላይ ሦስት ቤት ሰርተው ጨርሰው ካርታና ፕላን አረጋግጠው የወሰዱ

መሆናቸውን እና በስማቸው ተመዝግቦ መኖሩን እየገለጥን ለዚህ አስረጅ ሦስት ገጽ ሰነድን አባሪ በማድረግ አብረን የላክንላችሁ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡" በሚል ምላሹን ሰጥቷል፡፡

ጉባኤው በተጨማሪ ባደረገው ማጣራት አከራካሪውን ቤት በሚመለከት የፌዴራል የስነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በቀን 10/06/2007 ዓ.ም በቁ.15/መብ4-አ44/1413 ለአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በፃፈው ደብዳቤ ንብረቱ በአመልካች እና በተጠሪ የጋራ ንብረትነት መመዝገቡን በመጥቀስ መጻፉን እና አያይዞ በላከው 7 ገጽ የሀብት ምዝገባ ቅጽ ላይ ተጠሪ ንብረቱን የጋራ ነው ሲል ማስመዝገቡን መረዳት ተችሏል፡፡

የአመልካች ዋና ቅሬታ ተጠሪ አከራካሪውን ንብረት በተመለከተ በግልጽ አምኖ በፌዴራሉ ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የጋራ ነው ሲል አስመዝግቦ ፍርድ ቤቶችም አረጋግጠው እያለ ንብረቱ የተጠሪ የግል ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 35(1)፣ አንቀጽ 25 እና 37 ይጥሳል የሚል ነው፡፡

የአንድ ሕገ መንግሥታዊ መብት ጥሰት የሌላውንም ተያያዥ መብት የሚነካ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ከጉዳዩ ጋር በቀጥታ አግባብነት ካላቸው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34 (1)፣ 35 (7) እና 79 (1) አንፃር ጉዳዩ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ በጋብቻ ተጣምረው ሲኖሩ የነበረ እና ባለመግባባታቸው ጋብቻቸውን በፍቺ አጠናቀው ፍቺውን ተከትሎ ወደ ንብረት ክርክር መግባታቸውን መረዳት የሚቻል ነው፡፡

ጉባኤው በጉዳዩ ላይ የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን ለመመዝገብ ስልጣን ካለው የአዳማ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ በደብዳቤ ካደረገው ማጣራት ባገኘው ምላሽ አመልካች በፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር ጋር በሚቀራረብ መልኩ ተጠሪ ቤት ለመሥራት በቀን 21/10/1994 ዓ.ም መሬት ወስደው እንዲሁም በዚሁ ቀን የቤት ግንባታ የሥራ ፈቃድ የወሰዱ ቢሆንም ቤት ሰርተው ጨርሰው ካርታና ፕላን አረጋግጠው የወሰዱት ግን ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ ጽንቶ ባለበት በቀን 17/12/2005 ዓ.ም መሆኑ ሲታይ ተጠሪ አከራካሪው ንብረት የጋራ ነው ሲሉ ያረጋገጡበትን ግልጽ ማስረጃ ይበልጥ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪ በግራ ቀኙ በፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪ አከራካሪው ንብረት ከአመልካች ጋር የጋራችን ነው ሲል ለፌዴራሉ የስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በማመን የሰጠው ማስረጃ ያስረዳልኛል በሚል አመልካች ባቀረቡት ክርክር የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በትዕዛዙ ያስቀረበው ማስረጃ በግልጽ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ከአመልካች ጋር የጋራችን ነው ሲል በማመን ማስመዝገቡን መረዳት የሚቻል ነው፡፡ ጉባኤውም የፌዴራሉ የስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ለአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ከአባሪ ጋር የፃፈውን ደብዳቤ አስቀርቦ ይህንኑ መረዳት ችሏል፡፡

በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63(1) ሆነ በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79(1) በተመሳሳይ ‹‹አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል›› በሚል የተደነገገ ሲሆን በዚሁ መሠረት ተጋቢዎች ከፍቺ በኋላ በአንድ ንብረት ላይ የግል በመሆኑ ክርክር የሚያነሱ ከሆነ በሕጉ የተቀመጠውን ግምት የሚያስተባብል ማስረጃ ሊያቀርቡ የሚገባ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ባቀረቡት ክርክር መነሻ የሕጉን ግምት የሚያጠናክር የሰነድ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን፣ በፍርድ ቤቶች የሕጉን ግምት ሊያስተባብሉ ችለዋል የተባሉ የሰው ማስረጃዎችም መቅረባቸውን መረዳት ተችሏል። በማስረጃ አቀባበል ሕግ ወይም መርህ መሠረት በሰነድ የቀረበ በሰዎች የማስረጃነት ቃል ሊስተባበል እንደማይችል በግልጽ የተደነገገ ነው፡፡

በመሆኑም ጉባኤው በተያዘው ጉዳይ ፍርድ ቤቶች በግልጽ ይበልጥ ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ባለመቀበል ግልጽ ድንጋጌን በመጣስ የሰጡት ውሳኔ አመልካችን በፍቺ ጊዜ ያላቸውን የእኩል መብት የሚጥስ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(1) ‹‹በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በኃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡ በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል።

እንዲሁም ውሳኔው የአመልካችን ንብረት የማፍራት መብት የሚጋፋ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 35(7) ‹‹ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣

የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፤ እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም በተያዘው ጉዳይ ፍርድ ቤቶች በግልጽ ድንጋጌ ባለመመራት የሰጡት ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 79(3) ‹‹ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ፡፡ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፤ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ይኸው ጉዳዩ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ የተረዳው የአዳማ ከተማ መሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ባረጋገጠው መሠረት አመልካች በፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር ጋር በሚቀራረብ መልኩ ተጠሪ ቤት ለመሥራት በቀን 21/10/1994 ዓ.ም መሬት ወስደው እንዲሁም በዚሁ ቀን የቤት ግንባታ የሥራ ፈቃድ የወሰዱ ቢሆንም ቤት ሰርተው ጨርሰው ካርታና ፕላን አረጋግጠው የወሰዱት ግን ከተጠሪ ጋር ያላቸው ጋብቻ ጽንቶ ባለበት በቀን 17/12/2005 ዓ.ም መሆኑን ነው፡፡

በተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63(1) ሆነ በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 79(1) በተመሳሳይ ‹‹አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል በሚል ተደንግጎ እያለ በፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የአመልካችን ንብረት የማፍራት መብት የሚጋፋ ከመሆኑም በላይ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 35(7) ‹‹ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(1) ‹‹በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ

ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው›› በሚል የተጠቀሰውን ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል፡፤

በመሆኑም አጣሪ ጉባኤው ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት ያለው ሆኖ ስለተገኘ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በየደረጃው ባሉ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ. 896/05**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ.ም**

**አመልካች፦** የህፃን ሱራፌል ዘውዱ እናት እማሆይ ገ/ኢየሱስ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዘውዱ መርሻ

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የጉዳዩ መነሻ አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36 የተመለከተው የሕፃናት መብትና ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን የዓለም አቀፍ የሕፃናት መብት ስምምነትን የሚጥስ የፍርድ ቤት ውሳኔ በልጄ በሕፃን ሱራፌል ዘውዱ ላይ ስለተላለፈ ይህ እንዲታረም በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጣቸው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባኤ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡፡

የጉዳዩም ፍሬ ሃሳብ አመልካች ወ/ሮ እማሆይ ገ/እየሱስና አቶ ዘውዱ መርሻ በተባለው ግለሰብ መካከል በተደረገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ሕፃን ሱራፌል ዘውዱ ስለተወለደ የተጠሪ አባትነት ይረጋገጥልኝ በማለት አመልካች በሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱ ሲሆን ተጠሪም ክሱን ስለካደ አመልካች የሰው ምስክር አቅርባ ምስክሮቹ ከተጠሪ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸውና በኋላም ሕፃኑ የተወለደ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ተጠሪም በራሱ በኩል የሰው ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ምስክሮቹም ተጠሪና አመልካች ጎረቤታሞች እንደነበሩና ብር 1000 (አንድ ሺ ብር) በስጦታ መስጠቱን እንደሚያውቁ ሆኖም ሌላ ግንኙነት መኖሩን እንደማያውቁና ተጠሪ ግን የልጁን አባትነት አለመቀበሉን መስክረዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን በዚህ ሁኔታ ካከራከረ በኋላ የአመልካችን አቤቱታ በመቀበል ተጠሪ የልጁ አባት ነው ብሎ ወስኗል፡፡ ተጠሪም በውሳኔው ቅር በመሰኘቱ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠይቆ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም የተጠሪ

አባትነት በማስረጃ አልተረጋገጠም ሲል የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ሽሮ ተጠሪን በነፃ አሰናብቷል፡፡

አመልካቿም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ብታቀርብም በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ቅሬታዋን አላቀረበችም በማለት ተቃውሞታል፡፡ በመቀጠል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ብታቀርብም የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት አቤቱታዋ ውድቅ ሆኗል፡፡

የአመልካች ቅሬታም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ በሚያይበት ጊዜ ተጠሪው በሀሰት አመልካች በአካባቢው የለችም በማለት እኔ በሌለሁበት ጉዳዩ እንዲታይ አድርጎ ማስወሰኑን፣ ተጠሪ በከፍተኛ ፍርድ ቤት መልስ ሲሰጥ የዘረመል (DNA) ምርመራ እንዲደረግ ሲያመለከት እኔም ተስማምቼ እያለሁ ፍርድ ቤቱ አላግባብ ይህን ጥያቄ ማለፉን፣ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ይህንን ሳያጣራ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩን፣ እንዲሁም የተሰጠው ውሳኔ ‹‹In the best interest of the child” የሕፃኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም የሚለውን ዓለም አቀፋዊ መርህ›› የሚቃረንና ሕፃኑ ወላጆቹን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1) /ሐ/ እና (2) የተመለከተውን የሚፃረር ነው የሚል ነው፡፡

ፍሬ ሃሳቡ ከዚህ በላይ እንደተዘረዘረው ሲሆን ‹‹ተጠሪ አገባሻለሁ ብሎኝ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርገን ከዚሁ የተነሳ ሕፃን ሱራፌል ስለተወለደ የልጁ አባትነት ይታወቅልኝ›› ስትል አመልካች ክስ የመሠረተች ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይህን ክዷል፡፡

ሆኖም “አመልካች ከወለደች በኋላ ተጠሪው ብር 1000 በቅንነት ሰጥቻታለሁ፤ የእኔና የልጁ ደም ተወስዶ የዘረመል ምርመራ እንዲደረግልኝ” ሲል በከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን የተመለከተው የአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በኩል የቀረበው የሰው ምስክር በቂ ነው በማለት የዘረመል ምርመራውን ሳያዝ የልጁ አባት ነው ብሎ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረበውን ማስረጃ በቂ አይደለም ብሎ ውሳኔውን ሙሉ በሙሉ ውድቅ

በማድረግ ተጠሪ በቅሬታው ባመለከተው መሠረት የዘረመል (DNA) ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡

ውሳኔው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(2) ላይ የተመለከተውን እርምጃዎች ሲወስዱ በመንግሥታዊ ወይም በግል በጎ አድራት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጭው አካላት የሕፃናት ደኅንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት የሚለውን ድንጋጌ እንዲሁም ኢትዮጵያ ባጸደቀችው የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 4 መሠረት በስምምነቱ ዕውቅና ያገኙትን የሕፃናት መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ የአስተዳደርና ሌሎች ዕርምጃዎችን ሁሉ ተዋዋይ ሀገራት መውሰድ አለባቸው የሚለውን በሚቃረን መልክ የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚም የአመልካች አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉ በሞግዚቷ ስህተትና በሥነ ሥርዓታዊ ጉዳይ የሕፃኑን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ ውሳኔ መስጠቱ የሕፃኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም የሚጎዱና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1)/ሐ/እና(2) የተደነገገውን ሕፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት የሚጥስ ስለሆነ ጉዳዩ የልጁን ሕገ መንግሥታዊ መብት በሚያስጠብቅ መልኩ ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ስለሚገባ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ጉዳዩ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል የሚል ነው።

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በማድርግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው የሕጻን ሱራፌል ወላጅ እናት ሕጻኑ ከአቶ ዘውዱ የተወለደ በመሆኑ አባትነቱ እንዲረጋገጥለት በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ካቀረበች በኋላ ፍርድ ቤቱ በአመልካች በኩል የቀረበው የሰው ምስክር በቂ ነው በማለት ተከሳሹ የልጁ አባት ነው ብሎ ቢወስንም ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ በቂ አይደለም ብሎ ውሳኔውን ሙሉ

በሙሉ ውድቅ በማድረግ ተጠሪ በቅሬታው ባመለከተው መሠረት የዘረመል(DNA) ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡ አመልካቿም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ብታቀርብም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቅሬታዋን አላቀረበችም በማለት አቤቱታውን አልተቀበለውም፡፡

ይሁን እንጂ የሕጻናትን ጉዳይ በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36 ድንጋጌዎች መሠረት ፍርድ ቤቶችም ሆነ ሌሎች የመንግሥት አካላት ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወስዱበት ጊዜ የሕጻናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ እንዳለበት በአስገዳጅ ሁኔታ ተመልክቶ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሕጻኑ አባት አይደለም በማለት ሲወስንና የሰበር ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ በጊዜ ገደብ ምክንያት ውድቅ ማድረጉ የሕፃኑን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ እና የሕፃኑን መሰረታዊ መብትና ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በሕጻን ሱራፌል ጉዳይ ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1)/ሐ/እና(2) የተደነገገውን ሕፃናት ወላጆቻቸውን የማወቅና ከእነሱም እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው የሚለውን የሚቃረን ስለሆነ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ/** 021/08

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 5ኛ የሥራ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** አቶ ብርሃኑ ረጋሳ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መስከረም ምትኩ

የኢ.ፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የዚህ ጉዳይ መነሻ የሕጻን የሞግዚትነት ሥልጣንን በተመለከተ አመልካች የሸሪዓ ፍርድ ቤት የተጠሪን የሞግዚትነት ጥያቄ ተቀብሎ በማጽደቁ ሕፃን ሪያንን ለመረከብ የአፈፃፀም ፋይል አስከፍተው መጥሪያ ሲደርሰኝ ጉዳዩን ያወቅኩ በመሆኑ ፍርድ ቤት ቀርቤ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍቃዴን ባልሰጠሁበት እና ባልተከራከርኩበት የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 31፤ አንቀጽ 36(1/ሐ/እና 2) የተደነገገውን የሚቃረን ነው በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ለአጣሪ ጉባኤ ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 24 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ ማመልከቻ ለጉባኤው አቅርበዋል፡፡ በማመልከቻቸውም እኔ የክርስትና እምነት ተከታይ የሆንኩ የሙስሊም እምነት ተከታይ ከነበረችው ወ/ሮ ሲሀም መሐመድ ጋር ተጋብተን አሁን እድሜዋ 1 ዓመት ከ4 ወር የሆናት ሕፃን ሪያንን ወልደናል፡፡ ባለቤቴ ከሞተች በኋላ ተጠሪ የሆኑት የባለቤቴ እናት እና የሕፃን ሪያን አያት የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው በፌ/የመ/ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን አቅርበው ሞግዚትነቻቸውን አፀድቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የተጠሪን የሞግዚትነት ጥያቄ ተቀብሎ ካፀደቀላቸው በኋላ ሕፃን ሪያንን ለመረከብ የአፈፃፀም ፋይል አስከፍተው መጥሪያ ሲደርሰኝ ጉዳዩን ያወቅኩ በመሆኑ ፍርድ ቤት ቀርቤ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፍቃዴን ባልሰጠሁበት እና ባልተከራከርኩበት የተሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(4)፣ አንቀጽ 13፣ አንቀጽ 36 (1/ሐ/) እና (2) ጋር የሚቃረን ነው በማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ይሰጠኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች አሁን በሕይወት ከሌሉት ባለቤታቸው ለወለዷት ሕፃን ሪያን ተጠሪ የሆኑት የሕፃንዋ አያት የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን አቅርበው የሞግዚትነት ስልጣን ከተሰጣቸው በኋላ

ባስከፈቱት የአፈፃፀም ፋይል አመልካች መጥሪያ ሲደርሳቸው ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመቅረብ መቃወሚያቸውን አቅርበዋል፡፡

በመቃወሚያቸውም የሕፃን ሪያን አባት ሆነው እያለ በሌሉበት ቦታ የሕፃኗ አያት የሆኑት ተጠሪ ሞግዚት ሆነው መሾማቸው አግባብ አይደለም በማለት ለተጠሪ የተሰጠው የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ ከሰማ በኋላ ተጠሪን አስቀርቦ ያከራከረ ሲሆን ተጠሪ የአመልካች ባለቤት የሆኑት የሕፃኗ እናት ስትሞት አባት የሆነው አመልካች ሕፃን ልጁን ራሱ ተንከባክቦ ማሳደግ ሲገባቸው ሻሸመኔ የምትኖር እህቱ ጋር እንድታድግ የላኩ በመሆናቸው ሕፃኗ እኔ አያቷ ዘንድ ሆና ብታድግ የተሻለ ነው የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሸሪዓ ሕግ በክታብ ሙቅኒል ሙህታጅ 3ኛ ክፍል ከገጽ 452-455 የሕፃኗ እናት ከሞተች ሕጻኗን የማሳደግ ስልጣን የሚሰጠው ለእናት እናት (ለአያት) እንጂ ለአክስት ባለመሆኑ አመልካች ያቀረቡትን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ ለተጠሪ የተሰጠው የሞግዚትነት ስልጣን የፀደቀ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ጉባኤው የአመልካችን ጥያቄ አያይዘው ካቀረቧቸው የፍርድ ቤት ውሳኔዎች እና ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1 /ሐ/) እና (2) ጋር የሚቃረን መሆን ያለመሆኑን መርምሯል፡፡

በአንቀጽ 34(5) ላይ ሕገ መንግሥቱ የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሐይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል ተብሎ የተደነገገ ሲሆን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78(5) መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሐይማኖትና የባሕል ፍርድ ቤቶችን ሊያቋቁሙ ይችላሉ ተብሎ ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሠረት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነው ሕብረተሰብ የሚዳኝበት የሸሪዓ ፍርድ ቤት በአዋጅ የተቋቋመ ሲሆን የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁ.188/92 አንቀጽ 4/ሀ/ ማናቸውም የጋብቻ፣ የቀለብ አወሳሰን፣ አካለመጠን

ያልደረሱ ሕፃናት ሞግዚትነት እና በቤተሰብ ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ላይ ባለጉዳዮች በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ፈቅደው እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከላይ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖቹ በእስልምና ሐይማኖት ስርዓት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸው መርጠው የቀረቡ ከሆነ ብቻ ነው ተብሎ ተደንግጓል፡፡

ይህ የአዋጅ ድንጋጌም በሐይማኖታዊ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ በፈቃድ መርጦ መቅረብን እንደዋና መስፈርት ያስቀመጠ እንጂ የሌላ እምነት ተከታይ የሆነ ሰው በእስልምና ሐይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት የሚከለክል ያለመሆኑን ከአዋጁ መረዳት ተችሏል፡፡

አመልካች በአቤቱታቸው ላይ ፍርድ ቤቱ የሕፃን ልጃቸው ሞግዚትነት ጉዳይ ላይ ተጠሪ ቀርበው የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አባት ፍርድ ቤት ቀርበው ባለተከራከሩበት ቦታ መታየቱ እና የሌላ እምነት ተከታይ ሆነው በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃዳቸውን ባልሰጡበት ሁኔታ የተሰጠው ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናል በማለት አቤቱታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪ ለአመልካች ሕፃን ልጅ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ሞግዚት ሆነው ከተሾሙ በኋላ አመልካች ሕፃን ልጃቸውን እንዲያስረክቡ የአፈፃፀም መጥሪያ ሲደርሳቸው ሸሪዓ ፍርድ ቤት በመቅረብ ተጠሪ የሆኑት የሕፃን ልጃቸው አያት በሸሪዓ ፍርድ ቤት በተሰጣቸው የሞግዚትነት ስልጣን ሣይገኙ እና ሳይከራከሩ እንዲሁም የሕፃን ልጃቸው አባት የሆኑት ራሳቸው እያሉ የሞግዚትነት ስልጣን ለአያት መሰጠቱ አግባብ ያለመሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ይህም አመልካች በመጀመሪያ መጥሪያ ቢደርሳቸው ሊያነሱ የሚችሉትን ክርክር በማንሳትና ተቃውሟቸውን በማቅረብ የተከራከሩ፤ ተጠሪም የአመልካች ተቃውሞ ላይ መልሳቸውን በመስጠት ከአመልካች ጋር የተከራከሩ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት የሚቻል ስለሆነ አመልካች ከፈቃድ መስጠት ጋር አያይዘው ያቀረቡት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ከላይ የፌዴራል የሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር ከወጣው አዋጅ አንፃር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 34(5) ላይ የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በኃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም ከሚለው ድንጋጌ ጋር የማይቃረን መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1)/ሐ/ ማንኛውም ሕፃን ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱን እንክብካቤ የማግኘት፣ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰኑበት ጊዜ የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት ተብሎ ከተደነገገው ድንጋጌ አንፃር መርምረናል፡፡

ተጠሪ የሆኑት የሕፃኗ አያት ለፍርድ ቤት ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት የሞግዚትነት ስልጣኑ ሊሰጣቸው የቻለው የሕፃንዋ አባት የሆነው አመልካች ሕጻን ልጃቸውን ራሳቸው ተንከባክበው ማሳደግ ሲገባቸው ከምትኖርበት ድሬዳዋ ከተማ ሻሸመኔ የምትኖረው እህታቸው ጋር እንድታድግ በመስጠታቸው መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሕገ መንግሥቱ ላይ የሕፃኗን መብት ለማስጠበቅ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ለሕጻኗ መልካም አስተዳደግ ሲባል መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ሳይጣሩ የተወሰነ በመሆኑ ጉባኤው በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል መጣራት የሚገባቸው ነጥቦች ተጣርተው እንዲቀርቡ ከጽሕፈት ቤቱ ለሕፃናት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ደብዳቤ ተጽፏል፡፡

የሕፃናት ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤትም ግንቦት 8 ቀን 2008 ዓ.ም በቁ.ሃ/4-39/16019 በተፃፈ ደብዳቤ ለአመልካች ሕፃን ልጅ መልካም አስተዳደግ ሲባል ሕፃኗ አሁን የምትገኝበትን አክስቷን ጨምሮ በፍርድ ቤት ተከራካሪ በነበሩት የሕፃኗ አባትና አያት አካባቢ በመሄድ ቤት ለቤት ጉብኝት እና ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቃለ ምልልስ በማድረግ ለሕፃኗ መልካም አስተዳደግ ሲባል በቀጣይ ሕፃኗን የማሳደግ መብት ለወላጅ አባት ቢሰጥና ሕፃኗ ባለችበት አክስቷ ዘንድ እንድትቆይ ቢደረግ፣ ተጠሪም በሁለት ወር አንድ ጊዜ ሕጻኗን እንዲያዩዋት የጉብኝት ሁኔታ ቢመቻችላቸውና አመልካች በሥራ ምክንያት ከሻሸመኔ ድሬዳዋ ስለሚመላለሱ ሕፃኗን ድሬዳዋ ይዘው መጥተው ለተጠሪ እንዲያስጎበኙ ቢደረግ መልካም መሆኑን፣ በውይይቱ ጊዜ ተጠሪም ሕፃኗ ድሬዳዋ ከተማ የአመልካች እናት ጋር ማደግ ከቻለችና እርሳቸው በቅርብ መጎብኘት ከቻሉ ሕፃኗ ወላጅ አባቷ ጋር ብታድግ ቅሬታ እንደሌላቸው በሕፃኗም እድገት ዙሪያ ቅር የሚላቸው ነገር እንደሌለ መግለፃቸውን በመጥቀስ ሙያዊ አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በየደረጃው ቀርቦላቸው የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36(1) /ሐ/ እና (2) መሠረት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጭ አካላት የሕፃናት መብትን በቀደምትነት በማሰብ (the best interest of the child) ሕፃኗ ማን ዘንድ ብታድግ በተሻለ ሁኔታ መብቷ ይጠበቃል የሚለውን አጣርተው መወሰን ሲገባቸው ‹‹የሕፃኗ እናት ከሞተች ሕፃኗን የማሳደግ ስልጣን የሚኖራቸው አያት እንጂ የአባት እህት ወይም አክስት አይደሉም›› በማለት የወሰኑት ውሳኔ አመልካች ከጠቀሱት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1)/ሐ/ እና (2) ጋር የሚቃረን መሆኑን ጉባኤው በሙሉ ድምጽ የተስማማበት ስለሆነ ይህ የውሳኔ ሃሳብ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ በማለት ወስኗል፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው ክርክር በተነሳበት የሕፃኗ አሳዳጊነት ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ሕፃኗን የማሳደግ ስልጣን የሚሰጠው ለአያት ስለሆነ ተጠሪ የሕፃን ሪያን የሞግዚትነት ስልጣን አላቸው በማለት የወሰነው ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36(1) /ሐ/ መሠረት ማንኛውም ሕፃን ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱን እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው፤ እንዲሁም በአንቀጽ 36(2) የተደነገገውን ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤ በፍርድ ቤቶች፤ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት የሚለውን ድንጋጌ የጣሰ ከመሆኑም በላይ የሕፃኗን ደህንነትና ጥቅም ሊጠብቅ የሚችል ማን ነው የሚለውን ሳይረጋገጥ የሕጻኑዋ አባት እያለ ለአያት የሞግዚትነት ስልጣን እንዲሰጥ የሰጠው ውሳኔ አጣሪ ጉባኤው በአግባቡ እንደዘረዘረው ከላይ ከተጠቀሰው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ነው፡፡

በመሆኑም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤት እና በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሱትን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎች የሚቃረን በመሆኑ በሕገ

መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

የፌ/ም/መ/ቁ 34/09

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 3ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አመልካች፡-** ሲክስ ኮንቲኔንትስ ሆቴል ኢንክ (six Continents Hotels Inc.)

**ተጠሪ፡-** ክራውን (ባለቤት ወ/ሮ ዘውዲቱ መስፍን)

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ጋር ተያይዞ የተነሳን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሊጀምር የቻለው ተጠሪ በሄራልድ ጋዜጣ " CROWNE PLAZA" የሚለውን የንግድ ምልክት በተመለከተ ተቃውሞ ያለው እንዲቀርብ የወጣውን ማስተወቂያ መነሻ በማድረግ "CROWNE PLAZA" በሚል መጠሪያ የተመዘገበው ንግድ ምልክት የቀዳሚነት መብት ባለው "CROWN HOTEL" ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ መሆኑ "ክራውን " ከሚለው ቃል በኋላ አንዲት ፊደል በመጨመር "ክራውኔ" በማለት ተጠቃሚውን ህብረተሰብ በሚያሳስትና በሚያሳክር ሁኔታ በመቅረጽ የተጠሪን ሆቴል መልካም ስም የሚጎዳና ከፍተኛ ቁሳዊ ጉዳት የሚያደርስ ስለሆነ የአመልካች የንግድ ምልክት ሊፈርስ ይገባል ሲሉ ተጠሪ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ከሃምሌ 07 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ የተጠሪ የንግድ ምልክት በንግድ ሚኒስቴር ተቀምጦ ሲታደስ የቆየ ቢሆንም፣ ለመጨረሻ ጊዜ የታደሰው ሃምሌ 07 ቀን 2001 ዓ.ም በመሆኑ በሰርተፍኬቱ ላይ እንደተገለጸው የሕግ ጥበቃው ሃምሌ 06 ቀን 2003 ዓ.ም ስላበቃ የCROWNE PLAZA የንግድ ምልክት እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ የአመልካች የንግድ ምልክት በዓለም አቀፍ ደረጃ እና በኢትዮጵያ የሚታወቁ ሆቴሎች የሚጠቀሙበት በመሆኑ እንዲሁም CROWN HOTEL የንግድ ምልክት በያዘው የጀበናና የጎጆ ቤት ምስል ምክንያት ሊመሳሰልና ሊያሳስት ስለማይችል የተለያዩና የማያሳክሩ ናቸው ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥብቃ አዋጅ 501/98 አንቀጽ 24 መሠረት የንግድ ምዝገባ ጸንቶ የሚቆየው የምዝገባ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ጀምሮ ለ7 አመታት ነው፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በንግድ ምልክቱ ላይ እስከ ሃምሌ 06 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ የሕግ ጥበቃ ስላላቸው በሰርተፍኬቱ ላይ ያለውን የ2 ዓመት ገደብ መሠረት በማድረግ የቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት ስለሌለው ታልፏል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የተጠሪን መዝገብ አስቀርቦ ሲመለከት CROWNE PLAZA እንዲመዘገብ በቀረበ

ጥያቄ የካቲት 18 ቀን 2005 በንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና ሥራ ሂደት በተፃፈ ደብዳቤ የንግድ ምልክቱ CRWON HOTEL በሚል መጠሪያ በጽ/ቤቱ ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር በአዋጅ ቁ.501/98 አንቀጽ 7(1) መሠረት ተመሳሳይ ስለሆነ ሊመዘገብ እንደማይችል ውሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ በንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የሥራ ሂደት ግንቦት 09 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.Id218-9-05 ጸሚክስ ግሎባል አንተርኘራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማ ድርጅት በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንደተጠቀሰው ድርጅቱ ከሚሰራው ባለ 5 ኮከብ ሆቴል ኢንቨስትመንት ጋር በቀጥታ የተገናኘ መሆኑን በመጥቀስ የንግድ ምልክቱ በድጋሚ እንዲታይ በተጠየቀው መሠረት ምዝገባው እንዲቀጥል የተወሰነ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና ሥራ ሂደት CROWNE PLAZA የንግድ ምልክት ቀደም ሲል በጽ/ቤቱ ከተመዘገበው CROWN HOTEL የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ነው በሚል ውድቅ ካደረገው በኋላ በአመልካች ማመልከቻ መነሻነት የንግድ ምልክቱ ምዝገባ እንዲቀጥል ማድረግ ተገቢነት የሌለው አሰራር በመሆኑ በቀጣይ እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

በኢፌዴሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በኩል ኮሚቴው የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የሥራ ሂደት ዕለት ዕለት በሚያከናውናቸው ሥራዎች ከንግድ ምልክትና ምዝገባ ጥበቃ አዋጅ ባሻገር ሌሎች በአገሪቱ የሚገኙ ሕጎችንም ጭምር መሠረት በማድረግ መወሰን እንደሚገባ ያምናል፡፡ ከዚህ አንጻር የሥራ ሂደቱ የአገሪቱ የኢንቨስትመንት አዋጅ እና የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅን መነሻ በማድረግ CROWNE PLAZA የንግድ ምልክት ከኢንቨስትመንት አኳያ ለአገር የሚሰጠው አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት የሰጠው ውሳኔ መልካም ነው፡፡

በኢፌዴሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የአእምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ተጠሪ በጽ/ቤቱ ያስመዘገቡት የንግድ ምልክት በአመልካች ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር በዕይታ፣ በንባብና በድምጸት የሚለያዩ ናቸው፡፡ ሁለቱም ለሆቴል

አገልግሎት የሚውሉ በመሆኑ የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች አኳያ ሲታይ የኢኮኖሚ አቅም፣ የትምህርት ደረጃና የማገናዘብ አቅማቸው ከፍተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚጠቀሟቸው አገልግሎቶች በመሆናቸው ሁለቱ የንግድ ምልክቶች መሳከር የመፍጠር አቅማቸው በጣም አነስተኛ መሆኑን ተረድቷል፡፡

ስለዚህ በግራ ቀኙ ስም የተመዘገቡት የንግድ ምልክቶች በተመሳሳይ ሁኔታ የሕግ ጥበቃ አግኝተው ሥራ ላይ ቢውሉ አንዱ በሌላው አገልግሎት ላይ ጉዳትን የማያስከትል እና በተጠቃሚው ላይ የሚፈጥረው መሳከር ስለሌለ CROWNE PLAZA የንግድ ምልክት በአዋጅ ቁ. 501/98 ፈራሽ ሊደረግ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

ክርክሩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌሎች የተቃውሞ ክርክሮች ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ከዋና ክርክሮች ውስጥ በንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የሥራ ሂደት አመልካች በመጀመሪያ ያቀረበው የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በተጠሪ ስም ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይነት አለው በሚል ውድቅ ከተደረገ በኋላ እንደገና እንዲቀጥል የተደረገው ከኢንቨስትመንት አንጻር ሊከበርለት የሚችለው ከፍተኛ አስተዋጽኦን ከግንዛቤ በመውሰድ እንደሆነ ከውሳኔው ተገንዝበናል፡፡

በኢፌዴሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ከጅምሩ በሕጉ መሠረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ ይገባል ወይም አይገባም በሚለው ነጥብ ላይ የንግድ ምዝገባ፣ ጥበቃ አዋጅ፣ ዓላማና ግብ ከማሳካት አንጻር ሊታዩ የሚችሉት የጎንዮሽ ጉዳትና ጥቅሞች ላይ በቂ ጥናት ሳያደርግ በመወሰኑ፣ መጀመሪያ ውድቅ ያደረገውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ጉዳይ በድጋሚ ተመልክቶ መወሰኑ በአዋጅ ቁ.320/95 አንቀጽ 6 እና በደንብ ቁ.273/2005 አንቀጽ 19(1) እና (3) መሠረት በአመልካች የቀረበን የእንደገና ይታይልኝ ጥያቄ ተቀብሎ የመመርመር ስልጣን ስላለው ነው፡፡

ሌላው ስለንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የወጣው አዋጅ ቁ.501/1998 አንቀጽ 2(12) የንግድ ምልክት ማለት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው፡፡ ምልክቱም

ቃሎችን፣ ዲዛይኖችን፣ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀለሞችን፣ ዕቃዎችን፣ የመያዣዎቻቸውን ቅርጽ ወይም የእነዚህን ቅንጅት ሊይዝ ይችላል በማለት ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ስለዚህ ክርክሩ መነሻ የሆነው የንግድ ምልክት በተጠሪ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ስለንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የወጣው አዋጅ ቁ.501/1998 እና ደንብ ቁ.273/2005 የምዝገባ ጥያቄ ከቀረበለት የንግድ ምልክት ጋር አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ነው የሚባለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲኖሩ እንደሆነ በግልጽ የተደነገገ ነገር የለም፡፡

በመሆኑም አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ስለመሆኑ መመዘን የሚቻለው የንግድ ምልክቱ እንዲያመላክት (እንዲያስተዋውቅ) ወይም እንዲገለጽ ከተፈለገው ዕቃ ወይም አገልግሎት አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ከመሆን ወይም ከአለመሆን አንጻር አያይዞ በመመዘን እንደሆነ ከአዋጅ ቁ.501/199 አንቀጽ 6 እና 7 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር ተጠሪ በስሙ ያስመዘገበው የንግድ ምልክት CROWN HOTEL በሚል ጽሑፍና ዘውድ የተሳለበትና የጣሪያው ክዳን የጀበና ቅርጽ የሆነ መለስተኛ አዳራሽ ፎቶ ግራፍ የሚወክለው በክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው ባለ 4 ኮከብ ሆቴል የሆነ የንግደ ስሙ CROWN HOTEL የተባለ የሆቴል አገልግሎት ሲሆን፣ አመልካች ያስመዘገበውና የይፍረስ ተቃውሞ የቀረበበት CROWNE PLAZA የሚል የንግድ ምልክት እንዲወክል የተፈለገው የአገልግሎት አይነት ባለ 5 ኮከብ ሆቴል የሆነ የንግድ ስሙ ሲክስ ኮንቲኔንትስ ሆቴልስ ኢንክ (Six Continents Hotels inc) የተባለ የሆቴል አገልግሎት በመሆኑ፣ እንዲሁም አመልካች CROWNE PLAZA የሚለውን ሀረግ የሚጠቀመው ለንግድ ምልክትነት ስም CROWN HOTEL የሚል ዘውድ የተሳለበትና ጣሪያው ክዳን የጀበና ቅርጽ የሆነ መለስተኛ አዳራሽ ፎቶ ግራፍ በጣምራ በንግድ ምልክትንት የሚጠቀምበት እንደሆነ መገንዘብ በመቻሉ የንግድ ምልክቶቹ በንባብ፣ በጹሑፍ እና በድምጽ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ናቸው ለማለት የሚቻል አይደለም ሲል ወስኗል፡፡

ክርክሩን በሰበር የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁ.501/1998 መግቢያ ላይ ለንግድ ምልክቶች ጥበቃ ማድረግ ለብሔራዊ ኢካኖሚ መዳበር በተለይም ለንግድ እና ኢንዱስትሪ ልማት አወንታዊ

አስተዋጽኦ እንዳለው በመታመኑ ኢንቨስትመንት የሚያበረታታው ለንግድ ምልክቶች ጥበቃ ሲደረግ ነው በማለት አቅጣጫን የሚያሳይ ነው፡፡

አዋጁ ከወጣባቸው ምክንያቶች መካከል ዕቃ በማምረት፣ በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስምና ዝና ለመጠበቅ፣ በተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካከል መሳከርን ለማስወገድ የንግድ ምልክት ጥበቃ ለማድረግ፣ በነጻ ገበያ ስርዓት ውስጥ የሸማቾችን ምርጫ በመምራት እና ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ረገድ የሚጫወቱትን ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት እንጂ ክርክር የተነሳበት የንግድ ምልክት ለኢንቨስትመንት ተግባር እስከሆነ ድረስ አስቀድሞ የሕግ ጥበቃ የተደረገለት የንግድ ምልክትና አገልግሎት ዘርፍ ጋር የተመሳሰለ ሆኖ ቢገኝም ደርቦ ለመስጠት እንዲያስችል አይደለም፡፡

ለንግድ ምልክት የሕግ ጥበቃ እንዲያገኝ ማድረግ ኢንቨስትምንት የማበረታታት ፋይዳ አለው በሚል ያላቸውን ቁርጠኝነት ከመግለጽ በስተቀር ለኢንቨስትመንት ለታሰበ የአገልግሎት ዘርፍ አዋጅ ቁ.501/98 ስለ ንግድ ምልክት ጥበቃ ጉዳይ የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች አፈጻጸም ወደ ጎን ለማስቀረት የሚያስችል አይደለም፡፡

ኢንቨትስመንትን አስመልክቶ የወጡት ሕጎችም ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነትና ተፈጻሚነት ያለውን የአዋጅ ቁ.501/98 ዝርዝር ድንጋጌ የተፈጻሚነት ኃይሉን የሚያስቀር ስልጣን ሰጭ ድንጋጌ የላቸውም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 6 የንግድ ምልክቶች ለምዝገባ ብቁ ከማይሆንባቸው ውስጥ የአንድ ሰው አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች አገልግሎቶች በግልጽ ለመለየት የማያስችል ከሆነ፣ የምልክቱን ባህርይ የሚቀንስ ወይም የሌላውን ሰው መብት የሚጥስ ከሆነ፣ ህዝቡን የንግዱን ህብረተሰብ ሊያሳስት የሚችል ንግድ ምልክት ስለሆነ ሊመዘገብ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ከአዋጁ ዓላማና ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዘት አንጻር እየታየ ጉዳዩን በሚመለከተው አስተዳደራዊም ሆነ የዳኝነት ሰጭ አካል አስፈላጊው ውሳኔ በሕግ ከሚሰጥበት በቀር ኢንቨስትመንት በራሱ የአዋጁን ዓላማና ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲሁም ለተቋሙ በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለማስለወጥ የሚያስችል አይደለም፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 7 መሠረት የአመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄን በመጀመሪያ የተመለከተሙ የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት የሥራ ሂደት የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ከተጠሪ የንግድ ምልክት ተመሳሳይ በመሆኑ ሊመዘገብ አይችልም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ያደረገ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

በሌላ ጊዜ ፀሚክስ ግሎባል ኢንተርፕራይዝ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ስላመለከተ ምዝገባው እዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያ ለቀረበው ጥያቄ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ክፍል ሙያዊ ትንተናን መሠረት አድርጎ የሰጠውን ውሳኔ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ለውሳኔው መለወጥ መሠረት አድርጎ ከሰጠው ምክንያት ጋር ሲታይ፣ የመጀመሪያው በሙያዊ ትንተና የተደገፈ ምክንያት በመስጠት "CROWNE PLAZA የሚለው የንግድ ምልክት በጽ/ቤቱ አስቀድሞ ተመዝግቦ ከሚገኘው CROWN HOTEL ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በመገኘቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ከዚህ በኋላ አስቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ በምክንያትነት ተጠቅሶ የተገኘው የአመልካች "CROWNE PLAZA" የሚለውን የንግድ ምልክት ምዝገባ ሂደት ቢቀጥል ከኢንቨስትመንት አንፃር ሊያበረክት የሚችለው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ብቻ ከመሆኑ በቀር ሌላ የተለየ ምክንያት እንደሌለው ተገንዝበናል፡፡

ኢንቨስትመንትን ማበረታታት ተገቢ ቢሆንም ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ሲባል ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት እንዲመዘገብ እንደ መሥፈርት በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁ.501/98 ሆነ በኢንቨስትመንት አዋጅ ወይም በሌሎች ሕጎች ስልጣን ሰጭ ድንጋጌዎች በሌለበት ሁኔታ በደፈናው ኢንቨስትመንት ከማበረታታት አንጻር በሚል መወሰኑ የሕግ መሠረት የለውም፡፡

ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሕግ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁ.501/98 አንቀጽ 5፣ 6 እና 7 የተደረጉት ናቸው፡፡ ሲጠቃለል የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአገሪቱ ኢንቨስትመንት አዋጅና የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጆች መነሻ በማድረግ "CROWNE PLAZA" የንግድ ምልክት ለአገር ከሚሰጠው አስተዋጽኦ በማለት አዋጅ ቁ.501/98 ለማውጣት መነሻ ግብ ሆነው በሕጉ ስለንግድ ምልክቶች ጥበቃ አስፈላጊነት ከመግቢያው ላይ እና ዝርዝር

ድንጋጌዎች ትክክለኛ ይዘትና አፈጻጸም በመውጣት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል በማለት ውሳኔአቸው መሻሩን ገልጾ፣ የአመልካች "CROWNE PLAZA" የንግድ ምልክት ከተጠሪ "CROWN HOTEL" በሚል መጠሪያ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ መገኘቱ በአዋጅ ቁ.501/98 አንቀጽ 7(1) መሠረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ እና ሕጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ሃምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም ለጉባኤው በጻፈው አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ሀ) መሠረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ከማረም የስልጣን ገደብ በማለፍ፣ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ሙያዊ እና አለም አቀፋዊ አሰራሮች ተፈትሾ የሁለቱ የንግድ ምልክቶች እንደማይመሳሰሉና እንደማያሳክሩ ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ ፍሬ ነገር በመመልከት መወሰኑ ከተጠቀሰው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር ስለሚቃረን የሕገ መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥ ጠይቋል፡፡ ጉባኤውም በአመልካች አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ሲመለከት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ከተሰጠው የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን መሆን አለመሆኑ መርምሯል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሲመለከቱ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የሥራ ሂደት ውሳኔ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚባል ስለሆነ ጉዳዩን በድጋሚ ማየቱ እንደግድፈት እንደማይወሰድ ተመልክተዋል፡፡

በተለይም ከተያዘው ጉዳይ አንጻር ሲታይ "CROWNE PLAZA" የሚለው የንግድ ምልክት በጽ/ቤቱ አስቀድሞ ተመዝግቦ ከሚገኘው "CROWN HOTEL" ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ነው ተብሎ ውድቅ የተደረገው ውሳኔ መለወጥ የዚህ ውሳኔ መሠረት የነበሩት ፍሬ ነገሮች ሁሉ በመለወጥ የንግድ ምልክቶቹ እንደማይመሳሰሉ መደምደም የሚያስችል ነው፡፡

በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የሥራ ሂደት እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ "CROWNE PLAZA" የሚለውን የንግድ ምልክት "CORWN HOTEL" የሚል ጽሑፍ ዘውድ የተሳለበትና የጣሪያው ክዳን የጀበና ቅርጽ የሆነ መለስተኛ አዳራሽ ፎቶ ግራፍ በጣምራ በንግድ ምልክትነት የሚጠቀም እንደሆነ መገንዘብ መቻሉ የንግድ ምልክቶቹ በንባብ፣ በጽሑፍና በድምጽ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ናቸው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ስለዚህ በግራ ቀኙ ስም የተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች በተመሳሳይ ሁኔታ የሕግ ጥበቃ አግኝተው ሥራ ላይ ቢውሉ አንዱ በሌላው አገልግሎት ላይ ጉዳትን የማያስከትል እና በተጠቃሚው ላይ የሚፈጥረው መሳከር ስለሌለ "CROWNE PLAZA" የንግድ ምልክት በአዋጅ ቁ.501/98 ፈራሽ ሊደረግ እንደማይገባ መወሰናቸው እንደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አገላለጽ ጉዳዩን ከኢንቨስትመንት አስተዋጽኦ ብቻ ሳይሆን ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ መብት ጋር በጥልቀት መታየቱን የማያረጋግጥ ነው፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የሥራ ሂደት በተለያየ ወቅት ሁለት ውሳኔዎች ምክንያት የግራ ቀኙ የንግድ ምልክቶች ተመሳሳይ መሆናቸው ወይም ያለመሆናቸው የፍሬ ነገር ክርክር ሆኖ በማስረጃ እና በሙያዊ ትንተና የሚጣራ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ አግባብ የንግድ ምልክቶች ተመሳሳይ መሆኑ ወይም ያለመሆን እንደ ፍሬ ነገር አልተጣራም ከተባለ አግባብ ባለው አካል ተጣርቶ እንዲወሰን ወደስር ፍርድ ቤት መመለስ ሲገባው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3) (ሀ) ከተሰጠው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን በማለፍ የአመልካች "CROWNE PLAZA" የንግድ ምልክት ከተጠሪ "CROWN HOTEL" በሚል መጠሪያ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ በመገኘቱ በአዋጁ ቁ.501/98 አንቀጽ 7(1) መሠረት የንግድ ምልክቱ ሊመዘገብ እና ሕጋዊ ጥበቃ ሊሰጠው አይገባም ሲል መወሰኑ የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ማከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሰላም የዴሞክራሲ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ እድገት በማሳካት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት

አላማዎችና እምነቶች መያዛቸውና የእነዚህን ማሰሪያም የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መሆኑን በመግቢያው ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ እነዚህን ዓላማዎችና እምነቶች ለማሳካት መንግሥት የሚከተለውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ፍልስፍና መነሻ ሕገ መንግሥቱን ነው፡፡

ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ዕድገት በማሳካት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት ዓላማዎች እና እምነቶች እውን የሚሆኑት ሥር ሰዶ ያለውን ድህነት በመዋጋት እና በመቅረፍ እንደሆነ ሕገ መንግሥቱ ይገልጻል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ በማምጣት ድህነትን ከማስወገድ ጎን ለጎን ተጨማሪ ሥራዎችን መሥራት እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት የድህነት መቀረፍ ለሌሎች ዓላማዎች እና እምነቶች መሳካት ዋና መሳሪያ ነው፡፡

በአገራችን እየታየ ባለው ለውጥ እና በአደጉ አገሮች እንደታየው አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት ዓላማ እና እምነት የኢኮኖሚያዊ ዕድገት በመገንባት ለውጥ ለማምጣት በተለይ እንደ ኢትዮጵያ የአገር ውስጥ ባለሃብቱ አቅምና ብዛት አነስተኛ በሆነበት ሁኔታ ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ድህነትን ለመቅረፍ መሠረት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41 (4-7) እና 43 (1) የተጣለውን ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለህዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት የመመደብ እና ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል ፕሮጀክት የማካሄድ እንዲሁም በአጠቃላይና በተናጠል የአገሪቱ ዜጎች የኑሮ ሁኔታ የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸውን መንግሥት እንደ ግዴታ ሊወጣ የሚችለው በተመሳሳይ አዳዲስ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በማስፋፋት ዓመታዊ ግብር በመሰብሰብ፣ ተጨማሪ የሥራ መስኮች እንዲፈጠር በማድረግ፣ የቱሪዝም ፍሰቱን እና የውጭ ምንዛሪ ማግኛ መንገዶችን ማመቻቸት እንዲሁም ከቴክኖሎጂ አንጻር ያለውን ውስንነት ለመፍታት የቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር በማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥበቃ ሕጎች ስለንግድ ምልክት መመሳሰል ግልጽ ምላሽ ከሌላቸው የብሔራዊ ኢኮኖሚያዊ የሚዳብርባቸው በኢንቨስትመንት ሲሆን ከአገር ውስጥ

ባለሃብቶች በተጨማሪ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ትልቅ ሚና እንዲኖረው ነው፡፡ በመሆኑም ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎችና እምነቶች ጋር በማጤን ለኢንቨስትመንት ሰፊ በር የሚከፍት ትርጉም መስጠቱ ይበልጥ ሕገ መግሥታዊነት የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ሰበር ሰሚ ችሎት ሕጉን በጠባብ የተተረጎመበት አግባብ ከሕገ መንግሥቱ ውሳኔ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ይህም ውሳኔ የአመልካችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

**የፌ/ም/መ/ቁ.019/08**

**የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የሥራ ዘመን፣ 2ኛ ዓመት፣ 1ኛ መደበኛ ስብሰባ**

**ጥቅምት 2 ቀን 2009 ዓ.ም**

1.አመልካች፡-1ኛ. አቶ ወሰን አለሙ

2ኛ. አቶ ዳዊት ኦትቾ

ተጠሪዎች፡-1ኛ የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም፣

2ኛ. የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ፣

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአመልካቾች የቀረበውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ፣**

የዚህ አቤቱታ መነሻ በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 41/2/ እና አንቀጽ 25 የተደነገጉትን የኢኮኖሚና የእኩልነት መብቶችን የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን የኢፌዴሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው በመሆኑ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት የውሳኔ ሐሳብ በማቅረቡ ነው፡፡

የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ ለምክር ቤቱ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካቾች ሚያዝያ 8 ቀን 2007 ዓ.ም ለጉባኤው ጽፈው ያቀረቡት ማመልከቻ ፍሬ ሀሳብ ቀደም ብሎ በነበረ ልማድ 1ኛ ተጠሪ የሚያሰለጥናቸውን የሕግ ባለሙያዎች በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ለማሰራት ዕጣ በማስወጣት ሰልጣኞች የሚሰማሩበትን ዘርፍ እንዲመርጡ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በዚህ ሂደት ግን ማየት የተሳናቸውን ሰልጣኞች በተመለከተ ዕጣ በማስወጣት ሳይሆን በዳኝነት መሥራት አይችሉም በሚል ልማድ በቀጥታ በዐቃቤ ሕግነት የሚመደብ በመሆኑ አመልካቾች በመረጥነው የሥራ ዘርፍ መሰማራት መብታችን መሆኑን በመጥቀስ በዕጣ ውስጥ እንድንካተት ብንጠይቅም 1ኛ ተጠሪ ጥያቄው አዲስ መሆኑን በመጥቀስ ከማሰልጠን ውጭ ማየት የተሳነው ሰው ዳኛ መሆን ይችላል አይችልም በሚለው ላይ መወሰን እንደማይችል የገለፀልን ሲሆን መልሱን ግን በጽሁፍ ሊሰጠን አልቻለም፡፡ ጥያቄያችንን ለ1ኛ ተጠሪ ቦርድ ብናቀርብም በቀን 23/05/07 ባደረገው ስብሰባ ምንም መነሻ ሳይኖር ማየት የተሳናቸውን ዳኛ አድርጎ

መመልመል የሚከብድ እንደሆነ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የበላይ ተቆጣጣሪነት የባህርዳር ዩኒቨርስቲ በጉዳዩ ላይ ጥናት እንዲያደርግ መፍትሔ መቀመጡን የ1ኛ ተጠሪ ዳይሬክተር እና የቦርዱ ሰብሳቢ ገልፀውልናል፡፡ በተሰጠው መልስ ቅሬታችንን ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ብናቀርብም ጉባኤው ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ካልተመራልኝ ጉዳዩን አላይም በማለት ምላሹን ሰጥቶናል፡፡ በመቀጠል ቅሬታችንን ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ ለምክር ቤቱ የሕግ ቋሚ ኮሚቴ እና ለክልሉ አስተዳደር ቅሬታ ክፍል ብናቀርብም ጥያቄያችን ምላሽ አላገኘም፡፡ በመሆኑም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41(2) የተቀመጠው በመረጥነው ሙያ የመሰማራት መብታችን ተጥሷል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች ቅሬታቸውን ለአ/ብ/ክ/መንግሥት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም ለአ/ብ/ክ/መ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ተቋም ቦርድ፣ ለአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ለአ/ብ/ክ/መ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ፣ ለአ/ብ/ክ/ ምክር ቤት የሕግ ቋሚ ኮሚቴ እና ለአ/ብ/ክ/መ የሕዝብ ቅሬታ ሰሚ ጽሕፈት ቤት ማቅረባቸውን የሚያሳይ የማመልከቻውን ቀሪ ኮፒ በማድረግ አያይዘው አቅርበዋል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቁ. አጣጉ/335/02/08 እና አጣጉ 335/02/08 በቀን 02/02/2008 ለ1ኛ እና ለ2ኛ ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው በተፃፈ ደብዳቤ ባደረገው ማጣራት፡-

1ኛ ተጠሪ የአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዮት በደንብ ቁ.74/2003 መሠረት ሲቋቋም ከተሰጠው ስልጣን አንዱ በዩኒቨርስቲ የሕግ ዲግሪ ያላቸውን ተመራቂዎች በቅድመ ሥራ ሰልጣኝነት መልምሎ በማስገባት በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከትና በሥነ ምግባር በማብቃት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በማክበርና በማስከበር ለተጀመረው የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት የፍትህ ሥርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ባለሙያ በማፍራት ወደ ፍትህ ሥርዓቱ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ሰልጥነው የሚመረቁ ሰልጣኞች የሚመደቡት በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት ሲሆን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና በፍትህ ቢሮ በዕጣ ለይተን እንድንሰጣቸው ሲስማሙ እንጂ የኢንስቲትዩት ኃላፊነቱ ሆኖ አይደለም፡፡ ሆኖም ዕጣ በምናወጣበት ጊዜ ማየት የተሳናቸው ሰልጣኞች ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበው ከሥራው ባህርይ አንፃር ዳኛ እንዲሆኑ ያልተፈቀደላቸው

ስለሆነ በቀጥታ ዐቃቤ ሕግ ሆነው እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም አቤቱታቸውን ለክልሉ ምክር ቤት አቅርበው የሥራው ባህርይ ግምት ውስጥ ገብቶ ዐቃቤ ሕግ እንዲሆኑ የወሰነ በመሆኑ እንጂ በእኛ በኩል የተደረገ ክልከላ የሌለ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ በሚል ምላሹን ሰጥቷል፡፡

2ኛ. ተጠሪ በበከሉ ቅሬታቸውን ለጉባኤ ጽሕፈት ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን በእኛ በኩል በወቅቱ የተሰጣቸው ምላሽ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተን ስላልሆነ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቱንና ቦርዱን እንዲጠይቁ ምላሽ ሰጥተናቸው እንደነበር እናስታውሳለን የሚል ነው።

በክልላችን ውስጥ የዳኞችና የአቃቤ ሕጎች ምልመላና ስልጠና የሚካሄደው በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም አማካኝነት ነው፡፡ ስልጠናቸውን አጠናቀው ሲጨርሱ በዕጣ ወደ ፍርድ ቤት እና ዐቃቤ ሕግነት የሚገቡትን ለይቶ እንድንመድባቸው ይልክልናል፡፡ በዚህ ሂደት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤም ይሁን ጽ/ቤታችን ያለው ሚና ስልጠናቸውን አጠናቀው የተመደቡለትን በረዳት ዳኝነት መድቦ ሲከታተል ከቆየ በኋላ ለዳኝነት ብቁ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ለክልል ምክር ቤት ቀርበው እንዲሾሙ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በእኛ በኩል ወደ ዳኝነት ወይም ወደ ዐ/ሕግነት ይግቡ የሚለውን የመወሰን ስልጣንና ኃላፊነት የሌለን በመሆኑ ሙሉ ምላሽ ለመስጠት እንቸገራለን፤ ይሁን እንጂ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም በቦርድ የሚመራ በመሆኑና የጠቅላይ ፍርድ ቤቱም የቦርዱ አባል በመሆኑ ከቦርዱ ሰብሳቢና ከማሰልጠኛ ተቋሙ ጠይቀን እንደተረዳነው አሁን ቅሬታ ያቀረቡት ሰዎች በወቅቱ ለማሰልጠኛ ተቋሙ ቦርድ አቅርበው እንደነበር ተገልፆልናል፡፡

ቦርዱም ያቀረቡትን ቅሬታ በአግባቡ እንደመረመረ፣ በምርመራ ሂደቱ ወቅትም የዳኝነት ሥራ በአካል ምስክሮችን ማየትና ማስረጃውን ማረጋገጥ የሚጠይቅ መሆኑን በዚህ ረገድ በዓለም ላይም ይሁን በአገራችን ማየት የተሳናቸውን በዳኝነት መደብ የማሰራት ልምድ እንደሌለና እንደተቸገረ፣ በዚህ ምክንያት የተሻለው የሥራ ስምሪት ዐቃቤ ሕግ መሆኑን ተገንዝቦ ወደ ዐቃቤ ሕግነት የመደባቸው መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም ከዓለም አቀፍም ይሁን ከአገር አቀፍ ልምድ አንፃር ሲታይ የዳኝነት ሥራ ከአለው አስቸጋሪነት አንፃር ማየት የተሳናቸውን መድቦ ማሰራት ሊፈጥር የሚችለውን

ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ለእነሱ አመች ወደሆነው የሥራ ስምሪት የመደባቸው መሆኑን እንደተገለፀልን እና በእኛ በኩልም የቦርዱ ይሁን የማሰልጠኛ ተቋሙ አሰራር ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንገልፃለን፣ በማለት ምላሹን ሰጥቷል፡፡ ጉባኤው የተጠሪ ተቋማት ኃላፊዎችን ጠርቶ ቢያናግርም የተለየ ምላሽ ሊያገኝ አልቻልም፡፡

የአመልካቾች ቅሬታ በተጠሪዎች በተያዘ የአሰራር ልማድ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41/2// የተረጋገጠልን በመረጥነው ሙያ የመሰማራት መብታችን ተጥሷል በሚል ነጥብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከሰጡት ይፋዊ ምላሽ፣ በተጠሪዎች ዘንድ ማየት የተሳናቸው ሰልጣኞች በዳኝነት ሥራ ለመሰማራት የሥራው ፀባይ አይፈቅድላቸውም ከሚል መነሻ ማየት የተሳናቸውን ሰልጣኞች በዳኝነት ወይም በዐቃቤ ሕግነት የሥራ ዘርፍ ለማሰማራት በሚደረገው የዕጣ ማስወጣት ሂደት አሳታፊ ያለማድረግ የአሰራር ልማድ እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡ ኢትዮጵያ ተቀብላ በአዋጅ ቁ.676/2002 ያፀደቀችው የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን አንቀጽ 27 ሥራና ቅጥር በሚል ርእስ፡-

> የተዋዋይ መንግሥታት አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር በእኩልነት የመሥራት መብት ያላቸው መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ይህም ለአካል ጉዳተኞች ክፍት፣ አካታችና ተደራሽ በሆነ፣ በነፃነት በተመረጡና ወይም በሰራተኛ ገበያና የሥራ አካባቢ ተቀባይነት ባገኘ ቦታ ውስጥ በመሥራት ኑሮን ለመምራት ዕድል የማግኘት መብቱን ይጨምራል፡፡ ተዋዋይ መንግሥታት ተቀጥረው በመሥራት ሂደት ውስጥ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ጨምሮ የመሥራት መብታቸውን ያስጠብቃል፣ ያበረታታል፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ሕግ መደንገግን የጨመረ ሆኖ ከሌሎች ነገሮች መካከል የሚከተሉትን እውን ለማድረግ ነው፡፡

ሀ. ምልመላ፣ ቅጥር፣ ሥራን የመያዝ፣ የቅጥር ቀጣይነት፣ ሙያን ማሳደግና አደጋ የለሽና ጤናማ የሥራ ሁኔታዎችን የተመለከቱትን ጨምሮ ከሁሉም የቅጥር ዓይነቶች በተያያዙ ጉዳዮች በአካል ጉድለት ምክንያት የሚደርሱ አድልዎን መከላከል… የሚል ድንጋጌ ተካቶ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ እና በሙሉ ስምምነቱ ኢትዮጵያ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሥራ ምልመላን ጨምሮ በተለያየ መልኩ አድልኦ እንዳይፈፀም ኃላፊነት ወስዳለች፡፡ እንዲሁም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣው የአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት

መብት አዋጅ ቁ.(568/2000) አንቀጽ 4 የአካል ጉዳተኞችን የሥራ ስምሪት መብት ስለመጠበቅ በሚል ርዕስ፡-

1. የሥራው ጠባይ የማይፈቅድ ካልሆነ በስተቀር የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛዎችን አሟልቶ የተገኘና በውድድር ውጤቱ ብልጫ ነጥብ ያገኘ ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ በምንም ዓይነት መልኩ መድሎ ሳይደረግበት፣

ሀ. በማንኛውም መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ የሚገኝ ክፍት የሥራ ቦታን በቅጥር፣ በዕድገት በድልድል ወይም በዝውውር ለመያዝ ወይም

ለ. በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሚሰጥ የስልጠና ፕሮግራም ለመሳተፍ መብት አለው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛዎችን አሟልቶ የተገኘና ለወድድር ውጤት እኩል ወይም ተቀራራቢ ነጥብ ያገኘ ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ በምንም ዓይነት መልኩ መድልዎ ሳይደረግበት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ እና /ለ/ ለተመለከቱት መብቶች ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

3. በሥራው ጠባይ አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርት በተወደዳሪው ላይ ያለውን ጉዳይ የሚመለከት መሆን የለበትም፡፡

በሚል የተደነገገ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛዎችን አሟልተው ነገር ግን ውድድር ባለመኖሩ በውድድር ባይሳተፉም በሚከናወነው የዕጣ ስምሪት ግን እንዳይሳተፉ መከልከሉ ድንጋጌውን ያከበረ አይደለም፡፡ ድንጋጌው የሥራው ፀባይ የማይፈቅድ ካልሆነ በቀር.. በሚል ዓረፍተ ነገር የሚጀመር ሲሆን ለዚህ ዓረፍተ ነገር በአዋጁ አንቀጽ 2(8) ‹‹የሥራው ፀባይ የማይፈቅድ›› ማለት ተፈላጊውን ችሎታ የሚያሟላ የአካል ጉዳተኛ ተመጣጣኝ ማመቻቸት ተደርጎለትም ቢሆን ሊያከናውነው የማይችል ሥራን ያመለክታል›› በሚል የተተረጎመ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህም በመነሳት አመልካቾች ተመጣጣኝ ማመቻቸት ቢደረግላቸው ሥራውን ሊያከናውኑ እንደማይችሉ በተጠሪዎች የቀረበ አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡

የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41(2) «ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው» በሚል ተደንግጎ የሚገኝ ነው፡፡

መብቱ ፍፁም ያልሆነ እና ሊገደብ የሚችል ቢሆንም የአንድ ሥራ ተፈጥሯዊ ባህርይ አንዱን ከሌላው መለያ ሊሆን የሚችለው ሥራው ከተፈጥሯዊ ባህርይው የሚጠይቀው ቅድመ ሁኔታ በድንገት ወይም በምርጫ የሚጠይቅ ሳይሆን የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ከሥራው ባህርይ በሚል መነሻ በአሰራር የተጣለው ገድብ ከላይ ኢትዮጵያ ከተቀበለችው ዓለም አቀፍ ስምምነትም ሆነ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ከወጣው አዋጅ በተለይ በሌሎች አገራት ካለው ተሞክሮ አንፃር በበቂ ጥናት ወይም ምክንያት ላይ የተመሰረተ እና የግድ አስፈላጊ በሆነ ቅድመ ሁኔታ ላይ መሠረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም ያሰራር ልማዱ ከላይ የተጠቀሰውን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የሚያጣብብ ነው፡፡ እንዲሁም አመልካቾች በአሰራር ልማዱ ልዩነት የተደረገባቸው በመሆኑ የተያዘው ልማድ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 25 ‹‹ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው በመካከለቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ አኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው በሚል የሰፈረውን የእኩልነት መብት የሚጋፋ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልገው ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ይኸው ጉዳይ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ የሚል ነው፡፡

ምክር ቤቱም የአጣሪ ጉባኤውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የምክር ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ እንደተረዳው አመልካቾች የዳኝነት ይሁን የዓቃቤ ሕግነት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልገውን የሕግ ትምህርት ተምረው እና ለዚሁ ተግባራዊ ሥራ ብቁ የሚያደርጋቸውን በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የሚሰጠውን የቅድመ ሥራ ስልጠና ወስደው በማጠናቀቅ ተመርቀው እያሉ 1ኛ ተጠሪ አመልካቾችን አብረዋቸው እንደሰለጠኑት ሌሎቹ ሰልጣኞች እኩል ጥበቃ በማድረግ በዳኝነት ወይም በዓቃቤ ሕግነት ተመድበው እንዲሠሩ ለመወሰን ዕጣ እንዲያወጡ ማድረግ ሲገባው ይህንን ወደ ጎን በመተው ማየት የተሳናቸው በመሆናቸው ብቻ በሕግ ያልተደነገገን “ማየት የተሳናቸው የዳኝነት ሥራን መሥራት አይችሉም” የሚል ልማዳዊ አሰራርን በመከተል አመልካቾችን ከዕጣ ድልድል ውጭ በማድረግ በዓቃቤ ሕግነት እንዲመደቡ አድርጓል፡፡

ምክር ቤቱ እንደተገነዘበው አመልካቾች በዳኝነት እንዳይሰማሩ የሚከለክል ሕግ ካለመኖሩም በላይ በአጣሪ ጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ በዝርዝር እንደተገለፀው ተጠሪዎች የሰጡት ውሳኔ በአካል ጉዳተኞች የሥራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁ.568/2000 እና አገራችን ኢትዮጵያ በአፀደቀችው በአዋጅ ቁ.676/2002 ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብት ኮንቬንሽን ድንጋጌዎች መሠረት የሥራው ጠባይ የማይፈቅድ ካልሆነ በስተቀር ተፈላጊው የችሎታ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ አካል ጉዳተኞችን በአካል ጉዳታቸው ምክንያት መድልዎ እንዳይደረግባቸውና ተመጣጣኝ ማመቻቸት ተደርጎላቸው ጭምር ሊያከናውኑት በሚችሉት በመረጡት የሥራ ዘርፍ እንዲሰማሩ ያላቸውን መብት የሚጋፋ አሰራርና ውሳኔ ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪዎች ተቀባይነት በሌለው ልማዳዊ አሰራር መሠረት የሰጡት ውሳኔ በኢ.ፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 41(2) ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ሥራውን እና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው በሚል የተደነገገውን እንዲሁም በአንቀጽ 25 የተደነገውን የአመልካቾች ሕገ መንግሥታዊ የእኩልነት መብት የሚጋፋ በመሆኑ የተጠሪዎች የልማድ አሰራር እና ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

ሰኔ 2010 ዓ.ም

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ መንግሥታዊ ውሳኔዎች መጽሔት

## ቅጽ 3

ሰኔ 2010 ዓ.ም

## በሕገ መንግሥት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች እና በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬቶች የተዘጋጀ


**አዘጋጆች**

**ሙልዬ ወላለው**

**ዮሴፍ ጋይም**

**ያውቃል በቀለ**

**ኤዲተሮች**

**ምሕረት ተስፋዬ**

**ሞገስ ጀንበር**

**ብርቱካን መለስ**